ኢፕድ

# አዲስ ዘመን

ሐሙስ | 82ኛ ዓመት ቁጥር 054 ጥቅምት 24 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10:00 | ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!




## ባጎረሰ የተነከሰው የመከላከያ እጅ

ዳግማዊት ግርማ

በወታደር ሕይወት ውስጥ የመኖር እንቅስቃሴዎች እንደ ማንኛውም የሰው ልጅ አይነት አይደሉም። በውትድርና ኑሮ ቀን ለሠራዊት ማታ ለአራዊት የሚባል ታሪክ የለም፤ ቀንም ሌትም ለሀገሩ በዘብነት ይኖራል እንጂ። በመኖር ኡደቱ ውስጥ ማህበራዊ ሕይወት እርም ነው። እቁብ መጣል እድር መግባት በሰአት መብላት መጠጣት ህልም ነው። የሚወዱትን ቀጥሮ የወደዱትን ሊያገኙ መግባት መውጣት አይታሰቡም። ከፍቅርም ከራስም ከቤተሰብም በላይ ሀገር ትበልጣለች።

ወታደር በእድሜው የኔ የሚለው አንዳች እንኳ የለውም፤ እንኳን የእሱ የሆነውና ነፍሱን ያለመሰሰት ለክብርት ሀገሩ በመስጠት በክብር ይዋደቃል እንጂ። ነግጄ አትርፌ፣ አርሼ አጭጄ የሚለው ንብረት የለውም። በሞት መንገድ ላይ ሲዘዋወር ለአፍታ እንኳ አያቅማማም፤ በነፍሱ ይወራረዳል እንጂ። በሀገር ጉዳይ ላይ ቀልድ የለም፤ ነፍሱን ለመስጠት ቃል የገባ ቀን ሕይወቱ የእሱ

ባጎረሰ የተነከሰው ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



## የሰላም ስምምነቱ ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓቱንና የኢትዮጵያን ብሔራዊ ጥቅም ባስከበረ መልኩ ተጠናቀቀ

በጋዜጣው ሪፖርተር

አዲስ አበባ፡- በደቡብ አፍሪካ ላለፉት 10 ቀናት በመንግሥት እና በሕወሓት መካከል ሲካሄድ የቆየው የሰላም ንግግር ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓቱንና የኢትዮጵያን ብሔራዊ ጥቅም ባስከበረ መልኩ መጠናቀቁን መንግሥት አስታወቀ።

የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት ሚኒስትር ለገሰ ቱሉ(ዶክተር) በማህበራዊ ትስስር ገጻቸው ባወጡት ጹሑፍ እንዳስታወቁት፤ የሰላም ስምምነቱ ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓቱንና ብሄራዊ ጥቅማችንን ባስከበረ

የሰላም ስምምነቱ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



ፎቶ ፡- ሐዱሽ አብርሃ

## «የውጭ ሃይሎች ተጽእና በኢትዮጵያ ተሳሳኪ መንግሥት በማስቀመጥ እንደፈለጉ ለማሽከርከር ነው»

- ብርጋዴል ጀነራል አሰፋ አህፈርያም የቀድሞ የጦር ሠራዊት አባል

ገጽ 4




## ጥቅምት 24 ሲታሰብ የአሸናፊና የተሸናፊ ትርክት ለመፍጠር ሳይሆን ተመሳሳይ ታሪክ እንዳይደገም ለማድረግ ነው

- በሠራዊቱ ላይ ክህደት የተፈጸመበት 2ኛ ዓመት ዛሬ ታስቦ ይውላል

ገጽ 4

ደርባ ሚድሮክ ሲሚንቶ ኃ/የተ/የግል ማህበር
DERBA CEMENT

በልዩ የደርባ ሲሚንቶ መስመር 8688 ወይም
- 0111 26 26 27 - 0922 11 53 24/26
- 0111 26 26 28 - 0922 72 74 48/49
- 0111 26 26 29 - 0922 72 38 70
- 0111 26 26 30 - 0922 72 38 72
ፋክስ፡- 0111 26 23 45 እና 0111 26 23 18
ይዘዙን
ደረጃቸውን ጠብቀን የምናመርታቸውን ጥራት ያላቸው የሲሚንቶ ምርቶች ቤትዎ ወይም ፕሮጀክትዎ ደጃፍ ላይ ያለውጣ ውረድ በደርባ ትራንስፖርት ኃ.የተ.የግ.ማ አማካይነት እናቀርባለን።
ነገን ዛሬ እንሥራ

eccs
የኢትዮጵያ የግንባታ ግብዓቶች አቅራቢ ኃ/የተ/የግል ኩባንያ
ETHIOPIAN CONSTRUCTION COMMODITIES SUPPLY PLC.
የአርማታ ብረት እና ሌሎች ብረታብረቶች አከፋፋይ

Mob. 0911 225057/ 0989 343434
አድራሻ፡ ከሜክሲኮ አደባባይ ወደ መርካቶ በሚወስደው መንገድ ከዲ-አፍሪክ ሆቴል ፊት ለፊት

ሲዳማ ባንክ
Sidama Bank
Bank for All!
ሲዳማ ባንክ
ባንካችን የተሟላ የባንክ አገልግሎት መስጠት የሚያስችል ቅድመ-ሁኔታዎችን አጠናቅቆ በቅርቡ ሥራ ለመጀመር መዘጋጀቱን ስንገልፅ በታላቅ ደስታ ነው
አድራሻ:
ስልክ +251944119303, +251462123591, +251462200850,
ፖስታ ሣጥን ቁጥር 565,
ፋክስ +251462200850,
SWFT ኮድ: SIDANETAA
ኢ-ሜል : Info@sidamabank.com,
ዌብ ሳይት: www.sidamabank.com
ሲዳማ ባንክ የሁሉም ባንክ!



# ጥቅምት 24 የሠራዊቱ የመስዋዕትነት እና የድል አድራጊነት ገድል ማስታወሻ ነው

**ሞገስ ተስፋ**

<u>አዲስ አበባ</u>፡- ጥቅምት 24 ቀን 2013 ዓ.ም አሻባሪው ሕወሓት በሰሜን ዕዝ ላይ ያደረሰው ጥቃት ሲታወስ ሠራዊቱ ለሕዝብና ለአገር የከፈለውን መስዋዕትነት እና ድል አድራጊነት በመዘከር መሆን እንዳለበት የቀድሞ ጦር ሠራዊት አባል ተናገሩ። ኢትዮጵያ በታሪኳ ስንዴ ለምና ብታውቅም ነጻነት ለምና እንደማታውቅም አስታውሰዋል።

የቀድሞው የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት የድጋፍና የልማት ማሕበር ፕሬዚዳንት ሃምሳ አለቃ ብርሃኑ አማረ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ጥቅምት 24 ቀን 2013 ዓ.ም አሸባሪው ሕወሓት በሰሜን ዕዝ ላይ ያደረሰው ጥቃት የማይረሳ ጥቁር ጠባሳ ያረፈበትና ኢትዮጵያን ለማፍረስ ረጅም ርቀት የተሄደበት ቀን የሚታሰብበት ነው።

አሸባሪው ቡድን የዜጎቿን ደህንነትና የአገሪቱን ሉዓላዊነት ዳር ድንበር ለማስከበር ከቤታቸው ወጥቶ አደር ሆነው መስዕዋትነት የሚከፍሉ የቁርጥ ቀን ልጆቿ ላይ የደረሰው ጥቃት ጥቁር ጠባሳ ስለሆነ የሚረሳ አይደለም ነው ያሉት ሃምሳ አለቃው።

ሃምሳ አለቃ ብርሃኑ እንደተናገሩት፤ ኢትዮጵያ በታሪኳ ብዙ ፈተናዎችን አስተናግዳ አልፋለች። አሸባሪው ቡድን በሰሜን እዝ ላይ ያደረሰው ጥቃት ግን የማይታመን ጥቁር ታሪክ ነው።

ቡድኑ የቀድሞ የመከላከያ ሠራዊትን ሕገ ወጥ በሆነ መንገድ የበተነበት ስራ የሚታወቅ ነው ያሉት ሃምሳ አለቃ ብርሃኑ፤ በሰሜን እዝ ላይ የደረሰው ጥቃትም ሌላኛው የቡድኑ መገለጫ ባህርይ ነው ብለዋል።

በሰሜን ዕዝ ላይ የደረሰው ጥቃት ለየት የሚያደርገው ራሱ ኮትኩቶ አሳድጎ፣ ራሱ አለቃ፣ አዛዥ ሆኖ፣ እንደቤተሰብ፤ እንደመንግሥት መሪ ሆኖ፣ ለኢትዮጵያ ጠበቃ እንሆናለን፣ ለኢትዮጵያ ሕዝብ መስዋዕት እንሆናለን ብለው ምሽግ ውስጥ የሚገኘውን ሠራዊት መሆኑ የቡድኑን ጭካኔ የሚያሳይ እንደሆነም ጠቁመዋል።

ከ20 ዓመት በላይ በቀበሮ ጉድጓድ ውስጥ ሆነው ራሳቸውን ጎድተው ወገናቸውን ለመጠበቅ እየኖሩ ከሕይወታቸው ባሻገር ከሚያገኙት ደመወዝ በመቀነስ ትምህርት ቤት እየገነቡ፣ አንበጣ ሲመጣ እያባረሩ፣ በእርሻ ወቅት እያረሱ፣ አዝመራ ሲደርስ እያጨዱ፣ ከሬሽናቸው እያካፈሉ፣ ከልብሳቸው ቀንሰው እያለበሱ በኖሩ የሠራዊት አባላት ላይ እንዲህ አይነት ጥቃት መፈጸም ከሰው ልጅ የማይጠበቅ የአረመኔነት ጥግ መሆኑንም ሃምሳ አለቃ ብርሃኑ ጠቁመዋል።

እንደቤተሰብ አብረው አንድ ላይ ከኖሩት ጓዶቻቸው ይከሰትብናል ብለው ባላሰቡበት መንገድ ዘግናኝ ጭፍጨፋ መድረሱም የሚያሳምም እንደሆነ ነው ያብራሩት።

ጥቅምት 24 አገርን ለማፍረስ አሸባሪው ቡድን የሄደበትን ርቀት የተመለከትንበት ነው ያሉት ሃምሳ አለቃ ብርሃኑ፤ ዜጎቿ በማይጠበቅ መንገድ መስዋዕትነት የከፈሉበት ቀን ነው። ለወታደር መስዋዕትነት ቋሚ ሕይወቱ ነው። በአገርና በወገን ለመጣ የወታደር ስራው መሰዋእት በመሆኑ ሠራዊቱ የከፈለው ይህን ነው። የምንጽናናው ስለኢትዮጵያ ብሎ የከፈለው ዋጋ ስለመሆኑ ተናግረዋል።

ጥቅምት 24 ሲታወስ ሠራዊቱ መኩራት ያለበት ምንም ወገኖቹ የነበሩ የራሱ ሰዎች ጥቃት ቢፈጽሙበትም የከፈለው መስዋዕትነት ስለኢትዮጵያና ስለኢትዮጵያውያን በመሆኑ የሚኮራበት ቀን ነው ሲሉም ተናግረዋል።

መከላከያ ሠራዊት ከተጠቃ በኋላ ከወደቀበት ተነስቶ አሸባሪ ቡድኑን ድባቅ በመምታት ድል የነሳ ጀግናና ድል አድራጊ ሠራዊት መሆኑን ጭምር መዘከር ያስፈልጋል። ድል አድራጊ ሠራዊት ቀኑ ሲከበር የሚኮራበት እንጂ የሚሳቀቅበትና የሚያዝንበት ቀን አይደለም ብለዋል።

የተፈጸመው ጥቃት እጅግ ዘግናኝ፣ ሰቅጣጭ ቢሆንም ከደረሰበት ጥቃት ተነስቶ አሸናፊ መሆኑን ሠራዊቱ አስመስክሯል ያሉት ሃምሳ አለቃ ብርሃኑ፤ ኢትዮጵያ በታሪክ ስንዴ ለምና ሊሆን ይችላል፣ ነጻነት ግን ለምና የማታውቅ አገር መሆኗን አሁንም ዳግም ያስመሰከረ ሠራዊት ነው ብለዋል።

ጥቅምት 24 ሲከበር ሠራዊቱ የጀግና ሕዝብ ልጅ ድል አድራጊ ሠራዊት በመሆኑ ድሉን እያሰብን ጀግንነቱን በመዘከር መስዋዕትነቱ ለሕዝብና ለአገር መሆኑን እየተዘከረ በመላው ኢትዮጵያ ማክበር እንደሚስፈልግ ሃምሳ አለቃ ብርሃኑ ጠቁመዋል።



አቶ መስፍን ደሳለኝ

## ሰሜን እዝ ላይ የተሰነዘረው ጥቃት የሀገር ክህደት ማሳያ ጥግ ነው

**መኣርግ ገ/እግዚአብሔር**

<u>አዲስ አበባ</u>፡- ጥቅምት 24 ቀን 2013 ዓ.ም አሸባሪው ሕወሓት በሰሜን እዝ ላይ የፈጸመው ጥቃት የሀገር ክህደት ማሳያ ጥግ ነው ሲሉ የትግራይ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ (ትዴፓ) ምክትል ሊቀመንበር አቶ መስፍን ደሳለኝ ተናገሩ።

አቶ መስፍን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የሕወሓት ሽብር ቡድን ኢትዮጵያን ሲጠብቅ በነበረው ሠራዊት ላይ ጥቃት መፈፀሙ የኢትዮጵያን ሉዓላዊነት ደፍሯል።

ሠራዊቱ የሕዝብን ደህንነት ወይም የሀገርን ሉዓላዊነት የሚጠብቅ ሃይል ነው፤ ሆኖም ግን ባልተጠበቀ ሁኔታ በአሸባሪው ሃይል ከጀርባው መጠቃቱ አሳዛኝ ክስተት ነው ብለዋል።

ይህ የቡድኑ ድርጊት የሀገር ክህደት ወንጀል ነው ያሉት አቶ መስፍን፤ የሽብር ቡድኑ የትግራይ ሕዝብ አካል በሆነ የሀገር መከላከያ ሰራዊት ላይ ሃገር የሚያፈርስ የክህደት ተግባር በመፈጸሙ በታሪክ ሲወቀስ እንደሚኖር ተናግረዋል።

አሸባሪው ቡድን እንዳሰበው ሳይሆን ኢትዮጵያን የማፍረስ ዕቅዱ ከሸፏል፤ ህልሞቹ ከንቱ ሆነዋል። የኢትዮጵያ ሕዝብ በቁርጠኝነት ተነስቶ በአጭር ጊዜ ውስጥ እኩይ ተግባሩን አክሽፎታል ሲሉ አስረድተዋል።

የሀገር መከላከያ ሠራዊትን ማጥቃት ማለት የሀገርን ሉዓላዊነት አደጋ ላይ መጣል ማለት ነው። ይህ ክህደት ደግሞ በኢትዮጵያውያን ህሊና የማይረሳና በየአመቱ ሊዘከር የሚገባው ቀን ነው ብለዋል።

እንደ አቶ መስፍን ገለጻ፤ የሕወሓት አሸባሪ ቡድን በትግራይ የተለያዩ የልማት ስራዎችን ሲያከናውን በነበረው ሠራዊት ላይ ጥቃት መፈጸሙ ሕዝቡንም ጎድቶታል።

ሠራዊቱ በትግራይ ውስጥ ለብዙ ዓመታት የቆየ በመሆኑ በባህልና በቋንቋ ከሕዝቡ ጋር ተዋህዶ እንደነበር አስታውሰዋል።

ከዚህ አልፎ እንደትምህርት ቤት የጤና ተቋማትና የተለያዩ መሰረተ ልማቶችንም ሲገነባ መቆየቱን አንስተዋል። ጥቃቱ ከተፈጸመ በኋላ ግን ሠራዊቱ የሚያከናውናቸው የልማት ስራዎች በሽብር ቡድኑ ወድመዋል ሲሉ ገልጸዋል።


የሽብር ቡድኑ በፈፀመው የክህደት ተግባር ምክንያት በትግራይ ሕዝብ ላይ ከፍተኛ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊና ሥነ-ልቦናዊ ችግሮች መከሰቱንም ተናግረዋል።


አቶ መስፍን እንዳስታወቁት፤ የወራሪው ቡድን በየጊዜው በሚፈጥረው ጸብ አጫሪነት በርካታ የትግራይ ነዋሪዎች ላላመኑበት ጦርነት እንዲማገዱ ምክንያት ሆኗል።

ቡድኑ ካደረሰው ጉዳት ባለፈ ዕውነትን የማጣመም ባህሪ እንዳለው የገለፁት አቶ መስፍን፤ የፈፀመው ክህደት አልበቃ ብሎው የትግራይን ሕዝብ በእሱ ላይ እንዳይነሳ የሀሰት ፕሮፓጋንዳ በመንዛት ለጊዜው ሊያዳናግረው መቻሉን ጠቁመዋል።

የትግራይ ሕዝብ ከዚህ ቡድን ተጠቃሚ መሆን ስለማይችል አዲስ አስተሳሰብ፣ አደረጃጀትና ለሕዝቡ የሚስማማ የፖለቲካ ሃይል ያስፈልገዋል ብለዋል።

የትግራይ ሕዝብ የችግር መንስኤ የሕወሓት ሽብር ቡድን በመሆኑ ሰላሙንና ልማቱን የሚያረጋግጥ ሌላ አዲስ ፓርቲ ያስፈልገዋል ሲሉ አቶ መስፍን አሳስበዋል።






# «ሕወሓት በመከላከያ ሠራዊት ላይ ያደረሰው ዘግናኝ ጥቃት ታሪክ ይቅር የማይለው ነው»

*- የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪዎች*

**በኃይሉ አበራ**

<u>አዲስ አበባ</u>፡- ሕወሓት በኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት ላይ ያደረሰው ዘግናኝ ጥቃት ታሪክ ይቅር የማይለው ነው ሲሉ ኢፕድ ያነጋገራቸው የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪዎች ገለጹ።

የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪ የሆኑት አቶ ልዑልሰገድ ማሞ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የሽብር ቡድኑ ሕወሓት በኩል የነበረው እሳቤ ሕገወጥ በመሆኑ በመከላከያ ሠራዊቱ ላይ ጥቃት አድርሷል። የሽብር ቡድኑ በኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት ላይ ያደረሰው ዘግናኝ ጥቃት ታሪክ ይቅር የማይለው ነው።

ጥቃት የደረሰበት የሀገር መከላከያ ሰሜን እዝ በልቶ ጠግቦ የማያውቅ፣ ከመከራ ያልወጣ፣ በስቃይ የቆየ ሆኖ ሳለ በዚህ መልኩ የጭካኔ ድርጊት ሲፈጸምበት ማየት ታሪክም ይቅር የማይለው እና ኢትዮጵያ የሚኖሩ ጥቁር መዝገቦች ካሉም አንደኛው ሆኖ የሚመዘገብ ነው ያሉት አቶ ልዑልሰገድ፤ ድርጊቱም ቃላት በቃላት ቢደራረቡ የማይገልጹት አሳዛኝ ድርጊት ነው ብለዋል።

እንደ አቶ ልዑልሰገድ ገለፃ፤ ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባ ለኢትዮጵያ ሥልጣኔ ለሰው ልጆች አብሮነት እና መልካም ማሰብ እንጂ ጦርነት ቅድሚያ የሚሰጠው አይደለም። የሽብር ቡድኑ በነበረው ያልተገባ አስተሳሰብ እና ራስወዳድነት መከላከያው ላይ ጥቃት በመክፈት ሀገር ላይ አደጋ ደቅኖ ነበር።

ሆኖም በአሁኑ ጊዜ መከላከያ ቡድኑን አይቀጡ ቅጣት እየቀጣው መሆኑን በመጠቆም፤ ከመከላከያ ጎን በመቆም አገርን መጠበቅ የእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ የግል ጉዳይ ነው ሲሉም አሳስበዋል። ሁሉም ሰው በትንሹ እንኳን ባለበት ስፍራና ግዳጅ ለኢትዮጵያ ታማኝ በመሆን አገሪቷ በጠየቀችው ሁሉ አስተዋጽኦ ማድረግ እንደሚገባ አመላክተዋል።

የሽብር ቡድኑ መከላከያ ሠራዊት ላይ ያደረሰው ጥቃት እጅግ የሚያሳዝን መሆኑን በመጥቀስ፤ ሁሉንም ሰው አንድ አድርጎ ያሰባሰበን ኢትዮጵያዊነት ከምንም ነገር በላይ ቅድሚያ የሚሰጠው መሆኑን ገልጸው አገር መከላከያም ሕይወቱን እስከመስጠት ድረስ ኢትዮጵያዊነትን እና ሀገራዊ አንድነትን ለማስጠበቅ የሚሠራ በመሆኑ ክብር ይገባዋል ብለዋል።

መከላከያ ኢትዮጵያ በአሁኑ ጊዜም ለገጠማት ከባድ ፈተና የቀጣዩ የብሩህ ተስፋች መጨረሻ ነው ያሉት አቶ ልዑልሰገድ፤ የኢትዮጵያ መከላከያ የአንድ ትልቅ አገር ሉዓላዊነት ከምንም ነገር በላይ የሚጠብቅ እና በተለያዩ አገራዊ ችግሮች ከፊት የሚሆን ነው ብለዋል።

በትግራይ የሚገኙ ኢትዮጵያውያን ወንድሞችም ለሁሉም የማይጠቅመውን የተዛባውን አስተሳሰብ በመታገልና በማስወገድ በሰላም እና በአብሮነት በሰላም እንኑር ሲሉም መልዕክት አስተላልፈዋል።

ሌላዋ የአዲስ አበባ ነዋሪ ወይዘሮ ታደለች ሰርቤሳ በበኩላቸው፣ በመከላከያ ሰሜን እዝ የደረሰው የጭቃኔ ድርጊት ሲታወስ በኢትዮጵያዊነታቸው ልባቸው እንደሚያዝን እና መደገም የሌለበት መሆኑን ገልጸው ድርጊቱ ታሪክ ይቅር የማይለው መሆኑን አመላክተዋል።

እንደ ወይዘሮ ታደለች ገለፃ፤ መከላከያ ሠራዊት ብሔርን፣ ዘርን ሀገርን ሳይመርጥ ለሁሉም የቆመ አካል በመሆኑ በዚህ መልኩ መጠቃቱ አሳዛኝ ድርጊት ነበር። ኢትዮጵያ ለአንዱ የእንጀራ እናት ለሌላው እናት ሳትሆን ለሁሉም እኩል የሆነች የጋራ አገራችን መሆኗን አውቀን አንድ መሆን አለብን ብለዋል።

የአዲስ አበባ ነዋሪ ወይዘሮ ሰብለ ከበደ በበኩላቸው፣ የመከላከያ ሠራዊት ላይ በአሸባሪው ሕወሓት የደረሰውን ጥቃት በመገናኛ ብዙኃን ሲሰሙ እጅግ ማዘናቸውን በመግለጽ፤ ድርጊቱ ሊወገዝ የሚገባው እና ታሪክ ይቅር የማይለው ነው ሲሉ ገልጸዋል።

በሰሜን እዝ ላይ የተፈጸመውን ድርጊት ከአገር ውስጥ የሚመነጭ ሳይሆን የውጭ ተጽእኖ እንደሚሆን ግምታቸውን በመጥቀስ፤ የዚህ ዓይነቱን ተጽእኖ ለማቆም አንዱና ዋነኛው ከድህነት መውጣት እና የራሳችንን ባህልና መልካም የግብረገብነት ልምዶችን በመጪው ትውልድ ላይ መስራት እንደሚገባም አመላክተዋል።

ወይዘሮ ስንዱ ያለው በበኩላቸው በሰጡት አስተያየት የመከላከያ ሠራዊቱ ላይ በሽብር ቡድኑ የተሰነዘረበት ትቃት ወደኋላ መልሰው ሲያስቡት ሰብዓዊነት የሚሰማው ቡድንም ሆነ ሰው የሚያደርገው እንደማይሆን በመጥቀስ የሽብር ቡድኑ ድጊት በዘመናት እንዳይደገም ማድረግ እንደሚገባ ጠቁመዋል።

መከላከያ ሕይወቱን አሳልፎ እስከመስጠት ትልቁን ውለታ የዋለና አሁን ላይ ለመድረስ መሰረት መሆኑን አስታውሰው፤ ለቀጣዩ ትውልድም ኢትዮጵያዊ ማንነታችን በማስገንዘብና ጠንካራ አገራዊ አንድነቱን ለማስጠበቅ ከቤት እና ከትምህርት ቤት ጀምሮ በአገር ፍቅር ግንዛቤ ላይ መስራት እንደሚገባ ጠቁመዋል።

# «የትግራይ ሕዝብ ወደፊት ለሰሜን እዝ በቦታው ላይ የመታሰቢያ ሐውልት ያቆምለታል የሚል እምነት አለኝ»

**- ብርጋዴር ጄኔራል ዋሲሁን ንጋቱ**
**የቀድሞ ጦር ሠራዊት አባል**

**ፋንታነሽ ክንዴ**

አዲስ አበባ፡- የሀገር መከላከያ ሠራዊት ሕዝባዊ ውግንናው ከፍ ያለ በመሆኑ የተጣለበትን የአገር ዳር ድንበር ከማስጠበቅ ባለፈ በሰላም ወቅት ከሕዝቡ ጎን በመሰለፍ የልማት ሥራዎችን የሚሰራ ሃይል መሆኑን የቀድሞው የኢትዮጵያ ሠራዊት የጦር ጄኔራል ብርጋዴር ጄኔራል ዋሲሁን ንጋቱ ገለጹ። እዙ በአካባቢው በቆየባቸው ጊዜያት ሁሉ ከሕዝቡ ጋር ከነበረው መልካም ግንኙነት እና ቁርኝት አንጻር የደረሰበት ግፍ ከባድ በመሆኑ የትግራይ ሕዝብ ለወደፊት ሃውልት ያቆምለታል የሚል እምነት አለኝ ብለዋል።

ብርጋዴል ጄኔራል ዋሲሁን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ ጥቅምት 24 ቀን 2013 ዓ.ም ሰሜን ዕዝ ላይ በአሸባሪው ትህነግ ጥቃት በደረሰበት ዕለትም ወታደሩ ሰብል በመሰብሰብና አንበጣ በማባረረር የሕዝብ አለኝታነቱን ሲያሳይ ነበር ብለዋል።

በዚህ መልኩ አሸባሪው ሕወሓት ከሕዝብ ጋር ጥብቅ ቁርኝት ያለው ሠራዊት ላይ የፈፀመው ዘግናኝ ጥቃት የቡድኑን አረመኔያዊነት ጥግ የሚያሳይ መሆኑን ጠቁመዋል።

ብርጋዴር ጄኔራል ዋሲሁን ንጋቱ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ አሸባሪው የሕወሓት ቡድን ሰሜን ዕዝ ላይ ክህደት በመፈጸም ኢትዮጵያን አደጋ ላይ ለመጣልና እኩይ ፖለቲካዊ ፍላጎቱን ለማሳካት ጥረት አድርጓል። ቡድኑ በሰሜን እዝ ላይ የፈጸመው ጥቃት እጅግ የሚያሳዝንና የቡድኑን አረመኔት ያሳየ ነው።

የኢትዮጵያ ሠራዊት ሕዝባዊ ውግንናው ከፍ ያለ ነው ያሉት ብርጋዴር ጄኔራል ዋሲሁን፤ በዚህም የተጣለበትን የአገር ዳር ድንበር ከማስጠበቅ ባለፈ በሰላም ወቅት ከሕዝቡ ጎን በመሰለፍ የልማት ሥራዎችን ይሠራል። ሰሜን ዕዝ ላይ ይህ ጥቃት በደረሰበት ዕለትም ወታደሩ ሰብል በመሰብሰብና አንበጣ በማባረረር የሕዝብ አለኝታነቱን ሲያሳይ ነበር ብለዋል።

ሠራዊቱ በትግራይ ክልል በቆየባቸው ዓመታት ትምህርት ቤቶችን በመሥራትና በሌሎችም የልማት ሥራዎች ሕዝቡን ሲያገለግል እንደነበር ጠቅሰው፤ የተፈፀመበት ክህደት የሠራዊቱን ድካም ከግምት ያላስገባና እጅግ አሳዛኝ መሆኑን ተናግረዋል።

ቡድኑ ይህን አስነዋሪ ድርጊት ይፈፅም እንጂ የትግራይ ሕዝብ ሠራዊቱ በክልሉ በቆየባቸው ዓመታት ምን አይነት መልካም ሥራዎችን ይሠራ እንደነበር አይዘነጋውም ያሉት ብርጋዴር ጄኔራሉ፤ አርቆ አሳቢ የሆነው የትግራይ ሕዝብ ለወደፊቱ ለሠራዊቱ ጥቃት በተፈጸመበት ቦታ ላይ የመታሰቢያ ሀውልት ያቆምለታል የሚል እምነት እንዳላቸውም ገልጸዋል።


ፎቶ፡- ገባቦ ገብሬ

አንዳንድ የትግራይ ተወላጅ የሆኑ የመከላከያ ሠራዊት አባላት ሠራዊቱ ላይ ጥቃት በማድረስ ትልቅ ሚና እንደነበራቸው አስታውሰው፤ እንኳን አንድ አይነት መለዮ ለብሰው ይቅርና የጠላት ሠራዊት ሲማረክ እንኳን አስፈላጊው ጥበቃ ይደረግለታል። እነዚህ አንዳንድ የሠራዊት አባላት አብሮነትን ለማጽናትና በኢትዮጵያ ስም በጋራ ለመቆም የገቡትን መሃላ አፍርሰው ይህን እኩይ ድርጊት መፈፀማቸው የሠራዊቱን ሥነምግባር የማይመጥን የክህደት ጥግ መሆኑንም አመልክተዋል።

ሠራዊቱ ጥቃቱ በተፈፀመ ማግሥት እንደ አዲስ ተደራጅቶ የአገርን ሕልውና የግዛት አንድነት ለማስጠበቅ ዋጋ እየከፈለ መሆኑን አስታውሰው፤ ይህ እንዲሆን ያስቻለው ሠራዊቱ አንድነቱን አጠናክሮና የገባውን ቃል አክብሮ ኢትዮጵያን ለመጠበቅ በሠራው ሥራ የተገኘ ነው ብለዋል።

ይህ ውጤት እንዲገኝ የሕዝቡ የኋላ ደጀንነት የማይተካ ሚና እንዳለው አስታውሰው፤ በቀጣይነትም ሕዝቡና ሠራዊቱ እንደ ከዚህ ቀደሙ እጅና ጓንት ሆነው በመሥራት የኢትዮጵያ ሉዓላዊነትና የግዛት አንድነት ለማስከበር መትጋት እንዳለባቸው ጠቁመዋል።

ሰሜን ዕዝ ላይ የተፈፀመው ጥቃት በልኩ እንዲዘከር በማድረግ አዲሱ ትውልድ ከዚህ እኩይ ተግባር መማር እንዲችል መደረግ እንዳለበት የገለጹት የጦር ጄኔራሉ፤ መንግሥት ለዕለቱ ትኩረት ሰጥቶ ጥቃቱ የተፈፀመበት ዕለት መታሰቢያ መደረጉ ጥሩ ጅምር መሆኑንና ተጠናክሮ ሊቀጥል እንደሚገባውም አስረድተዋል።

# የታጋቾቹ ጄኔራሎች ትውስታ

**ጌትነት ተስፋማርያም**

አሸባሪው ሕወሓት ሰሜን ዕዝ ላይ ጥቅምት 24 ጥቃት ከከፈተ በኋላ ብርጋዴር ጄኔራል ኑሩ ሙዘይንና ሜጀር ጄኔራል አዳምነህ መንግስቴ ታግተው ከነበሩ አንድ ሺህ በላይ የመከላከያ ሠራዊት መኮንኖች መካከል ነበሩ።

ከእገታው ድራማ በኋላ ሁለቱ አመራሮች ሃሳባቸውን በወቅቱ አካፍለዋል። ብርጋዴር ጄኔራል ኑሩ በወቅቱ የጁንታው ታጣቂዎች የሠራዊቱ አባላት ትጥቃቸውን እንዲፈቱ መልዕክት በግዳጅ እንዲያስተላልፉ ታዘው እንደነበር ያስታውሳሉ።

እርሳቸውም “እኔ ትጥቄን ፈትቻለሁ እናንተም ፍቱ፤ እኔን ግን ከዚህ በኋላ አታገኙኝም” በሚል ጥንቃቄ እንዲያደርጉ የሚገልጽ ውስጠ ወይራ መልዕክት በስራቸው ለሚገኙ የሠራዊቱ አባላት አስተላለፉ። አክለውም በኦሮምኛ ቋንቋ ለሠራዊቱ ትጥቅ እንዳይፈታ የሚያግዝ መልዕክት ማስተላለፋቸውን ያስታውሳሉ።

ከታጋቾች መካከል አንዱ የነበሩት ብርጋዴር ጄኔራል ኑሩ ነጻ ከወጡ በኋላ ሲቃ በተሞላበት ንግግራቸው በወቅቱ ሁኔታውን እንዲህ ሲሉ አስረድተዋል። “ከሁሉ በፊት ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ለመከላከያ ሠራዊትም እንኳን ለዚህ ድል አበቃን ፤ እኛንም ከአንድ ወር ልፋትና እንግልት በኋላ እንኳን በሰላም አገናኘን።

ጓደኞቻችን ህዳር 30 ቀን 2013 ዓ.ም ላይ ኦፐሬሽናቸውን በብቃት በመፈጸም ነጻ አውጥተውናል። ለአንድ ወር ከስድስት ቀን ታግተው በረሃብና በእንግልት የቆዩት የመከላከያ ሠራዊት መኮንኖችን ነፃ ለማድረግ ለተደረገው ጥንቃቄ የተሞላበት ጥረት በወቅት ምስጋና አቅርበዋል።


**ብርጋዴር ጄኔራል ኑሩ ሙዘይን**


**ሜጄር ጄኔራል አዳምነህ መንግስቴ**

በርካታ ቀናትን ያለምግብና ውሃ በተለያየ መልከአምድር ላይ ተንገላተናል። በርካታ የሠራዊት አባላትም ይህን እንግልት ተቋቁመን አሁን የደረስንበት ደረጃ በመድረሳችን በታጋቾችና በእራሴ ስም ለመከላከያ ሠራዊት ሆነ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ምስጋና ማቅረብ እፈልጋለሁ።

በአጠቃላይ በሠራዊታችንም ሆነ በህዝባችን ሲከናወን የነበረውን ነገር በተለያየ መንገድ የሰማነው ስለሆነ እኛም ደስ ብሎናል። ለመከላከያ ሠራዊትም ሆነ ለኢትዮጵያ ህዝብ ለድል ያበቃችሁን አንድነታችሁን በማጠናከር የቀሩትን ስራዎችም እንድታጠናቅቁ አደራ ማለት እፈልጋለሁ”

ከታጋቾች መካከል የነበሩት ሌላኛው የመከላከያ ከፍተኛ አመራር ሜጀር ጀኔራል አዳምነህ መንግስቴ ናቸው። በወቅቱ የነበረውን ሁኔታ ሲያስረዱ “ሠራዊቱ ላይ ጥቃት ለመፈጸም ሲነሱ በእኔ አመራር በምሰጥበት ግቢ ነው ተኩስ የከፈቱት” ብለዋል።

የሕወሓት ሰዎች ከምሽቱ አምስት ሰዓት ከሩብ ላይ ሰሜን ዕዝ ግቢ የጀመሩት ጥቃት በሁሉም ግንባሮች ቀጠሉ። ከሠራዊቱ ጋር የነበሩ የእነሱ ሰዎች የመሳሪያ ካዝናዎችን፣ የተለያዩ ግብዓቶችን እየዘረፉ መውሰድ ጀመሩ። ዋና ዋና ቦታውን ይዘው ስለነበር ከፍተኛ የክህደት ጥቃት ነው የፈጸሙት ሲሉ አስረድተዋል።

ታሪኩን ሲያስታውሱም “በኋላ የቀረነው የሠራዊት አባላት እየተታኮስን ቆየን፤ ከቀናት በኋላ ግን አፍነው ወሰዱኝ። እኔና ሌሎች አመራርና አባላት ከታፈንን በኋላ በአስቸጋሪ መልከዓምድሮች በእግር ጉዞ እንድናደርግ ስንገደድ ነበር።

በአንድ ስፍራ አስቀምጠው በምግብ እጦት እንድንሰቃይ ሲያደርጉን ነበር። በኋላም የመከላከያ ጥቃት ሲበረታባቸው ከአቢይ አዲ ወደ ጉያ ከጉያ ወደተከዜ እየተመላለስን በረሃውን በስቃይ አሳለፍን።

ቁስለኞችና ታማሚዎች ጭምር ነበሩ፤ እናም ወደወርሂ ወንዝ አካባቢ ወሰዱን። ከዚያም አዴት ሄድን፤ የወገን ጦር ይበልጥ እየተጋና የጥንቃቄ እርምጃውን ሲያጠናክር ከህዳር 25 እስከ 30 ቀን 2013 ዓ.ም ያለእረፍት ቀንም ሌትም አጓጓዙን።

በኋላ አዴት ላይ የጁንታው አመራሮች ታጋቾችን መሃል ላይ አድርገውን እራሳቸውን ለመከላከል ሲሞክሩ መከላከያ ሠራዊቱ ጥንቃቄ በተሞላበት አካሄድ ከፊትና ከኋላ ጭምር እርምጃ ሲያካሂድ ተደናገጡ። ሰው አልባ አውሮፕላን ጥቃቱን ጭምር በተሳተፈበት ኦፐሬሽን እኛን ማስለቀቅ ተቻለ። የጁንታው ታጣቂዎች እግሬ አውጪኝ ብለው በየቦታው ፈረጠጡ” ሲሉ ተናግረዋል።

መንግሥት የፈጀውን ጊዜ ፈጅቶ ሕይወታችን ለማትረፍ የወሰደው ጥንቃቄ የተሞላበት እርምጃ የሚያስመሰግን ነው ያሉት የመከላከያው አመራር፤ ቀን ሲለፋ የልማት ስራ ሲያግዝ የቆየው ሠራዊት ጥቅምት 24 ቀን የተፈጸመበት ክህደት ግን መቼም የማይረሳ ነው ሲሉ ሃሳባቸውን አካፍለዋል።

# ጥቅምት 24 ሲታሰብ የአሸናፊና የተሸናፊ ትርክት ለመፍጠር ሳይሆን ተመሳሳይ ታሪክ እንዳይደገም ለማድረግ ነው

- **በሠራዊቱ ላይ ክህደት የተፈጸመበት 2ኛ ዓመት ዛሬ ታስቦ ይውላል**

**ሞገስ ጸጋዬ**

አዲስ አበባ፡- ጥቅምት 24 ሲታሰብ የአሸናፊና የተሸናፊ ትርክት ለመፍጠር ወይም ቂምና ጥላቻ እንዲነግስ ለማድረግ ሳይሆን ተመሳሳይ ታሪክ እንዳይደገምና ትውልድ እንዲማርበት ለማድረግ መሆኑን የመከላከያ ሚኒስቴር አስታወቀ። መከላከያ ሠራዊቱ ላይ ክህደት የተፈፀመበት 2ኛ ዓመት ዛሬ ታስቦ ይውላል።

ጥቅምት 24 2013 ዓ.ም የሰሜን ዕዝ የተጠቃበት 2ኛ ዓመት መታሰቢያ አስመልክቶ የመከላከያ ሚኒስቴር የሕዝብ ግንኙነት ዳይሬክተር ኮሎኔል ጌትነት አዳነ በትናንትናው ዕለት ለጋዜጠኞች እንዳስታወቁት፤ የአሸባሪው ሕወሓት ቡድን የሰሜን ዕዝን ያጠቃበት 2ኛ ዓመት መታሰቢያ በተለያዩ ዝግጅቶች ታስቦ ይውላል። እንዲሁም በመከላከያ ጠቅላይ መምሪያ ደረጃን ጨምሮ በውጭና በአገር ውስጥ ያሉ የሠራዊቱ ክፍሎች፣ አመራሮች፣ አባላትና ሲቪል ሰራተኞች አክብረውት እንደሚውሉ ገልጸዋል።

ኮሎኔል አዳነ በመግለጫቸው እንዳስታወቁት፤ ጥቅምት 24 ቀን 2013 ዓ.ም ስናስብ የአሸናፊና የተሸናፊ ትርክት ለመፍጠር ወይም ቂምና ጥላቻ እንዲነግስ ለማድረግ ሳይሆን ተመሳሳይ ታሪክ እንዳይደገም፤ ትውልድ እንዲማርበት ለማድረግ ነው።

እለቱ ለአገራችን ቀርቶ ለዓለም እንግዳ ኢ-ተገማች በሆነ መልኩ አሸባሪው ሕወሓት የሠራዊት አባላት ላይ ጭፍጨፋ የፈጸመበት ዕለት በመሆኑ የተለያዩ የሕብረተሰብ ክፍሎችም አክብረውት ይውላሉ ብለዋል።

ሠራዊቱ ትግራይ ክልልን ጨምሮ በበቆየባቸው ሁሉም አካባቢዎች በፍጹም ወታደራዊ ሥነ ምግባርና ሕዝብ አክባሪነት ተልዕኮውን ሲወጣ መቆየቱን ያስታወሱት ኮሎኔል ጌትነት፤ በእለቱም ሕዝባዊ ስራ ሲሰራ ውሎ ምሽቱን መከዳቱን አስታውሰዋል።

በመለዮው ጥላ ስር ከፉና ደጉን አብረው ያሳለፉና ወገኔ ጓዴ ብሎ ባመናቸው የቅርብ አባላት መከዳቱን ስናስበው ለማመን የሚከብድና ከአዕምሮ በላይ የሆነ ጭካኔ ነው ብለዋል።

በሠራዊቱ አባላት ላይ የደረሰው ጥቃት ኢትዮጵያውያንን የማይመጥን መጥፎ የታሪካችን ጠባሳ ነው ያሉት ኮሎኔል ጌትነት፤ ዕለቱን ስናስብ ከመሰል ጥፋቶችን ላለመላመድና ላለመድገም በማሰብ መሆን እንዳለበትም ጠቁመዋል።

ኮሎኔል ጌትነት እንዳሉት፤ እንዲህ አይነት ጥፋት በራሱ አጥፊዎችን የሚያጠፋ እንደሆነ የምንማርበት አጋጣሚ አድርጎ ማሰብ ይገባል። በሌላ በኩል ጥቅምት 24 ቀን ሠራዊቱ ሊገድሉት ያሰቡትን ጥሶ ታሪክ የሰራበት ከችግር ወደ ድል መሸጋገር እንደሚችል ያሳየበት ዕለት ነው። በሠራዊቱ ላይ በመሳለቅ ከማን ጋር እንደራደራለን ሲሉ የነበሩ እብሪተኛ ጠላቶች ብረት የሚያቀልጥ የሠራዊቱን እጆች ቀምሰው ራሳቸው እጅ የሰጡበትም ነው።

ሠራዊቱ የተከዳበት ጥቅምት 24 2013 ዓ.ም 2ኛ ዓመት መታሰቢያ በዛሬው ዕለት በመከላከያ ጠቅላይ መምሪያ በኩልና ሠራዊቱ ባለበት ቦታ ሁሉ ታስቦ ይውላል። ሠራዊቱ ጥቃት ከደረሰበት ቀን አንስቶ በአገር ውስጥና በውጭ አገር ሁነው ድጋፍ ላደረጉ አካላትም ኮሎኔል አዳነ ምስጋናቸውን አቅርበዋል።

# «የውጭ ሃይሎች ተጽእኖ በኢትዮጵያ ተሳላኪ መንግሥት በማስቀመጥ እንደፈለጉ ለማሽከርከር ነው»

**- ብርጋዴል ጀነራል አሰፋ አህፈርያም**
**የቀድሞ የጦር ሠራዊት አባል**

**ዘላለም ግዛው**

አዲስ አበባ፡- አንዳንድ ምዕራባውያን እና አጋሮቻቸው በኢትዮጵያ ላይ ጫና የሚያደርጉትና አሸባሪውን ትህነግ የሚደግፉት በኢትዮጵያ ተላላኪ መንግሥት በመሾም እንደፈለጉ ለማሽከርከር ካላቸው ጽኑ ፍላጎት መሆኑን የቀድሞ የጦር ሠራዊት አባል ብርጋዴል ጀነራል አሰፋ አህፈርያም ገለጹ።

ብርጋዴል ጀነራል አሰፋ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በደቡብ አፍሪካው የሰላም ውይይትም ሆነ በተለያዩ ሁኔታዎች አንዳንድ ምዕራባውያን እና ወዳጆቻቸው ሚዛኑን በሳተ መልኩ ለአሸባሪው ትህነግ ድጋፍ የሚሰጡበት ሁኔታ ኢ-ፍትሃዊ አካሄድ ነው።

እነዚህ ሀገራት ቀደም ሲልም ቡድኑ የሳተላይት መረጃ እንዲያገኝ በማድረግ ድጋፍ ሲያደርጉለት ነበር ያሉት ብርጋዴል ጄኔራል አሰፋ፤ አሁንም በይፋ በተለያዩ የፕሮፓጋዳና ሌሎች መንገዶች ድጋፋቸውን ቀጥለውበታል ብለዋል።

በትጥቅ ትግል ጊዜ ለትህነግ ድጋፍ ያደረጉት አዲስ አበባ ሲገባም ይዘውት የገቡት እነዚህ አካላት ናቸው። ኢትዮጵያን የወደዱት አሸባሪ ቡድኑን ይዘው ነው። ይህ ድርጊታቸው አሻባሪው ትህነግ ተላላኪያቸው መሆኑን በግልጽ ያሳያል። አሁን ተላላኪያቸውን ቢደግፉ አያስደንቅም ብለዋል።

ቡድኑ በመሳሪያ ሃይል ይገዛ የነበረ፣ በጠባብ አመለካከት የአንድ ቡድን ሃያልነት ያሰፈነ፣ ኢኮኖሚውን የተቆጣጠረና ፖለቲካውን በተወሰኑ ሰዎች የበላይነት ብቻ እንዲዘወር ያደረገ እንደነበርም አስታውሰዋል።

ለይስሙላ ራሱ የደነገገውን የብሄር ብሄረሰብ እኩልነት ራሱ የመረጣቸው እና እንደፈለገ ሊመራቸው የሚችላቸውን እንደፓርቲ አቋቁሞ ኢህአዴግ በሚል ስያሜ ትህነግ ግንባር ቀደም ሆኖ የተወሰኑትን ይዞ ኢትዮጵያን ሲገዛ መቆየቱንም ጠቁመዋል።

የትግራይ ሕዝብ የአሸባሪ ቡድኑ ተጽዕኖ በከፍተኛ ደረጃ አርፎበታል። የውጭ ሃይሎች ቡድኑን በግልጽ እንደምትደግፍ እየታየ መጥቷል። አሁን በኢትዮጵያ ላይ የሚያደርጉት ተጽዕኖ ምክንያቱ ግልጽ አይደለም። በጣም አወዛጋቢ ነው ብለዋል።

በጸጥታው ምክር ቤት በተደጋጋሚ የሚንጸባረቀውም ሚዛኑን የሳተ ነው ያሉት ብርጋዴል ጀነራል አሰፋ፤ ምክር ቤቱ ከፍተኛ ተጽእኖ የሚያደርግበት እና የሚያካሄድበት ጉዳይ ኢትዮጵያን የሚመለከት አይደለም። ሕዝብን እርስ በእርስ ማጋጨትን ለምን እንደወደዱትም አይገባኝም ነው ያሉት።

የሽብር ቡድኑ በሥልጣን ላይም ሆኖ ብዙ ግፍ ፈጽሟል። ከሥልጣን ከተባረረ በኋላ ደግሞ በአፋርና በአማራ ክልል በሰብአዊ ቀውስና በንብረት ላይ ከፍተኛ ውድመት በማድረስ ክፉነቱን አስመስክሯል። ለትግራይ ሕዝብም ደንታ እንደሌለው በግልጽ አሳይቷል።

አንዳንድ ምዕራባውያን ከዚህ በፊት ታላቋ ኢትዮጵያን የማይደግፉበት ምክንያት የርዕዮት ዓለም ልዩነት በመኖሩ ነበር ብለን እንወስድ ነበር። በአንድ በኩል የኮሚኒዝም በሌላ በኩል ደግሞ የኢምፔሪያሊዝም ሁኔታ እና የምስራቅ እና የምዕራብ ዓለም በሚል የተከፈለ የሃይል ጉዳይ ነበር፤ አሁን ተጽእኖ ለመፍጠር እያደረጉት ያለው ነገር ግን ከምን የመነጨ እንደሆነ ግልጽ አይደለም፣ የአገራቱን ታሪካዊና የቆየ ግንኙነት ግምት ውስጥ በማስገባት ሊስተካከል ይገባል ብለዋል።

# የሰላም ስምምነቱ...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

መልኩ በተሳካ ሁኔታ ተጠናቋል።

ስምምነቱ መንግሥት ካስቀመጠው አቅጣጫ ጋር የተጣጣመ፣ የመላ ሕዝባችንን ፍላጎት የሚያሟላ፣ ዘላቂ ሰላምን የሚያረጋግጥና የትግራይን ሕዝብ መሠረታዊ ችግሮች የሚፈታ ነው። ወደዚህ ድል የደረስነው መላው የጸጥታና የደህንነት ሃይሎቻችን በከፈሉት መስዋእትነትና መሬት ላይ ባስመዘገቡት ድል ነው ያሉት ሚኒስትሩ፤ ሕዝባችን አንድ ሆኖ በመቆሙና መንግሥት ሰላምን ለማረጋገጥ ባሳየው ቁርጠኝነት እንደሆነም አንስተዋል። ድሉ የመላ ኢትዮጵያውያን ድል መሆኑን የገለጹት ሚኒስትሩ፤ በዚህ የሰላም ስምምነት የአሸነፈችው ኢትዮጵያ ናትም ብለዋል።

ስምምነቱን በተመለከተ መንግሥት ባወጣው መግለጫ፤ ስምምነቱ ሁለት ዓመት የዘለቀውን ጦርነት የሚያስቀር፣ በኢትዮጵያ ሊኖር የሚገባው አንድ የመከላከያ ሠራዊት ብቻ መሆኑን የሚያጸና ነው ብሏል።

እነዚህንና ሌሎች በስምምነቱ የተጠቀሱ ሌሎች መርሆች ተግባራዊ ለማድረግም ሕወሓት ትጥቅ ሊፈታ፣ ታጣቂዎቹም ወደ ተሃድሶ እንዲገቡ ስምምነት ተደርሷል።

መንግሥት በግጭቱ የተጎዱ የሕብረተሰብ ክፍሎችን መልሶ ለማቋቋም በፍጥነት ወደተግባር እንደሚገባና ከዓለም አቀፍ አጋሮች ጋር እንደሚሰራ ተገልጿል።

# ባጎረሰ የተነከሰው...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

መሆኗ ይቀራል።

ውትድርና ወደ ጥቁር ሕዝቦች የነጻነት ተምሳሌቷ፣ ተነግሮ የማያልቅ ገድል ሀብታሟ በሰው ዘር መገኛነቷ በዓለም ሕዝብ ዘንድ ስሟ ለናኘው ኢትዮጵያ ሲመጣ ደግሞ ሌላ አይነት አንድምታ አለው።

ለኢትዮጵያዊው ወታደር ሀገሩ በኩርፊያ መሀል የማትኮረፍ፣ ነገሥታት ቢለዋወጡ ካለችበት ከፍታ የማትናወጽ፣ ከፍጥረት ሁሉ ሊሞትላት የተገባ በነፍሱ ቃል የገባላት በደም ማህተም ፍቅሯን ያተመላት ናት። ኢትዮጵያ የእኛ መመኪያ እያለ ፍቅሩም ህልሙም ቅዠት ምኞቱ መሽቶ በመንጋት ሂደት ውስጥ የነገሩ ሁሉ ፍፃሜ ሀገሩ ናት።

ወታደር ለሷ ሲል ርስት ጉልቱን ሳይል ለተሰደደላት ሀገሩ ያለውን ፍቅር በምንም ለመግለፅ ቃላት ሰነፍ ናቸው። ክቡር ዶክተር አርቲስት ጥላሁን ገሰሰ አይኑ በእንባ ማዕበል ተሞልቶ ብሔራዊ መዝሙር የሚመስለው ኢትዮጵያ የሚለውን ዘፈኑን ሲዘፍን፣ እነ ሻለቃ አትሌት ሃይሌ ገብረስላሴና ሌሎች አትሌቶቻችንን በዓለም አደባባይ ፊት በድል ዋዜማቸው ላይ ሰንደቋን በማየት ብቻ እንባቸውን መቆጣጠር ሲያቅታቸው ያለው ስሜት ወታደር ለሀገሩ ከሚሰማው እጅግ ትንሹን ያሳያል።

የዛሬ ሁለት ዓመት ጥቅምት 24 ልክ በዛሬው ቀን ግን በዚህ ለሀገሬ እንጂ ለኔ በማይለው ምስኪን ወታደር ላይ ብዙዎች ሰምተው በማያውቁት መንገድ ግፍ ተፈጸመ። ጠላት እንኳን የማይፈጽመው ወንጀል ወዳጅ በጠባቂው ላይ ፈጸመ። ይህ ቀን በታሪክ መዝገብ ላይ በቀይ መስመር ተከተበ። በጥቁሯ ቀን ጠላትን ለመከላከል የቆመው ሠራዊት ወዳጄ ባላቸው የሀገሩ ልጆች ተከዳ።

የክህደት ጥሩ ባይኖርም በሚጠብቁት ጠላት ሲሆን ቀላል ነው፤ ጠሩ የተከዳው ግን እንደ መልካም እረኛ ሲጠብቀው ሲያበላው ሲያጠጣው በኖረው በግ ነው። መከላከያ ሠራዊት ከሀገር ተለይቶ አይታይም፤ ሠራዊቱ የሀገር ትንሿ ስዕል ነው። የአንድን ሉዓላዊት ሀገርን ዳር ድንበር የሚጠብቅን ኃይል መንካት ማለት ትልቋን ሀገር መድፈር ነው።

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅትም የክህደቱ ገፈት ቀማሽ ከሆኑ አባላት መካከል የታጋቹ ማስታወሻ በሰሜን ዕዝ ላይ የተሰኘ መጽሃፍ ለአንባቢያን እያደረሱ ያሉትንና ሕወሓት በሰሜን እዝ ላይ ጥቃት ሲፈጽም በቦታው የነበሩትን የሻንበል አክሊሉ ሃይሉ ጥላሁንን ምስክርነት ተቀብሏል።

ሻምበል አክሊሉ ሃይሉ ይባላሉ። ስራቸውን በኢትዮ ኤርትራ ጦርነት ላይ በመጀመር ሀገራቸውን ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይሉ ላለፉት 24 ዓመታት በውትድርና አገልግለዋል። ከዚህ የውትድርና ልምዳቸው ውስጥ 14 ያህል ዓመቱን በትግራይ ውስጥ ነበር ያሳለፉት።

የመጀመርያ ዲግሪያቸውንም እዛው መከላከያ ውስጥ ነው የተማሩት፤ በዚሁ በውትድርና ስራ ውስጥ አግብተው ሁለት ወልደዋል። ስፍራው ብዙ መከራን እና እልፍ ደስታንም ያሳያቸው ነበር። ማስታወስ በሚከብደው ጥቅምት 24 የተሰራውን የግፍ ትውስታ በኀዘን ተሞልተው አጋሩን። በዚህ ቀን በኢፌዴሪ የመከላከያ ሠራዊት ውስጥ የነበሩ የትግራይ ክልል ተወላጆች መከላከያውን በመካድ አሳልፈው ለሽብር ቡድኑ ሰጡ ይላሉ ሻምበል አክሊሉ በንግግራቸው።

ሠራዊቱ ቀኑን አንበጣ በማባረር፣ ሰብል መሰብሰብና ሌሎችም ክልሉን በሚጠቅሙ ተግባራት ላይ ነበር ተሰማርቶ የዋለው። የምስጋና መርሀግብር ተከውኖ ሁሉም ወደ ማደርያው ሄደ፤ ምንም አይነት ነገር ይኖራል ብሎ ያልጠረጠረው ሠራዊት ከሌሊቱ አምስት ሰአት ላይ በሁሉም በሰሜን እዝ ላይ ባሉ ካምፖች አቅጣጫ የተኩስ እሩምታ ተሰማ።

እልፎች ሞቱ፣ ብዙዎች ቆሰሉ፣ አብዛኛው መሳሪያውን ተቀማ፣ በቅርብ ርቀት መቀሌ ላይ ልምምዶች ስለሚደረጉ ምንም አይነት ጥርጣሬ ያልነበረው ሠራዊቱ ስልጠና ነው ብሎ ተዘናግቶ ነበር።

ጠዋት ወደተለመደው ስራ ለመሄድ ሲነሳሱ ማንም ከግቢው እንዳይንቀሳቀስ ተባለ። ማንኛውም አይነት ትራንስፖርት እንዳይጠቀሙ ተነገረ። ከመቀሌ አንስተው ወደ ተንቤን የወሰዱበት መንገድ በጣም አሰቃቂና አጸያፊ ነበር፤ ምግብና ውሃ የሌለበት፣ ብዙዎች በጉዞው የሞቱበት እጅግ አታካችም ጭምር ነበር።

የመጀመሪያው የጦርነቱ ምክንያትም የታገቱ የመከላከያ ሠራዊት አባላትን ለማስፈታት ሲባል የተደረገ እንደሆነ ሻምበል አክሊሉ ነግረውናል። ከታገቱት መሀል በመኮንን ደረጃ ከምክትል መቶ አለቃ እስከ ጄነራሎች ከአንድ ሺህ ሶስት መቶ በላይ እንዲሁም ባለ ሌላ ማዕረጎች ደግሞ ከአስር ሺህ በላይ ወታደሮች ታግተው ነበር። ዘግናኙ ጭፍጨፋ ግን በሲቪል ሰራተኞች ላይ የደረሰው ነበር።

"እኔ ለትግራይ ብዙ ውለታ ውያለሁ፤ ካለችኝ ትንሽ ደመወዝ ላይ ትምህርት ቤት እንዲገነባ በማድረግ ተማሪዎችን አስጠና ነበር፣ ችግረኞችን ለመርዳት በፌዴራል ደረጃ ከሚዋጣው በተጨማሪ በልዩ ሁኔታ መዋጮ ይደረግ ነበር" ብለው በኀዘን በመሞላት ነበር ያችን ቀን ያስታወሱት። ለዚያ ሁሉ ዓመታት ለበለጠው ውለታቸው ግን ምላሹ በሽብር ቡድኑ የተፃፈላቸው የሞት ድግስ ነበር።

ከጥቅምት 25 ጀምሮ ከዚህ በኋላ ታጋች ናችሁ ብለው የተለያዩ የጦር መሳሪያዎች እንዳይነኳቸው ወታደሩን እንደ ምሽግ በማድረግ እነሱ በመሀል በመኪና እየሄዱ ነበር።

የአካባቢው ሕዝብ የሚበላና የሚጠጣ ሊሰጣቸው ሲል የአሸባሪ ቡድኑ ሲከለክልና በርሀብና ጥም በመቅጣት ሲጎዳን ነበር ብለዋል። ከጥቅምት 24 በፊት ጀምሮ ትልቅ ዝግጅት ሲያደርጉ እንደነበርም በማስታወስ እለቱ የጭካኔ ጥግ የታየበት እንደሆነ በኀዘን ድባብ በዋጠው ስሜት ገልጸውልናል።

# ርዕሰ አንቀፅ

ልዩ ዕትም

ጥቅምት 24 መቼም አንረሳውም



## ጥቅምት ሃያ አራትን መቼም ቢሆን አንረሳውም!

ጥቅምት 24 ቀን 2013 ዓ.ም አሸባሪው ትህነግ በሰሜን እዝ ላይ የሰነዘረው ጭካኔ የተሞላበት የክህደት/የባንዳነት ጥቃት በሀገሪቱ ታሪክ ውስጥ ታይቶ የማይታወቅ ፤ ሀገሪቱን ከመኖር መደ አለመኖር ታሪክነት በመለወጥ፣ የጠላቶቻችንን የዘመናት ህልም እውን ለማድረግ የታቀደበት፤ ኢትዮጵያ ከጀርባዋ የተወጋችበት የከፋ ተግባር ማሳያ ነው።

ሃገራችን ኢትዮጵያ እንደ ሀገር በብዙ አስቸጋሪ የታሪክ ምዕራፎች ውስጥ ያለፈች ፤ በዜጎቿ የመስዋእትነት ተጋድሎ ሕልውናዋን አስጠብቃ መቆየት የቻለች ታላቅ ሀገር ነች። ዜጎቿ ለሀገራቸው ያላቸው ወደር የለሽ ፍቅር፤ ከዚህ የሚመነጨው አትንኩኝ ባይነታቸው የአሸናፊነት ምልክት ሆኗት ዘመናትን ተሻግራለች።

ኢትዮጵያውያን በየዘመኑ በአንድ በኩል ባህር ተሻግረው ፣ ድንበር ገፍተው ከሚመጡ ባዕዳን ጠላቶች ጋር ፤ በሌላ በኩል ለነሱ መንገድ ጠራጊ ሆነው ሰልፍ ከሚያሳምሩ የናት ጡት ነካሽ /ባንዳዎች ጋር እልህ አስጨራሽ መራራ ትግሎችን አካሂደዋል። ትግሉ የሚጠይቀውን መስዋእትነት በመክፈልም እንደሀገር መዝለቅ ችለዋል።

በሀገሪቱ የቀደመ ታሪክ ውስጥ ሰፊ ስፍራ የሚይዘው እንዲህ ዓይነቱ ክስተት ዛሬም ለዚህ ትውልድ ተስፋና ራዕይ ተግዳሮት ሆኖ በአሸባሪው ትህነግ ከቆመ ውሎ አድሯል። ቡድኑ ከውልደቱ ጀምሮ በተጠናወተው ሀገር ጠልነቱ እና ከልክ ያለፈ የሥልጣን ጥማቱ ሀገርና ሕዝብን ብዙ ዋጋ አስከፍሏል።

በተለይም በሕዝባዊ እንቢተኝነት ከሥልጣን ከተወገደ ማግስት ጀምሮ መቀሌ በመመሸግ የተጓዘበት የጥፋት መንገድ የሀገሪቱን በህልውና ዘመቻውም ጊዜ በላይ ስጋት ውስጥ ከቶ ነበር። ሕዝባችን እንደቀደመው ዘመን ትግሉ የሚጠይቀውን መስዋእትነት ከፍሎ ስጋቱም መቀልበስ ባይችል ኖሮ ሀገራዊ የታሪክ ትርክቱ ምን ሊመስል እንደሚችል ማሰብ ዛሬም ቢሆን በራሱ አስጨናቂ ነው።

ለአንድ ዓላማ አብሮት የተሰለፈን ፣ ለዓላማው ራሱን ለመስዋእት ያዘጋጀን ወንድም /ጓድ በግፍ በማሰቃየት ፣ በተኛበት ገድሎ ትጥቁን በመዝረፍ የተጀመረው የአሸባሪው ትህነግ የባንዳነት የጥፋት ጉዞ ሀገርን በማፍረስ ፤ሕዝብን በመበተን የማብቃት ዓላማን ያነገበ የታሪካዊ ጠላቶቻችን የዘመናት ምኞት መሆንን ባሰብን ቁጥር፤ ከቡድኑ የከፋት ጥግ በላይ ኢትዮጵያን ጠልነቱን በተጨባጭ ማየት የምንችልበትን ተጨማሪ ዕድል የፈጠረልን ነው።

ቡድኑ ጥቅምት 24 /2013 በሰሜን እዝ ላይ በሰነዘረው ጥቃት ሊያዋርድ የሞከረው የመከላከያ ሠራዊቱን ብቻ ሳይሆን ከሠራዊቱ በስተጀርባ ያለውን መላውን ሕዝባችን ነው። ሠራዊቱ የሚወክለውን ይህን ትውልድ ብቻ ሳይሆን የቀደመውን ትውልድ የተጋድሎና የነጻነት ታሪክ ነው። የከፋት ሙከራው ሀገርና ሕዝብን አንገት በማስደፋት የባንዳነት የአገዛዝ ሥርዓት የመጫን ሙከራ አካልም ነው።

ይህ በቀደመው ታሪካችን ያልታየ በሀገር ግንባታ ታሪክ ውስጥ የጎላ ስፍራ ባለው የትግራይ ሕዝብ ስም እየማለ በሚገዘት አሸባሪ ቡድን ያጋጠመን የህልውና ስጋት ዳግም እንዳይከሰት ቀኑን በየአመቱ አስቦ መዋል ያስፈልጋል። የቡድኑን የባንዳነት ጥግ መጪው ትውልድ እንዲገነዘበው ፤ በሀገሪቱ ቀጣይ ታሪክ እንዲህ አይነት የባንዳነት ታሪክ እንዳይደገም ቀኑን ማሰብ ወሳኝ ነው።

ዛሬም "ጥቅምት 24ን መቼም አንረሳው" በሚል መሪ ቃል ቀኑን የምናስታውሰው ይህን አይነቱን ሀገርን እስከ ማፍረስ ፤ሕዝብን እስከ መበተን ፤ታሪክን እስከ ማርከስ የሚደርስ የባንዳነት ታሪክ እንዳደገም የአሁኑን ጨምሮ ቀጣዩን ትውልድ ለማንቃት ነው። ከዚህም በላይ ለሀገር የሚከፈል የመስዋእትነት ጥግ የቱን ያህል እንደሆነም ለማስተማርና መከላከያ ምንም ያህል ተግዳሮትና ክህደት ቢገጥመውም ጥሶ የመውጣትና የማሸነፍ ደማቅ ታሪክ ያለው መሆኑን ለመዘከርም ጭምር ነው።

በርግጥም በዕለቱ በአሸባሪው ትህነግ በሠራዊቱ አባላት ላይ የተፈጸመው የክህደትና የጭካኔ ተግባር ፤ በሀገራችን የባንዳዎች ጥቁር ገጽ ውስጥ ሰፊ ስፍራ የሚይዝ ፤ ለሀገርና ለሕዝብ ክብር መስዋእት መሆን የማንነት ልእልናቸው ለሆኑ ትውልዶች የልብ ስብራት የሚሆን መቼም ቢሆን ሊረሳ የማይችል ጥቁር ታሪካዊ ክስተት ነው!

---


ኢፕድ

# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ:- 011 126 4240

Email:- wendweson.shimelis@press.et

wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73

ፋክስ - 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ**

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


---

ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው:: በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም::

## የአሸባሪው ትህነግ የባንዳነት ተግባር ‹‹መቼም የትም እንዳይደገም››

**ቦጋለ አበበ**

ጥቅምት 24/2012 ዓ.ም የሰሜን እዝ በከሃዲው የአሸባሪው ትህነግ ቡድን ከጀርባ ከተወጋ ዛሬ ሁለተኛ ዓመቱን ደፍኗል። ኢ- ሰብአዊ ድርጊቱ ከተፈጸመ ከሰባት መቶ ቀናት በላይ ቢቆጠሩም በኢትዮጵያ ላይ ጥሎት ያለፈው ቁስል ዛሬም አልጠገገም። "የወጋ ቢረሳ የተወጋ አይረሳም" ያንን የአውሬዎች አሳፋሪ ተግባር ዛሬም፣ ነገም እስከወዲያኛውም ብንረሳው የጀግኖቹ መስዋእቶች አጥንት እሾህ ሆኖ ሲወጋን ይኖራል።

ኢትዮጵያ ይቅር ባይነች፣ የህዝቦቿም ልብ ቂም አይዝም፣ ይህን የእንቁ ልጆቿን በግፍ የፈሰሰ ደም ግን ኢትዮጵያም ህዝቦቿም ይቅር አይሉትም፣ መቼም አይረሱትም። ይቅር የማይሉት፤ የማይረሱት የልባቸው ስብራት ከፍያለ ከመሆኑም በላይ እንዳይደገም ስለሚፈልጉ ጭምር ነው ።

መከላከያ ሰራዊት አገሬ፣ ወገኔና ዳር ድንበሬን ከውጪ ጠላት ጠብቃለሁ ብሎ ከሃያ ዓመታት በላይ ጨርቄን ማቄን ሳይል በቀበሮ ጉድጓድ ኖሯል። በኖረበት ዓመታትም ከራሱ አስበልጦ ለሕዝብ አለኝታ መሆኑን በተግባር አሳይቷል። የወር ደመወዙን ሙሉ በሙሉ ተቆራጭ አድርጎ ትምህርት ቤቶችን ገንብቷል፣ በህክምና እጦት ለሚንገላታው ወገኑ ጤና ጣቢያዎችን አሰርቷል፣ የአንበጣ መንጋን ገበሬውን ሲያሰቃይ እጁን አጣጥፎ አልተቀመጠም፣ አብሮ አርሷል አብሮ አጭዷል።

ሰብል ሲሰበስብ ውሎ የደከመ ጎኑን ለማሳረፍ በተኛበት ግን የእናት ጡት ነካሾች ጥይት ሲያርከፈክፉበት ያን ሁሉ መስዋእትነቱ ቆመው እንዲያስቡ አላደረጋቸውም። በጥይት መሞት የወታደር ወጉ ነው፣ በዘረኝነት የታወሩና የሰከሩ ባንዳዎች ግን ጥይት አልበቃ ብሏቸው ሰይጣን እንኳን የሚቀናበትን ግፍ መከላከያ ሰራዊቱ ላይ ለመፈጸም አላመነቱም።

አብሮ በልቶ ጠጥቶ፣ ተጋብቶና ተዋልዶ የኖረን ሰራዊት መግደል ብቻ አይደለም ለአስከሬኑ የክብር ረፍት እንኳን ነፍገው በጅብ አስበልተዋል። በጥይት መግደል የዘረኝነት ጥማቸውን አልቆርጥ ብሎ ሰራዊቱ በህይወት እያለ በመኪና ሄደውበታል፣ ልብሱን አስወልቀው እርቃኑን ሰድደውታል። ብቻ ስንቱን ግፍ ዘርዝሮ ይዘለቃል፤ መከላከያ ሰራዊት ላይ የተፈጸመውን ግፍ ኢሰብአዊ ድርጊት ብቻ ብሎ መኮነን የሆነውን ክህደት ማለዘብ ይሆናል።

መንግስት የአሸባሪው ትህነግ የሽብር ቡድን በመከላከያ ሰራዊት ሰሜን እዝ ላይ ጥቃት የፈጸመበት የዛሬዋን ቀን "ጥቅም 24 ን አንረሳውም " በሚል መሪ ቃል ታስቦ እንዲውል ውሳኔ ማስተላለፉ ተገቢ ነው። ቀኑን ትውልድ ሊዘክረውና ሊማርበት ይገባል። ከዚህ ጎን ለጎንም "መቼም የትም እንዳይደገም" በሚለውም ሀሳብ ቢጠናከር ተገቢ ይመስለኛል። ሀሳቡ ለቀይ ሽብር ሰማእታት ብቻ ሳይሆን መከላከያ ላይ ለተፈጸመው ግፍ የበለጠ ይሰራል ባይ ነኝ።

የአሸባሪው ትህነግ የሽብር ቡድን ኢትዮጵያን ለማፍረስ የመጨረሻ ያለውን እርምጃ ጥቅምት 24/2012 ዓ.ም በመከላከያ ሰራዊት ላይ በመፈጸም በኢትዮጵያውያን ላይ ግልጽ ክህደት በመፈጸም ብቻ አላበቃም። ከሰራዊቱ የጦር መሳሪያ በመዝረፍና ከባድ ጥቃት በማድረስ ኢትዮጵያን ያፈራርሳል ያለውን ሁሉ የጥፋት እርምጃ ወስዷል።

በመከላከያ ሰራዊቱ የተወሰደበትን ጥቃት ፈጣን በሆነ አጸፋዊ እርምጃ በመቀልበስ የቡድኑን ሕልውና የሚያሳጥሩ እርምጃዎች ቢወስድም ቡድኑ በምእራባውያን ከመቃብር አፋፍ እየተመለሰ በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ተጨማሪ ሁለት ወረራዎችን ፈጽሟል።

የኢትዮጵያ ሉዓላዊነትን ለመንካት በሽብር ቡድኑ የተወሰደው እርምጃ መቼም የሚረሳ ባለመሆኑ ይህ ቀን በሁሉም ኢትዮጵያውያን ዘንድ ታስቦ ይውላል። "መቼም የትም እንዳይደገምም" ሲታሰብም ይኖራል። መከላከያ ሰራዊታችን ከፍ ተብሎ የሚታሰብበት ቀንም ይሆናል።

ኢትዮጵያውያን ቀኑን " ጥቅምት 24ን አንረሳውም " በሚል መሪ ሃሳብ በሰራዊታችን ላይ የተፈጸመውን ግፍ ሲዘክሩ፤ እኔም እንደ አንድ ኢትዮጵያዊ በማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ መስክ ሰራዊት ነኝ በሚል ቁርጠኝነት ሊሆን ይገባል። ኢትዮጵያውያን በሁሉም ዘርፍ ተደራጅተው አገራቸውን ከአደጋ ለመጠበቅ ከራሳቸው ጋር ቃል እየገቡ መሆን ይኖርበታል።

በመላው አገሪቱ የሚገኙ የመንግስት ተቋማት ያለን ሰራተኞች እና መላው ህዝባችን አንድ ላይ በመሆን ለ45 ሰኮንዶች እጃችንን ደረታችን ላይ አድርገን ቀኑን ስናስብ፤ በእለቱ የደም ልገሳን ጨምሮ የሻማ ማብራት ፕሮግራም ስናካሂድ ዛሬ ላይ በሰላም እንደ አገር ያለነው ሰራዊቱ በከፈለው መስዋእትነት መሆኑን በማስተዋል ሊሆን ይገባል። ኢትዮጵያዊ ሁሉም በዚህ የመሳተፍ የሞራል ግዴታ አለበት።

የኢፌዲሪ ጠቅላይ ሚንስትር ዐቢይ አሕመድ የዛሬ ዓመት ይህን ዕለት በማሰብ በማህበራዊ የትስስር ገጻቸው ላይ ባጋሩት ጽሑፍ፤ "አቻምና ጥቅምት 24 ግፍ የተፈጸመባቸው ጀግኖቻችን ታሪክ ፈጽሞ የሚረሳ አይደለም። . . . ዛሬ የቆምነው ለእኛ ሲሉ የግፍ ጽዋን በተጎነጩ ጀግኖቻችን አጥንት ላይ ነው። እነዚያ ብርቅዬ የኢትዮጵያ ልጆች "ከወገኔ በፊት እኔ ልቅደም" ብለው ደማቸውን ለአፈር፣ ሥጋቸውን ለአሞራ ባይሰጡ ኖሮ የዛሬው ቀን ዛሬን ባልመሰለ ነበር" ብለዋል።

ቀኑ የሰሜን እዝ የመከላከያ ሰራዊት አባላትን በማሰብ እኛም ለአገራችን ሰራዊት በመሆን ቃል የምንገባበት እንዲሆን ይጠበቃል። እለቱ የኢትዮጵያ ጠላቶች አንገታቸውን የሚደፉበት ኢትዮጵያውያን ግን ቀና የሚሉበትና አገራቸውን ለመጠበቅ ቃላቸውን የሚያድሱበት መሆን ይገባዋል።

አሸባሪው ትህነግ አገር ለማፍረስ ያሰለፈውን መንጋ መመከት የሚቻለው እንደ ህዝብ በመንቀሳቀስ ነው። ቡድኑ እየዘረፈ እና እየገደለ አገር ለማዳከም የሚያደርገውን እንቅስቃሴ በጋራ መግታት፤ የፈለፈላቸው ሸኔን የመሰሉ ድርጅቶችን ጨምሮ አገር ለማፍረስ የቋመጡ ኃይሎችን እንደ ህዝብ መታገል ያስፈልጋል።

የሽብር ቡድኑ ጥቅምት 24 የፈጸመው ግፍ መዳረሻው አገር ማፍረስ በመሆኑ ተስፋ የቆረጠና ለመሞት የተዘጋጀ ቡድን በማሰለፍ እንዲሁም ሰርጎ ገቦችን በማደራጀት አገርን የማወክ እንቅስቃሴውን ለመቀጠል ቢጥርም ዛሬም የኢትዮጵያ የቁርጥ ቀን ልጆች ደማቸውን አፍስሰው አጥንታቸውን ከስክሰው እኩይ ተግባሩ እንዳይፈጸም የብረት መዝጊያ ሆነዋል።

ይህ ቡድን ኢትዮጵያን ለማፍረስ ከሚፈልግ የውጭም ሆነ የውስጥ ኃይል ጋር በማበር የጀመረውን እኩይ ተግባር መግታት የሚቻለው በጋራ በመሰለፍ በመሆኑ በሁሉም የአገሪቱ አቅጣጫ ያለው ኢትዮጵያዊ አገርን ከወራሪዎች ለመታደግ ቆርጦ ሊነሳ ይገባዋል።

በሰላም ውይይት ስም የኢትዮጵያን እጅ ጠምዝዞ የአሸባሪውን እስትንፋስ ለማቆየት የሚደረግ ማንኛውም ጥረት ለማክሸፍ በውጪም ይሁን በአገር ውስጥ ያሉ ሁሉም ኢትዮጵያውያን በጋራ ሊቆሙ የግድ ነው። ለዚህም በየጊዜው እየተካሄዱ በሚገኙ ሰላማዊ ሰልፎች ላይ በስፋት መሳተፉን አጠናክሮ መቀጠል የዜግነት ግዴታ ነው።

እየተካኄደ ያለው የሰላም ውይይት የአገር ሉአላዊነትንና የህዝቦችን በሰላም የመኖር መብት ታሳቢ ያደረገ፤ አሻበሪው ቡድን አራተኛ ዙር ጦርነት መክፈት የሚያስችለውን እድል ሆነ አቅም ሊፈጥርለት የሚገባ መሆን የለበትም። መከላከያ ሰራዊት ላይ የዛሬ ሁለት ዓመት የተፈጸመው ግፍና ክህደት መቼም የትም የማይደገምበት ትክክለኛው ሃዲድም ይህ ነው።

ልዩ
ዕትም

ቁምላቸው አበበ በአማራ ባህል፣ ቱሪዝምና ማስታወቂያ ቢሮ፣ በኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት፣ በደቡብ መገናኛ ብዙኀን፣ በጋዜጠኝነትና በታሪክ ባለሙያነት ያገለገሉ ሲሆን፣ የደቡብ ኤፍ ኤምን ከባልደረቦቻቸው ጋር በመሆንም አቋቁመዋል።በፌዴራል ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅትና በአለ በጅምላ በኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተርነት አገልግለዋል። ከአአዩ በቋንቋና ታሪክ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን የሰሩ ሲሆን፣ በዚሁ ዩኒቨርሲቲ በጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በማጠናቀቅ ላይ እያሉ ባጋጠማቸው ድንገተኛ ህመም ተስተንጉዷል። ጥልቅ ሀሳብ ያዘሉ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩሩ ፁሑፎችን በማህበራዊ ሚዲያና በተለያዩ ጋዜጦች በማውጣት ይታወቃሉ።



በቁምላቸው አበበ ይማም (ሞሼ ዳያን)
fenote1971@gmail.com

# ትውልድና ታሪክ ይቅር የማይለው የክፍለ ዘመኑ ታላቅ ክህደት እና አገር የመታደግ የመስዋእትነት ጥግ

ሀይዌል ዊሊያምስ፣"DAYS THAT CHANGED THE WORLD"በሚል ርዕስ ለንባብ ባበቃው ድንቅ መጽሐፍ፤ የመጀመሪያውን የባሕር ላይ ጦርነት በአቴናውያንና በፐርዥያ መካሄዱን፤ የሮማን ገዢ የጁሊየስ ቄሳርን መገደል፤ የእየሱስ ክርስቶስ ስቅለት፤ ኮንስታንቲኖፕል የቤዛንታይን ግዛት መቀመጫ መደረጉ፤ የኦቶማን ኢምፓየር ቤዛንታይንን በመርታት ኮንስታንቲኖፕል በመቆጣጠር ስሟን ወደ ኢስታንቡል በመቀየር ዛሬ ላይ የቱርክ (የቱርኪዬ) መዲና መሆኗን፤ የጀርመን ኮንፌደሬሲ መመስረት፤ የእስልምና መወለድ፣ የአውሮፓውያን አዳዲስ እሳቤ መጀመር፤ የፍራንኮች ቅዱስ ጦርነት፤ የሞንጎል ኢምፓየር ማንሰራራትንና ሌሎችን ሁነቶች በወሳኝ አለማቀፍ ክስተትነት ያነሳሳል።

ወደ አህጉራችንም ሆነ ወደ አገራችን ስንመጣ የአድዋ አንጸባራቂ ድል፤ የጣሊያን ፋሽስት ዳግም ወረራ፤ የጣሊያን የአዲስ አበባ ጭፍጨፋ፤ የጣሊያን 2ኛ ወረራ መቀልበስ፤ የኢትዮጵያ አብዮት፤ የሕወሓት አገዛዝ የተጀመረበት፤ የ1997 ምርጫ፣ የጠቅላይ ሚንስትር ዐቢይ ወደ አመራር መምጣትና የአሸባሪው ትህነግ ወደ መማጸኛ ከተማው መቀሌ መሸሽና መመሸግ፤ የሕዳሴው የመጀመሪያ የውሃ ሙሌት፤ የመጀመሪያው ኃይል ማመንጨት፤ የአረንጓዴ አሻራ የተጀመረበት፤ የስንዴ ምርትን ከውጭ ማስገባት እንዲቆም አቅጣጫ መቀመጡ፤ በአገሪቱ ታሪክ ታይቶና ተሰምቶ የማያውቀው በከሀዲውና አሸባሪው ትህነግ የጥቅምት 24 ቀን 2013 ዓ.ም በሰሜን ዕዝ ላይ ጥቃትና ጭፍጨፋ የወሳኞች ሁሉ ወሳኝ መታጠፊያና የታሪክ ማርሽ ቀያሪ ሆነው ሲዘከሩ ይኖራሉ። የቀድሞው በኢትዮጵያ የአሜሪካ አምባሳደር ቲቦር ናጅ፤ ሰሞኑን በዋሽንግተን ኤግዛማይነር ላይ ባስነበቡን መጣጥፍ ጦርነቱን ሕወሓት እንደጀመረው አረጋግጠው፤ የሰሜን ዕዝ ጥቃትን የደቡብ ካሮላይና ሚሊሻ የአሜሪካን የጦር ካምፕ በማጥቃት የእርስ በርስ ጦርነት ከመቀስቀስ ጋር አነጻጽረውታል።

በ21ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ከአጽናፍ እስከ አጽናፍ እግር እስኪቀጥን ቢታህሳስ እንደ አሸባሪው ትህነግ/ሕወሓት ጁንታና ጉጀሌ ያለ አሪዮስና አረመኔ የፖለቲካ ቡድን የለም። በዚህ ጊዜ በአለማችን የትኛውም ክፍል እንደ አሸባሪው ትህነግ ያለ እፉኝት የፖለቲካ ስብስብ በዲያጎን ፋኖስ እንኳ ቢፈለግ አይገኝም። በአፍሪካም ሆነ በላቲን አሜሪካ አልያም በእስያ ከአሸባሪው ትህነግ ጋር በዘመነ ጓዴነት (ኮንቴም ፓራሪስ) ሊነጻፀር የሚችል ምንም አይነት እኩይ ኃይል የለም። በዚህ ሁለት ዓመት ያረጋገጥነው ይሄን ሀቅ ነው። ለግማሽ ክፍለ ዘመን የዘለቁት እኩይ ተግባሮቹ እንዳሉ ሆነው። ገና ከምስረታው እንደሱ የደርግን ወታደራዊ አገዛዝ ለመታገል ጫካ የገቡትን እንደ ኢህአፓ፣ ኢዲዩና የትግራይ ድርጅቶችን እንደራደር፣ ልዩነታችንን በውይይት እንፍታ እያለ እያግባባ እውነት መስሏቸው ለድርድር ሲመጡ አንድ በአንድ የጨረሰ አረመኔና ከሀዲ ስብስብ ነው። እነ ስሁልን፣ ሙሴን፣ ሀየሎምንና ሌሎቹ በሀሳብ የተለዩትን እልፍ አእላፍ ታጋዮችንና ልጆቹን፤ የዛሬ ዓመት በሰሜን ዕዝ፣ በመከላከያ ሰራዊታችን፣ በአገራችንና በሕዝባችን ላይ እንደፈጸመው ክህደት ከጀርባ ወግቶ ወይም በጥይት ደብድቦ የጨረሰ አሪዮስ ነው። ለጊዚያዊ ፖለቲካዊ ጥቅም ሲል የሀውዜንን ሕዝብ በገበያ ቀን በአውሮፕላን አስፈጅቶ ሙሾ የሚያወርድና የአዞ እንባ የሚያነባ የሀፍረተቢሶች ስብስብ ነው።

በ77 ድርቅ ለትግራይ ሕዝብ የተላከ እርዳታን ሽጦ የጦር መሳሪያ የገዛ የማፍያ ስብስብ ነው። አገዛዝ ላይ በነበረባቸው 27 የግፍና የዘረፋ ዓመታት በከፋፍለህ ግዛ መርሁ በኢትዮጵያውያን መካከል ልዩነትንና ጥላቻን ሲጎነቁል የኖረ ከፋፋይ ቡድን ነው። ከማዕከላዊ መንግስት ስልጣን ከተነቀለ ወዲህም በተላላኪዎቹና ምንደኞቹ አማካኝነት እዚህም እዚያም ግጭትንና ሽብርን ስፖንሰር ሲያደርግና ስምሪት ሲሰጥ የባጀ እንዲሁም ደባን ሲጎነጉን ሴራን ሲሸርብ የመሸበት እኩይ ነው። ከጠቅላይ ሚንስትሩ የግድያ ሙከራ አንስቶ በመላ አገሪቱ ከተፈጸሙ የሽብር ወንጀሎች ጀርባ እጁ እንዳለበት የሚነገርለት ተስፋ የቆረጠ አጥፍቶ ጠፊ ነው። በእነዚህ ሁሉ ዓመታት የራሱን የሽብር፣ የሴራ፣ የደባ፣ የዘረፋና የእብሪት ክብረ ወሰን ሲሰባብርና ሲያሻሽል፤ ወደ አዲስ ምዕራፍ ሲያሸጋግር እና ልምድ ሲቀምር የኖረ መርገምት፣ ባንዳና ከሀዲ ነው። ታሪክም ትውልድም ዘላለም በማይረሷት በዚያች ጥቁር ቀን ማለትም ጥቅምት 24 ቀን 2013 ዓ.ም በሰሜን ዕዝ የፈጸመው ክህደት፣ ዘግናኝ ሽብርና ጥቃት የዚህን አረመኔ ስብስብ ማንነት ገሀድ አውጥቶታል።

ላለፉት 21 ዓመታት የቀን ሀሩር የሌሊት ቁር እየተፈራረቀበት፤ በቀበሮ ጉድጓድ የዕድሜውን ሲሶ ገብሮ ሲጠብቀው፤ በትግራይ ሕዝብ ደስታና ሀዘን ተካፋይ፤ ከትግራይ ሕዝብ ጋር ተጋብቶና ተዋልዶ የኖረ፤ በእርሻው በዘሩ በአረሙ በአጨዳውና በበራዬ እንዲሁም አንበጣን በመከላከል እንደ ቀንጃ (ረዳት ገበሬ) ተለይቶት በማያውቀው፤ ከሬሽኑ እየቀነሰ ለልጆቹ ትምህርት ቤትና ጤና ተቋም ሲገነባ፤ በኮቪድ 19 ለችግር ለተጋለጡ አሁንም ከእጅ ወዳፍ ከሆነች አበሉ ያካፈለ እሩህሩህና ለወገኑ ሟች የሆነ ሰራዊት በአረመኔውና ጉግማንጉጉ የአሸባሪው ትህነግ እፉኝት ቡድን ለማየት የሚዘገንንና ለመስማት የሚሰቀጥጥ ትውልድና ታሪክ ይቅር የማይለው ክህደትና ግፍ የተፈጸመበት በዛሬዋ ቀን 2013 ዓ.ም ነው።

ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ፣ " ለስግብግቡ ጁንታ ግፍ እስትንፋሱ፤ ጭካኔ ነፍሱ ነው። " ያሉትን እዚህ ላይ ያስታውሷል። ጥቅምት 30 ቀን 2013 ዓ.ም በወልቃይት ማይካድራ ትህነግ በዘር ማጥፏት እና በጦር ወንጀለኝነት የሚያስጠይቀውን 1600 ንጹሐንን በማንነታቸው የጅምላ ጭፍጨፋ ፈጽሟል። በወቅቱ የመንግስታቱን ድርጅት የጦር ወንጀል ሳይፈጸም እንዳልቀረ በመግለጽ ማጣራት እንደሚያደርግ ሲገልጽ፤ እንደ አምንስቲ ኢንተርናሽናል ያሉ አለማቀፍ ተቋማትን ጨምሮ እነ ሲኤንኤንና ቢቢሲም ይሄን ዘግናኝ ጭፍጨፋ የተቀባበሉት ቢሆንም እዚህ ግባ የሚባል ፖለቲካዊና ዲፕሎማሲያዊ ጫና አለማድረጋቸው አገሪቱን ዛሬ ለምትገኝበት ውጥንቅጥ ዳርጓታል።

አሜሪካ ምዕራባውያንና አለማቀፍ ተቋማት ሲጠቃ ጩኸቱን ሲያስተጋቡ ሲያጠቃ ግን ድምጻቸውን ከማጥፋት ባሻገር የሳተላይት ድጋፍ ይሰጡታል። የዚህ አረመኔ ግፍ መቼ በዚህ ይቆምና፤ ጠቅላይ ሚኒስትሩ በወቅቱ በፌስ ቡክ ገጻቸው ባሰፈሩት ፅሁፍ፣ ጀግናው የመከላከያ ሠራዊት ሽራሮን ሲቆጣጠር፣ እጅና እግራቸውን የፈጥኝ ታስረው የተረሸኑ የመከላከያ አባላትን ማግኘቱን ገልጸዋል። በየቦታው ከዚህ የከፋ ጭካኔና ግፍ ሊያጋጥም እንደሚችል ጠቁመዋል። ጭካኔው ልብ የሚሰብር መሆኑን ጠቅላይ ሚንስትሩ በወቅቱ ገልጸው ዓላማውም ኢትዮጵያን መስበር ነበር፤ ኢትዮጵያ ግን ከአልማዝ የጠነከረች መሆኗንም አመልክተዋል። ሰሞኑን ባስተላለፉት መልዕክት ይሄን ሀሳባቸውን ደግመውታል።

የጁንታው ዓላማ ሠራዊቱንና ሕዝቡን አስቆጥቶ ለበቀል እርምጃ ማነሳሳት እንደሆነም ጠቁመው፤ ኢትዮጵያም ልበ ሰፊ ሕዝብና ሠራዊት እንዳላት አስታውቀዋል። ሠራዊቱ ለሰብዓዊነት የተናጠል ተኩስ አቁም አውጆ እስከወጣበት ሰዓት ድረስ ሰብአዊ እርዳታና አገልግሎት እየሰጠ እንደነበር አስታውሰው፤ ነጻ ባወጣቸው አካባቢዎች ሕዝቡን እየመገበ፣ እያከመና እየተንከባከበ ነበር ብለዋል።

ሌተናል ጄኔራል ባጫ ደበሌ የዛሬ ዓመት በጥቃቱ ሰሞን የሰሜን ዕዝ ጎብኝተው ሲመለሱ የሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫ የአሸባሪው ትህነግ እፉኝት ስብስብ ምን ያህል ከትግራዋይና ከኢትዮጵያ የስነ ልቦና ውቅር፣ ሀይማኖትና ወግ ያፈነገጠ መደዴና ወፍ ዘራሽ እንደሆነ ያሳያል። ይህ ስግብግብና አረመኔ ቡድን እውን ከትግራይ ሕዝብ አብራክ የተገኘ ነው !? የሚል ጥያቄ ለማንሳት ያስገድዳል። አረመኔው ስግብግብ ጁንታ ሰራዊቱ በተኛበት በውድቅት ሌሊት በማረድ፣ በቦንብና አውቶማቲክ በማርከፍከፍ የአውሬነት ጥጉን አሳይቶናል። አስከሬን ከሙሽራ ባልተናነሰ ክብር በሚሰጥበት አገር አስከሬን ገፎ ከማዋረድ ባሻገር የአውሬ ሲሳይ እንዲሆን አድርጓል። ለስልጣንና የሸረበውን ሴራ ለማስፈጸም ሲል ምንም ከማድረግ እንደማይመለስ አረጋግጧል። ከዚያ በኋላ በማይካድራ ጋሊ ኮማ አጋምሳ ጭና ሰሞኑን ደግሞ በሀይቅ በኮምቦልቻና በውጫሌ ይሄን አብሮ አደግ አረመኔነቱን በአደባባይ አስመስክሯል።

ይሁንና ክቡር ጠቅላይ ሚንስትሩ በሰሜን ዕዝ ጥቃት ወቅት እንዳሉት፣ ዛሬም ሕልውናችን በሉዓላዊነታችን በግዛት አንድነታችን ላይ ጦርነት ተከፍቶብናል። ይህ የጡት ነካሽ፣ የከሃዲና የባንዳ ስብስብ የተናጠል የተኩስ አቁሙን እንደ መልካም አጋጣሚ በመውሰድ በአማራና በአፋር ክልሎች በሕዝባዊ ማዕበል የውጭ አገር ቅጥረኛ ወታደሮችን (መርሲናሪስ) ሳይቀር በማሳተፍ ወረራውንና ጥቃቱን እያስፋፋ ይገኛል። አሸባሪው ትህነግ በትግራይ ክልል በሚገኘው የመከላከያ ሰራዊት ሰሜን እዝ ላይ ጥቃት በመሰንዘሩ አገር እና ህዝብ ለማዳን ሲባል መከላከያ ሠራዊቱ የኃይል እርምጃ እንዲወስድ እንደታዘዘው ሁሉ ዛሬም ሁሉንም ክልሎች ያሳተፈ ክተት ታውጇል።

አገር እና ህዝብ ለማዳን ሲባል ኃይል የመጨረሻው አማራጭ ሆኗል። ለዚህ ነው ጠቅላይ ኤታማዦር ሹም ጀኔራል ብርሃኑ ጁላ በወቅቱ" ሳንወድ ተገደን አሳፋሪ ጦርነት ውስጥ ገብተናል " ያሉት፤ ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓቱን ለመጠበቅና አገርን ከውጭ ወራሪ ለመከላከል አገራዊ ተልዕኮ ተቀብሎ በግዳጅ ላይ የነበረን የአገር መከላከያ ሠራዊት ላይ የተከፈተው ጥቃት" የአገር ክህደት" ነው ሲሉ ገልጸውታል። በሌላ በኩል ብልፅግና ፓርቲ የተከሰተውን ጦርነት አስመልክቶ በወቅቱ አውጥቶት የነበረው መግለጫ ዛሬም ወቅታዊ ሆኖ ስላገኘሁት እንዳለ እንደሚከተለው አቅርቤዋለሁ። የትግራይ ሕዝብ ከመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር በመሆን በአገር ላይ ክህደት ፈጽሟል ያለውን የሕወሓት ኃይል እንዲታገል ጥሪ አቅርቦ። "የትግራይ ሕዝብ ከሌሎቹ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ጋር ጠንካራ ታሪካዊ አንድነትና ውህደት ያላቸው፣ ባህላዊና ጥንታዊ ሃይማኖታዊ እሴቶችን የሚጋሩ፣ በጋብቻና በደም የተሳሰሩ፣ በፀረ ጭቆና ትግል ከሌሎች ሕዝቦች ጋር ሆነው በአንድ ጉድጓድ ክቡር መስዋዕትነት እየከፈሉ አሁን ላለንበት የአገረ መንግሥት ምሥረታ ጉልህ አሻራ ያሳረፉ ሕዝቦች ናቸው፤" ያለው መግለጫው፣ በማስከተል " የሕወሓት አጥፊ ቡድን የአገርንና የሕዝብን ሰላም፣ አደጋ ላይ ለመጣል የሚያደርገው ሴራ መሆኑን አውቃችሁ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር ያላችሁ ወንድማዊና ቤተሰባዊ ግንኙነታችሁ ሳይቋረጥ የትግራይን ሕዝብ የሚያለያዩ ሙከራዎችን በፅናት እንድትታገሉ የከበረ ጥሪያችንን እያቀረብን በዚህ አሸባሪ ቡድን ላይ ዕርምጃ በመውሰድ ኅብረ ብሔራዊ አንድነታችንን ለማስቀጠል በምናደርገው ትግል ውስጥ ከጎናችን እንድትሆኑ፤ " ሲል ጥሪውን አቅርቧል። የትግራይ ክልል የፀጥታ ኃይሎች በአገሪቱ ከሚገኙ የፀጥታ ኃይሎች ጋር በጋራ በመሆን ሕዝባዊነታችሁን ጠብቃችሁ ለአንዲት ሉአላዊት አገር መከበርና ቀጣይነት ክቡር መስዋዕትነት በመክፈል ላይ መሆናችሁን ብልፅግና ፓርቲ ከልብ እንደሚገነዘብ ገልጿል።"ምንም እንኳ በክልሉ አምባገነን የሆነው የሕወሓት ቡድን በትግራይ ሕዝብ ላይ እያደረሰ ያለውን እንግልትና ስቃይ የታዘባችሁ ቢሆንም ባለው ፀረ ዴሞክራሲያዊ አካሄድ ምክንያት ለውጡን ከሕዝባችሁ ጋር ሆናችሁ ማጣጣም ሳትችሉ ቀርታችኋል፤" ያለው መግለጫው፣ " ሆኖም ለረዥም ዓመታት የክልሉን ሕዝብ ሰላም ደኅንነት በኃላፊነት መንፈስ ወስዳችሁ ስትጠብቁ የቆያችሁ የክልሉ ፖሊስ፣ ልዩ ኃይል አባላትና ሌሎችም በሕዝብ ትከሻ ላይ ሆኖ እየቀለደ ባለው ዘራፊና አጥፊ የአሸባሪው ትህነግ ቡድን ላይ ዕርምጃ ለመውሰድ እየተደረገ ያለውን ትግል በመቀላቀል ሕዝባዊነታችሁን እንድታረጋግጡ በድጋሚ ጥሪያችንን እናቀርባለን፤ "

## እንደ ማውጫ

መንግስት ስግብግቡን የአሸባሪው ትህነግ ጁንታ ቡድን ከሁለት ዓመት በላይ የለውጡ አካል እንዲሆን በአደባባይም በጓዳም ለምኖታል። ከሰማይ በታች ያሉ የሰላም አማራጮቹን ሁሉ አሟጦ ተጠቅሟል። በሰሜን እዝ ላይ ጥቃቱን ለመሰንዘር ጥቂት ሰዓታት ቀርተውት እያለ እንኳ አይተ ደብረጺዎን ገብረሚካኤል ጋር ክቡር ጠቅላይ ሚንስትር ስለክልሉ ኢኮኖሚና እና ስለአዲሱ የብር ለውጥ ተነጋግረዋል። በዚህ አላበቃም በዛው ምሽት አዲሱ የብር ኖቱም ወደ መቀሌ ተልኳል። ይህ መንግስት እስከ መጨረሻዋ ደቂቃ ድረስ ለሰላምና ለፖለቲካዊ መፍትሔ የነበረውን ቁርጠኝነት ያሳያል። ክህደትና አረመኔነት ምሱ የሆነው እፉኝቱ የአሸባሪው ትህነግ ጁንታ ግን ታሪክም ትውልድም ይቅር የማይለውን ክህደት ፈፅሟል። በዚህም ቀዩን መስመር አልፏል። የኢፌዴሪ መንግስትም በሚገባው ቋንቋ ለማነጋገር ተገዷል።

ስግብግቡና ከሀዲው የአሸባሪው ትህነግ ጁንታ የሰሜን ዕዝን በውድቅት ሌሊት ካጠቃ፤ በዚህም የአገሪቱን ሉዓላዊነት ከተዳፈረና ቀዩን መስመር ካለፈ በኋላ የኢፌዴሪ መንግስት ሕግን ለማስከበር ሲንቀሳቀስ ጁንታው ተወረርሁ፤ ጦርነት ተከፈተብኝ እያለ በተለመደው ቅጥፈቱ አለምን እንዳዳረሰው ሁሉ ሰሞኑን እያስፋፋው ያለውን ወረራ ለመቀልበስና ግብዓተ መሬቱን ለማፋጠን ሕዝብ ዳር እስከ ዳር ሲነሳ ደግሞ ተመሳሳይ እየየውን ያቀልጠዋል። ከሰሞነኛው የደሴና የኮምቦልቻ ጊዜያዊ የድል ስካር ነቅቶ በአሜሪካና በአውሮፓ ደጋፊዎቹ በየጎዳናው እንዲከባለሉ ያደርጋል። የተወሰነውን አለማቀፍ ማህበረሰብና ሚዲያም ማደናገሩን ካቆመበት ይቀጥላል።

ይሄን ሸሩን ቀድሞ ማምከንና ማጋለጥ፤ የሕዝብ ግንኙነትና የዲፕሎማሲ ስራውን ማጠናከር ከመልሶ ማጥቃቱ እኩል ትኩረት ሊሰጠው ይገባል። ይህ ኃላፊነት ለመንግስት ብቻ የሚተው ሳይሆን ለአገራችን ሁላችንም ቃል አቀባይ፣ አፈ ቀላጤ መሆንን የሚጠይቅ ስለሆነ ከዲያስፖራው ጋር ተናቦ መስራት ይጠበቅብናል። ሳይጠቀስ መታለፍ የሌለበት፤ ክቡር ጠቅላይ ሚንስትር፣ " ይህን ሕዝብ ማገልገል በራሱ ክብር ነው !" ያሉለትም ሆነ፤ መከላከያ ሰራዊታችን " ለዚህ ሕዝብ መሞት ክብር ነው !" ያለለት የኢትዮጵያ ሕዝብ ልዩነቱን ወደ ጎን ብሎ ከመንግስት እና ከመሪው ጎን ከመሰለፍ አልፎ የገንዘብና የአይነት ድጋፍ በማድረግ ደጀንነቱን አጠናክሮ መቀጠል ይጠበቅበታል። የኢትዮጵያን ሕዝብ ደጀን ያደረገ ጀግና ሰራዊት ባጠረ ጊዜና መስዋዕትነት እጅን በአፍ የሚያስጭን ድል በማስመዝገብ ያንዣበበውን የህልውና ስጋት እንደሚገፍ ቅንጣት ታክል አንጠራጠርም።

#መቼም አንረሳውም።

# ‹‹ ወታደር ሆኜ ጓዴ ሲከዳኝ፣ ሲሰነዝርብኝ እና ሲገድለኝ የሚሰማኝ ስሜት በአንድ ስሜት የምገልጸው ሳይሆን እድሜ ልክ የሚያመኝና የሚቆጠቁጠኝ ነው ››

የሃምሳ አለቃ ብርሃኑ አማረ
የቀድሞ የኢትዮጵያ ሰራዊት የድጋፍ እና የልማት ማህበር ፕሬዚዳንት

አስቴር ኤልያስ

ልክ ዛሬ ሁለት አመት ጥቅምት 24 /2013 ዓ.ም መቼም ቢሆን ከአዕምሮ የማይፋቅ ግፍ በሰሜን እዝ ላይ በአሸባሪው ትህነግ ተፈጽሟል። ሰራዊቱ ሕዝብ የሰጠውን አደራ በኃላፊነት ለመወጣት ሌሊት በቀበሮ ጉድጓድ፤ ቀን ደግሞ በአርሶ አደሩ ማሳ ሲታትር አመታት አስቆጥሯል። በእለቱ ከአንበጣ መንጋ ጋር ሲታገል ውሎ እንቅልፍ በጣለው ሰዓት ወገኔ ነው ባለውና በገዛ ወንድሙ ክህደት ተፈጽሞበት ከጀርባው ተወግቷል። ይህ የቡድኑ የክህደት ተግባር ምንጊዜም ቢሆን የማይረሳ አይደለም። እለቱ ዛሬ ‹‹ጥቅምት 24ን መቼም አንረሳውም›› በሚል መሪ ሐሳብ የሚታሰብ መሆኑን አስመልክተን በጉዳዩ ዙሪያ ከቀድሞ የኢትዮጵያ ሰራዊት የድጋፍ እና የልማት ማህበር ፕሬዚዳንት ከሃምሳ አለቃ ብርሃኑ አማረ ጋር ያደረግነውን ቃለ ምልልስ እንደሚከተለው አጠናቅረን አቅርበነዋል።

**አዲስ ዘመን፡- የዛሬ ሁለት ዓመት ልክ በዛሬው ዕለት አሸባሪው ትህነግ ከአገር መከላከያ ሰራዊት ጀርባ አድብቶ ሰራዊቱን የወጋበት ቀን ነው፤ በእለቱ የተሰማዎ ስሜት ምን አይነት ነበር?**

**ሃምሳ አለቃ ብርሃኑ፡-** የኢፌዴሪ መከላከያ ሰራዊት የሀገሪቱን ዳር ድንበር ለማስከበርና የዜጎቿን ሰላም ለመጠበቅ ሲል በአካባቢው ለሁለት አስርት የቆየ ነው። ሰራዊቱ በአካባቢው ካለው ኅብረተሰብ ጋር የተዋሃደ፤ የተዋለደም ጭምር ነው። ከውትድርና ባሻገር ማህበራዊ ሕይወቱ ከሕዝቡ ጋር ተሳስሮ የዘለቀ ነው።

በዚህ ሰራዊት ላይ በአሸባሪው ትህነግ የደረሰበትን በደል እንደወታደር እርሱ ጫማ ውስጥ ሆኜ ስናገር ስሜቱ እጅግ በጣም የሚያም ነው። አንድ ወታደር ከጎንሽ አብሮሽ ታጥቆ፤ ጓደኛዬ ነው፤ ወገኔ ነው፤ ብለሽ ሕይወት ልትሰጪውም ቁርጠኛ ሆነሽለት፣ አካልሽን ገብረሽለትና ደምሽን አፍስሰሽለት የኔ የራሴ ነው በማለት ሐሳብሽን ጥለሽ ባንቀላፋሽበት ሰዓት እንደዚያ አይነት ክህደት መፈጸሙ ምናልባት ለእሱ አይነት ክህደት ቋንቋ ሊጠፋ ይችላል።

ስሜቱን መለካትና መገመት ቢቻል እጅግ ሲበዛ የጭካኔ ጥግ የታየበት ሆኖ ይሰማኛል። በወገን ላይ አይደለም ጠላትን ስትማርኪ እንኳን የአያያዝ ወታደራዊ ስነ ምግባር አለው። ያንን ወታደር በጥንቃቄና በሰብዓዊነት ይዘሽ ከምትበይው አካፍለሽ ነው የሚትይዥው። ከዚህ አንጻር ሲታይ መከላከያችን ላይ የደረሰው ጥቃት ለማመን የሚከብድ ሆኖ አግኝቼዋለሁ።

በሰራዊቱ ላይ በርካታ ኢ-ሰብዓዊ ድርጊቶች ተፈጽመዋል። እነዚህን መግለጽ የሚቻለው የክህደት ድርጊት ነው በሚል ብቻ አይደለም። ባንዳነት ጭምር ነው። ባዳነትና የባንዳ ስሪት መሆን ወገንንም አገርንም ያስከዳል። በወገናችን ላይ የተፈጸመው ይህ ነው። ወትሮም የነበሩት በባንዳነት ውሃ ልካቸው ላይ እንጂ በኢትዮጵያዊነት ውሃ ልክ ላይ እንዳልነበሩ በተግባራቸው አሳይተውናል።

ኢትዮጵያውያን በዘመናችን ስንዴ ለምነን እናውቃለን። እውነት ነው እራፊ ጨርቅም ለምነን እናውቃለን። ነጻነት ግን ለምነን አናውቅም። ምክንያቱም ነጻነታችንን በራሳችን መንገድ መስዋዕትነት ከፍለን አስከብረን የኖርን ሕዝቦች ነን። ያ በሰሜኑ የአገራችን ክፍል ጀርባውን በከሃዲዎቹ የተወጋው ሰራዊት ከዚህ ጀግና ሕዝብ የወጣ ጀግና ሰራዊት ነው። ይህን ሰራዊት መድፈርና እንዳልነበር ማድረግ ማለት ኢትዮጵያን ማፍረስ ማለት ነው። ሌላ ሊሰጠው የሚችል ትርጉም አይኖረውም። የአገር መከላከያ ሰራዊት ማለት ኢትዮጵያን የሚያቆይና የሚያቆም ነው። የኢትዮጵያውያንን ክብር የሚያስጠበቅ ማንነትና ቁመና ያለውን ሰራዊት በዚህ መልኩ ማስተናገድ ማለት እጅግ በጣም ከባድ ክህደትና የባንዳነት ተግባር ነው።

የጭካኔውን ጥግና እንደ ወታደር የምገልጸው በህመም ስሜት ውስጥ ሆኜ ነው። እዛ ወታደር ጫማ ውስጥ ቆሜ ወንድሜ/ጓዴ ሲከዳኝ፣ ሲሰነዝርብኝ እና ሲገለኝ እና የሚቆጠቁጠኝ ነው። በአጭሩ ፈውስ የሌለው ሕመም ማለት ነው። እኔም ወታደር ነበርኩና ይህ እሳት ከውስጤ መቼም ቢሆን ሊጠፋ አይችልም።

**አዲስ ዘመን፡- የአሸባሪው ትህነግን ጭካኔና ክፉ የሆነውን ባህሪ እርስዎ የሚገልጹት እንዴት ነው?**

**ሃምሳ አለቃ ብርሃኑ፡-** በመሰረቱ ትህነግ የተባለው ቡድን የኢትዮጵያ ታሪካዊ ጠላቶች በራሳቸው አመለካከት ቀርጸው ያስማሩት የኢትዮጵያ ትልቁ ጠላት ነው። ይህ ቡድን ወደ ጫካ ሲገባ በጎ ነገር አልነበረውም። ምክንያቱም እኔ ወታደር በነበርኩበት ጊዜ ለደርግ መንግስት ብዙ ጊዜ የድርድር ወንበሮች ተዘጋጅተውለት ያውቃል። ይህ አሸባሪው ቡድን በየጊዜውና በየደረሰበት ደረጃ ጥያቄዎቹን ይቀያይር ነበር። በሐሳቡም ይገለባብጥም ነበር። ለሰላም ምንም አይነት ፍላጎት የሌለው ቡድንም ነበር።

በሌላ በኩል ደግሞ ጭካኔው ዳር የሌለው ነው። የመጀመሪያው ጭካኔ ያረፈውም በራሱ ማኅበረሰብ ላይ ነው። ከ40 እና ከ50 ሺ ያላነሱ የትግራይ ተወላጆችን ቅርጥፍ አድርጎ የዋጠ አረመኔ ቡድን ነው። ስለሆነም ለሌላው ሩህሩህ ይሆናል ብለን አንጠብቅም። ከዚህ አንጻር የቡድኑ ስብስብ በጭካኔና በክህደት እንዲሁም ለጠላቶቻችን ፈረስ በመሆን እና በባንዳነት የሚያገለግል ነው። ይህ ቡድን ከዚህ ውጭ ስም ሊሰጠው አይችልም። ስለዚህም ከዚህ ቡድን የሚጠበቅ በጎ ነገር አይኖርም። ወደስልጣንም ሲመጣ ባህሪው ያው ያልተለወጠ ማንነቱን ቁልጭ አድርጎ ያሳየነው፤ ሲያስር፣ ሲገርፍና ሲዘረፍ የነበረውም ለዚህ ነው። ቆሜለታለሁ ለሚለው ለትግራይ ሕዝብ እንኳ ርህራሄ ያጣው በዚህ ባህሪው ነው።

የዚህ ቡድን ስሪት ኢትዮጵያዊነት አይደለም። ከዚህ የተነሳ ድርጊቱ ሁሉ ከኢትዮጵያዊነት ውጭ ያፈነገጠ ነው። በመሆኑም ከኢትዮጵያዊ ማንነት ውጭ የወጣን ቡድን ስለኢትዮጵያ ብሎ የሚገደው፣ የሚጨንቀው እንዲሁም የሚራራበትና የሚያዝንበት አንዳችም ስብዕና የለውም። ከትህነግ እንዲህ አይነት ባህሪን መጠበቅ ከእባብ እንቁላል እርግብ እንደመጠበቅ የሚቆጠር ነው።

ቡድኑ ሸፍጠኛ ከመሆኑም በተጨማሪ ዘዋሪዎች ያሉት ነው። በተለይ ደግሞ ቃል የገባላቸው የኢትዮጵያ ታሪካዊ ጠላቶች አሉ። ቤተ መንግስትም ገብቶ የነበረው የእነዚህ ታሪካዊ ጠላቶቻችንን ጉዳይ እንዲያሳልጥ በመመረጡ ነበር። ብርቱ ኢትዮጵያውያን በከፈሉት መስዋዕትነት፣ የኢትዮጵያ ወጣቶች ባደረጉት ተጋድልዎ፣ በርካታ የሰብዓዊ መብት ተሟጋቾች ባስተጋቡት እውነት፣ የኪነ ጥበብ ሰዎች ባደረጉት ትግል እና ሌሎችም በከፈሉት ዋጋ ቡድኑ ከመንበሩ ሊፈነገል በቅቷል። በተለይ በእርሱ ዘመን የእርሱን ፕሮፓጋንዳ በግድ ሲጋቱ የነበሩ የኢትዮጵያ ወጣቶች የምትሻለው ኢትዮጵያ ናት ብለው ታግለውታል። የወደቀውም የወጣቱ ትግል ኃያል ስለሆነ ነው።

የእርሱን ጭካኔ የሚገለጸው በተለያየ መንገድ ነው። ቡድኑ ሲወለድ ጀምሮ ተፈጥሯዊ ማንነቱ ክህደት፣ ሌብነት፣ ማጭበርበር እንዲሁም ሴራና ሸፈጥ ነው። በእርሱ ዘንድ እውነት የሚባል ነገር የለም። እስካሁኗ ጊዜ ድረስ እንኳ እውነት የተባለ ነገር አይተነፍስም። እየተሸነፈ፣ እየተመታ፣ እየወደቀና እየሞተ ባለበት በዚህ ጊዜ እንኳ ሐቁን መናገር አይፈልገም። ከዚያ ይልቅ የተካነበትን ፕሮፓጋንዳ እንደለመደው ሊያስት ሲናገር ይውላል። በዚያ ላይ የሚጠበብ ከመሆኑም በተጨማሪ ነጮች ወዳጆቹ ያግዙታል። በዙሪያ ታሪካዊ ጠላቶችን ጨምሮ ሌሎች ሀይሎች አሉ ፤ ለእነዚህ ጋር ቀኝ እጅ ሆኖ እየሰራ ነው።


ፎቶ - በገባቦ ገብሬ

ይህ ቡድን ማንነቱን የካደ ነው። ነገር ግን ቡድኑ በኢትዮጵያ ምድር ተወልዶ የኢትዮጵያ እናት ጡት የጠባ፣ በኢትዮጵያ ምድር ላይ የኢትዮጵያን አፈር ፈጭቶ፣ በወንዟ ተራጭቶ ያደገ ስብስብ ነው። ግን ደግሞ ኢትዮጵያን የካደ ማንነት ያለው ቡድን ነው። ከዚህ አንጻር ክፋቱ በእጅጉ የት የለሌ ነው። ለዚህም ነው ወንድሞቹ ላይ እጁን ያለርህራሄ ያነሳው።

ከሁለት አስርት ዓመት አብሮት የነበረ ሰራዊት ያደረገው ነገር ቢኖር አንበጣ ሲመጣ ማባረር፣ የሚታጨድ እህል ሲደርስ ማጭድ ነበር። ከደሙ ፍሳሽ እና ከአጥንቱ ፍላጭ ባሻገር ከዚህ አልፎ ሕይወት ከመስጠት በተጨማሪ ያለውን ሁሉ ከማካፈል ውጭ የሰራው ሌላ ነገር አልነበረም። ለዚህ ወገኑ ምንም አልራራለትም። ይህ የጭካኔ ጥጉ ምን ያህል ለማሰብ የሚከብድ እንደሆነ አመላካች ነው።

**አዲስ ዘመን፡-በመከላከያ ሰራዊት ላይ በጨካኙ ቡድን የደረሰውን ጥቃት ለመቀልበስ መንግስት የሄደበት አግባብ እንዴት ያዩታል?**

**ሃምሳ አለቃ ብርሃኑ፡-** በመሰረቱ የኢትዮጵያ መንግስት ጥቃቱን ለመቀልበስ የሄደበት ፍጥነት የሚያስገርም ነበር። እውነት ለመናገር ወታደር የሆንኩበትን ዘመን በአግባቡ አውቀዋለሁ። የደርግ መንግስት ሙሉ አቅም የነበረው እንደሆነ ይታወሳል። በተለይ ወደሰሜኑ ግንባር ከዞረ በኋላ የኢትዮጵያ ሰራዊት በምስራቅ አፍሪካ አስፈሪው ሰራዊት እንደነበርም የሚዘነጋ አይደለም።

በትህነግ የተሰነዘረው ጥቃት በወቅቱ ሰራዊቱን ብትንትኑ እንዲወጣ ቢያደርገውም ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያውያን መሪዎች ቁርጠኛ ሆነው የተወሰደው እርምጃ ኢትዮጵያን ዳግም በጸና መሰረት ላይ ማቆም ያስቻለ ነው። ኢትዮጵያ አትሸነፍም የምንለው ለዚህ ነው። እርግጥ ነው በወቅቱ የሰራዊት ቁጥሩ በጣም ቀንሷል፤ መሳሪያው የነበረውም በእነርሱ እጅ ነው ሊባል ይችላል፤ ነገር ግን የኢትዮጵያ መንግስት የተናበበ ተግባር በመፈጸምና በኢትዮጵያዊነት ውሃ ልክ ላይ የቆመ በመሆኑ ባለው ኃይል፣ እኩይ ተግባር የነበረውን ቡድን ሲያሸንፈው ተመልክተናል። ይህ የሚያሳየው ኢትዮጵያ ምን ያህል ደባ ቢፈጸምባትም የማትሸነፍ መሆኗን ነው።

እውነታውን እንደወታደር ስመዝን መሪዎቻችን በነበራቸው ብቃት ደስተኛ ነኝ። በመከላከያ ውስጥ የነበሩ ጀነራል መኮንኖች፣ ተዋጊ ወታደሮች በተለይ ደግሞ ሴት ወታደሮች ያሳዩት ጀብዱ የማይረሳ ነው። እኔ ለምሳሌ እንደገና የመወለድ እድል ቢሰጠኝ መሆን የምፈልገው ወታደር ነው። ሴት ወታደሮቹን ስመለከት የሚመለስለኝ ሴት ወታደር የሆነች አይደለም፤ ኢትዮጵያ ራሷ ወታደር የሆነች ያህል ይሰማኛል። ከዚህም የተነሳ አገሬ ራሷ ወታደር ሆና ስለምትታየኝ ምንአለ አብሬት ብዋጋ ብዬ እንዳስብ ያደርገኛል። በዛ ውስጥ የነበሩ ሴት ወታደሮች ትንታጎች ናቸው፤ ወንዱን የሚያጀግኑም ነበሩ። ከአመራሮች ባሻገር ተዋጊው ራሱ እየከፈለ የነበረው ዋጋ በቆራጥነት ነው። በጥቅሉ ኢትዮጵያ እንድታሸነፍ ያደረጋት የመሪዎቿ ጥበብ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- አሸባሪው ትህነግ የራሱ አጀንዳ የሌለው ከመሆኑም በላይ በሌላ የሚዘወር ቡድን ነው፤ ይህን ርዕይ የሌለውን ስብስብ በኢትዮጵያ ላይ እየደረሰ ካለው የውጭ ጫና ጋር አስተሳስረው ቢገልጹልን ?**

**ሃምሳ አለቃ ብርሃኑ፡-** በዘመነ ደርግ ጊዜ አንድ አምስት የሚሆኑ የፖለቲካ ድርጅቶች ነበሩ። ከእነዚህ ውስጥ አንዱ ትህነግ ነው። ነጮቹ የሌሎቹን መርሃ ግብር በሙሉ ተመልክተው ያስተዋልኩት ነገር ቢኖር ምንም እንኳ ፍላጎታቸው ስልጣን ላይ መውጣት ቢሆንም መደምደሚያው ግን ኢትዮጵያ ናት። ቡድኑ ግን መደምደሚያው ኢትዮጵያ አልነበረችም። ለዚህም ነው ነጮቹ ‹ይህ ቡድን ይስማማናል፤ ይበጀናል› በሚል

የተቀበሉትና በጀት የበጀቱለት። የአገሩን ሰርዶ በአገሩ በሬ እንዲሉ እነሱ የመረጡበት ትልቁ ምክንያት ይህ ነው።

የኢትዮጵያ መንግስት ደግሞ ኃላፊነት ያለበት ነው። በዚያ ላይ ኢትዮጵያ የጸና አገረ መንግስት ሊኖራት ይገባል። አለዚያ እንደሶሪያ፣ ሊቢያ ወዘተ ዕጣ ፈንታ ሊያጋጥመን ይችላል። የእነዚህ አገር ዜጎች ‹‹እርዱን›› ብለው በኢትዮጵያ ጽፈው ደረታቸው ላይ በማንጠልጠል ማሳየት ጀምረዋል። ይሁንና እነርሱ የአገራቸው ቋንቋ ምን ነበር ቢባል አረብኛ ነበር። ልክ እንደእነርሱ ሲኮን ቋንቋና ብሔር አፈር ይበላል። ስለዚህ በኢትዮጵያ ውሃ ልክ ላይ መቆም ለኢትዮጵያውያኑ ያዋጣዋል ብለው መሪዎቿ በኢትዮጵያ ሐዲድ ላይ እያስጓዟት እዚህ ደርሰዋል። መሪዎቹ ኢትዮጵያዊ ሆነው ባይገኙ ኖሮ ከጥቅምት 24 በኋላ ምንም ጥያቄ የለውም ኢትዮጵያ ትበታተን ነበር ብሎ በድፍረት መናገር ይቻላል።

ስለዚህ ይህ ቡድን መጀመሪያ የተጣበው ክህደት ነው። ብሎም ባንዳነት ነው፤ እሱን ባንዳነት ተጠቅመው ሲጋልቡት የነበረው እንደ ፈረስ ‹ቼ› የሚሉት ኃይሎች እስከመጨረሻው አልተለዩትም። ከዚህ አንጻር በዓለም አቀፍ ደረጃ በርካታ ተጽዕኖዎች ነበሩት። በተለይ ደግሞ በዲፕሎማሲው ዘርፍ ትልልቅ ፈተናዎች ነበሩ። ኢትዮጵያ እርዳታ እንዳታገኝ፣ የመሳሪያ ግዥ እንዳትፈጽም ትከለከል ነበር። እንዲያም ሆኖ ጥበበኛ መሪዎቿ ኢትዮጵያን ከተደቀነባት ተጽዕኖ ነጻ ሲያወጧት ተስተውለዋል።


ዛሬ ብቻ አይደለም፤ የመጀመሪያዎቹን እነ አጼ ምኒልክ እና እነ አጼ ኃይለስላሴን ብንለከት ኢትዮጵያ አጣብቂኝ ውስጥ ገብታ በነበረችበት ጊዜ ሁሉ ጥበባቸውን ተጠቅመው ከፈተና አውጥተዋታል። ዛሬም የኢትዮጵያ መሪዎች እንደ እሱ አይነት ጥበብ በደማቸው ውስጥ ስላለ ኢትዮጵያ ፈተናን አልፋ እንድትሻገር እያደረጓት ነው። ይህን ጥበብ ነጮቹ ሲመለከቱ እንዳያሳካ የተቻላቸውን ያህል እየታገሉን ይገኛሉ፤ ታግለዋልም። ይሁንና ኢትዮጵያ ካለችበት ፈተና በሚያስገርም ብልሃት እየወጣች ትገኛለች።

እውነት ለመናገር በአሁኑ ሰዓት እየተሰራ ያለውን የስንዴ ምርት ስመለከት በጣም ያስገርመኛል። ድሮ የምንለምነው ስንዴ ነበር። ኢትዮጵያ በታሪኳ ነጻነትን ለምና አታውቅም። የጀግና አገር ስለሆነች የማትነካና የማትደፈር ሉዓላዊት ናት። ኢትዮጵያውያን ቢርባቸው እንኳ ማንነታቸውን የማይጥሉ ብርቱዎች ናቸው የምንባል ሕዝቦች ነን። ስለዚህ እንናቅ የነበረው በስንዴ ነበር። ዛሬ ግን የአገር መሪ ስንዴ ማሳ ቆሞ ሲታይ አንዳች እልፍ ያለ ነገር እንዳለ ማስተዋል ትጀምሪያሽ። በስንዴ በኩል የተፈጠረብን ቀዳዳ እንደሚደፍን በልበ ሙሉነት መናገር ይቻላል።

ያ ሲሆን በእርግጠኝነት ያከብሩናል። ምክንያቱም ለልመና የምንዘረጋው እጅ ይታጠፋል። ወደ እርሻ እና ሌላ ስራ ይሄዳሉ። ስራ ስለሚያስተባብር ወደ አንድነትና ወደመጨባበጥ ይወስዳል። ስለዚህ እንድንበተን የሚያደርገን ስንዴ ማጣታችን ነው። ስንዴ እንዲኖረን መሪዎቹ እየሰሩ ያለው ስራ የሚያስገርም ነውና የስራው አድናቂ ብቻ ሳንሆን ተባባሪም ልንሆን ይገባል ባይ ነኝ።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ ወደጦርነት ሲወርዱ ተከትለዋቸው መስዋዕትነት የከፈሉ በርካታ የቀድሞ ሰራዊት አባላት አሉ። በየማስልጠኛው ገብተው የሰለጠኑ ከ400 በላይ የእኛ አባላት አሉ። ይህ የሚከፈለው መስዋዕትነት አገራችን ኢትዮጵያ ስለሆነች ነው። እንዲያማ ባይሆን ኖሮ ጡረታ የተከለከልንም አካላት ነበርን። እንዲሁም ሕክምናም ጭምር ተከልክለናል ነበር ።

በእናት ኢትዮጵያ እንዴት ይኮረፋል? አሁን እኛ መለመኛችንን አሳልፈን የምንሰጥ አይደለንም። ምክንያቱም የአንድ ዘመን ጉዳይ በየቤተ ክርስትያኑና በየመስጂዱ ለማኞች አድርጎን ነበር። መለመን እንኳ የቻልነው ኢትዮጵያ ስለኖረች ነው። የቀድሞ የጦር ሰራዊት የወደቅነውም ኢትዮጵያ ስላለች ነው። ስለዚህ በምንም አይነት ሁኔታ መለመኛችንን አሳልፈን አንሰጥም። ከዚህም የተነሳ ነው ያለማቅማማት የቀድሞው ጦር ስለአገራችን ዘብ መቆም የምንፈልገው። ኢትዮጵያ ማለት እንዲህ ናት፤ እኛ የገባችን ኢትዮጵያ ይህች ናት። በዚህ ውሃ ልክ ላይ ያለ መንግስትና መሪ ያለን በመሆኑ በጣም ደስተኞች ነን። ከዚህም የተነሳ ይህን መንግስት በእጅጉ እንደግፈዋለን። ክፍተት ካለ ደግሞ እናሳያለን። የምንችለው ያህል ደግሞ ከጎኑ እንሆናለን።



**አዲስ ዘመን፡- የአገር መከላከያ ሰራዊትን ብቃት እንዴት ይገልጹታል?**

**ሃምሳ አለቃ ብርሃኑ፡-** እኔ በ14 ዓመት እድሜዬ ወታደር ስለነበርኩ የወታደርን ውጣ ውረድ የማወቀው አሳምሬ ነው። ገና ታዳጊ ህጻን ሳለሁ ነው ወታደር እንደምሆን ነፍሴ ሹክ ያለችኝ። ኢትዮጵያ እንዳትደፍርና ማንም እንዳይነካት ለኢትዮጵያ መስዋዕት መሆን እንዳለብኝ የነገረችኝ ነፍሴ ናት። ይህ በኢትዮጵያውያኑ ደም ውስጥ ያለ ማንነት ነው። በውትድርና ስራ ላይ መሰማራት የቻልኩት በዚህ የውስጥ ጥሪ ላይ ወታደራዊ ሳይንሱን ሰልጥኜ ነው።

አሁን ያለው ወጣት ለእኔ አስደማሚ ነው። ሕግ ማስከበርና የሕልውና ዘመቻው ላይ ወጣቶች በራሳቸው ፍላጎት ተነቃቅተው ሲሄዱ እኔ አልቅስ ነበር። በወቅቱም እድሉን አግኝቼ በየቀበሌው በመገኘት እሸኝ ነበር። ሲያስለቅሰኝ የነበረውም ለነጻነት ሲሉ ፊታቸው ላይ ያንን ቁርጠኝነት በማየቴ ነው። ይህ ነጻነት ፍለጋችን የማያቋረጥ ከአያት ቅድመ አያት የመጣ ትስስር መሆኑን ነው መረዳት የቻልኩት።

አሸባሪው ሲያስተዳድር የነበረው 27 ዓመት ያህል ነበር። በዚህ ጊዜ ውስጥ ሁሉ ኢትዮጵያዊነት ተቋርጧል ብዬ ተስፋ ቆርጬ ነበር። በኋላ ግን በኢትዮጵያ ጉዳይ ሲባል በሕወሓት ዘመን የተወለደው ልጅ ተነስቶ ሄዶ ለኢትዮጵያዊነት መፋለሙን ተመለከትኩ። በጣም ሲያደምመኝ የነበረው ጉዳይ የአገሬ ሰው በኢትዮጵያዊነት ላይ እንዲህ አንድ እንዲሆን ያደረገው ትስስር ምን ይሆን የሚል ነበር። እያንዳንዱ ወጣት ስሜቱ ፊቱ ላይ ሲንቦገቦግ ማየትና መስዋዕት ለመሆን ያለውን ፈቃደኝነት ማየት በራሱ የሚያኮራ እና የተሰጠን ማንነት እንደሆነ ነው መረዳት የቻልኩት።

ዛሬ የሚዋጋው ሰራዊት የዚህ የጀግና ሕዝብ ልጅ ክፋይ ነው። እንደ እድል ሆኖም ይህን ወጣት በሕግ ማስከበር ዘመቻው ላይ ተገኝቼ ማየት ችያለሁና የሚነበብባቸው የአገር ፍቅር ስሜት የሚጋባ አይነት ነው። ዘመኑ ደግሞ እኛ እንዳለንበት ሳይሆን የቴክኖሎጂ ዘመን ነው። ድሮ ድሮ ውጊያው ይካሄድ የነበረው ወታደር ተልኮ በቃኚ ነው። ዛሬ ደግሞ አብዛኛው ሒደት የሚከናወነው በቴክኖሎጂ ነው። ስለዚህ ይህ በቴክኖሎጂ የዘመነ አገር መከላከያ ሰራዊት ስላለን ጠላቶቻችን ይህን ሰራዊት ሊገጥሙት በማያስችላቸው ቁመና ላይ ነው የሚገኘው። ስለዚህ ኢትዮጵያ እንኳን ገጥመዋት ለመግጠም የማያስቧት የብቃት መለኪያ የሆነ ሰራዊት ያላት ናትና ማንም አይሞክራትም።

**አዲስ ዘመን፡- በአሁኑ ወቅት ትህነግ ለሰላም ያለው እይታ የተንሸዋረረ ነው፤ ለዚህ ዘላቂ መፍትሄ ምንድን ነው ይላሉ?**

**ሃምሳ አለቃ ብርሃኑ፡-** እውነት ለመናገር የትህነግ ቁመና እና ማንነት ለሚገነዘበው ለእንደ እኔ አይነት ሰው ቡድኑ ሰላም ፈልጎ የቀረበለትን ጥያቄ ተቀብሎ ወደዚህ ድርድር ማብቂያ በተለይ ኢትዮጵያ የምታርፍበት፣ አሳዛኙ የትግራይ ሕዝብም እፎይ የሚልበት ቢሆን መልካም ነበር። የትግራይን አካባቢ አሳምሬ አውቀዋለሁ። እኔ ያደኩበት ማኅብረሰብ ነው። የአካባቢው እናቶች እየተደበቁ እያጎረሱኝ፣ ስቆስል ደሜን እያሰሩልኝ ያሳደጉኝ ናቸው።

እሱ ማኅበረሰብ በጣም ይናፍቀኛል፤ ሰላም በማጣት እየደረሰ ያለውን እንግልት ስመለከት የማዝነው በጣም ነው። ይሁንና የዚህ ሕዝብ መከራ ያብቃ ብሎ ትህነግ ደንታ ኖሮት በዚህ ድርድር መቋጫ እንዲገኝ ያደርጋል፤ ነገሮች በሰላም እንዲጠናቀቁ የበኩሉን ይወጣል ብዬ ተስፋ አላደርግም።

ከዛ በተረፈ ግን ዘላቂ መፍትሄ ለማምጣት የኢትዮጵያ መንግስት ማድረግ ያለበትን ምክረ ሐሳብ መለገስ እፈልጋለሁ። አንደኛው የቡድኑን ማንነት ይበልጥ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ማሳወቅ ተገቢ ነው። በእርግጥ ሕዝቡ የቡድኑን ማንነት ጣርማ በር ድረስ በመጣበት ጊዜ የተረዳው ጉዳይ ነው። የዚህ እኩይ ተግባር ባለቤት የሆነውን ቡድን ስራ ለትግራይ ሕዝብም ይበልጥ እንዲረዳ ማድረጉ መልካም ነው። በተለይ የዚህን ድርጅት እርቃን የሚያቀር ስራ መሰራት አለበት ባይ ነኝ።

ድርጅቱ የትኛውም ስፍራ ላይ ቀዳዳ ሊያገኝ አይገባውም። ለምሳሌ ብዙ ጊዜ ያለንበት ሁኔታ አገርና ሕዝብ ከሚለው በተሻለ ገንዘብ ወይም ሀብትና ስልጣን የሚሉ ነገሮች ይቀድማሉ። ቡድኑ ደግሞ ይህን የታጠቀ ቡድን ነው፤ ገንዘብ አለው። ስለዚህም በርካታ ነገሮችን ሊጋፈጥ የሚያስችል እድል ሊኖረው ይችላል፤ ስለዚህ እንዲህ አይነቱ ነገር እንዳይፈጠርና ያለውን ገንዘብ እንዳይጠቀም መዝጋት ያስፈልጋል።

ከዚህ ጎን ለጎን ደግሞ ኢትዮጵያዊነትን ለማጽናት መንግስት ብርቱ ስራ ይጠበቅበታል። ኢትዮጵያውያን ቡድንን ማብዛት ግድ ይለዋል። ከቀበሌ ጀምሮ ኢትዮጵያዊነት ላይ የሚያጠነጥኑ ጉዳዮችን ማብዛትም ያስፈልጋል። በእነዚህ ጉዳዮች ላይ ኢትዮጵያዊ ስነምግባርን የሚያስተምሩ ሰዎችን በጉዳዩ ተሳታፊ እንዲሆኑ ማድረግ መልካም ነው። ከዚህ አኳያ ትውልድን መግራት ይጠበቅብናል ብዬ አስባለሁ። ዝም ብለን የምንቀጥል ከሆነ ግን የጠበቅነው ያህል ኢትዮጵያዊነትን ማምጣት ይቸግረናል፡፤ በመሆኑም መንግስት እዚህ ላይ በብርቱ መስራት አለበት ብዬ አስባለሁ።

በዲፕሎማሲው መስክም በይበልጥ ጠንክሮ መሄድ አለበት ብዬ አምናለሁ። ኢትዮጵያ በርካታ ወጣቶች ያሏት አገር ናት፤ ከዚህ አንጻር እነዚህን ወጣቶች በዲፕሎማሲው መስመር እንዲሳተፉ ማድረግ ተገቢ ነው። የኢትዮጵያን ማንነት የሚገልጹና የውጭ ዓላማም ላይ ተጽዕኖ ማሳረፍ የሚችሉ አንደበተ ርዕቱና ባለአዕምሮ ወጣቶችን በዘርፉ አብቅቶ ማሰማራት ያስፈልጋል። በዚህ ላይ የኢፌዴሪ የውጭ ጉዳዩ በትኩረት መስራት አለበት ብዬ አስባለሁ። ከዚህ አንጻር እንዲህ አይነት ስምሪት ካለ የኢትዮጵያ ጉዳይ በአግባቡ እያሳወቁ የሚሄዱ ኃይሎች እየበዙ ይሄዳሉ። በዚህም የቡዱኑን እኩይ ተግባር መግለጽ ይችላሉ። እኩይ ተግባሩን እየገለጡ ሲሄዱ የተሻለ ነገር መምጣት ይችላል።

ዘላቂ ሰላም ለማምጣት ትውልዱ ላይ መስራት አዋጭ ነው። አዲሱን ትውልድ ከዚህ አይነት ጉዳይ ማዳን አለብን። ኢትዮጵያን የሚወድ ሰው በየቤቱ ያለው ልጅ ላይ መልካምነትን መዝራት አለበት። ቤተሰብ ለልጁ የኢትዮጵያን ውሃ ልክ አሳይቶት ማለፍ አለበት። ቁሳቁስ ሌላ ጉዳይ ነውና ልጆቻችንን ኢትዮጵያዊ አድርገን ልንቀርጻቸው ይገባል። ይህን የምናደርግ ከሆነ ዘላቂ ሰላም እንዲመጣ ማድረግ እንችላለን። ካልሆነ ግን በዘመቻ መልክ ብቅ ብለን ወዲያው ጥፍት የምንል ከሆነ እኩይ ተግባር ተመልሶ ማቆጥቆጥ ይጀምራል።

ኢትዮጵያ የድል ዘመን አላት ብዬ አስባለሁ። ጥቅምት 24 የሁሉንም ኢትዮጵያውያዊ ልብ የሰበረ፣ መከላከያ ሰራዊታችን ከክህደት ጥቃት እራሱን ተቋቁሞ አንጸባራቂ በመጎናጸፍ ሀገርን የታደገበት ቀን ነው። የማንረሳው ሞቱን ብቻ ሳይሆን አንጸባራቂ ድሉን ጭምር ነው። አጼ ኃይለስላሴ በ1949 ዓ.ም አንድ ነገር መናገራቸውን ከአንድ መጽሐፍ ላይ ማንበብ ችያለሁ። አባባሉም “ሲታገሉ መውደቅ ያለ ነው፤ ነገር ግን ከወደቁበት ተነስተው የጣለን ጠላት መጣል እሱ ትልቅ ነገር ነው” የሚል ነው። መከላከያችንም ይህን ነው ያደረገው። የጣለውን ጠላት ጥሎ አይተነዋል። ኢትዮጵያ እንዲህ ናት፤ ሰራዊታችን በየትኛውም ዘመን የሚከበርና ድል አድራጊ ሰራዊት ነው። አሁንም እኛ በኢትዮጵያ ውሃ ልክ ላይ ያለን እስከሆንን ድረስ የትኛውም ኃይል ይገጥመን አሸናፊዎች እኛ ኢትዮጵያውያን ነን።

**አዲስ ዘመን፡- ስለሰጡን ማብራሪያ ከልብ አመሰግናለሁ።**

**ሃምሳ አለቃ ብርሃኑ፡-** እኔም አመሰግናለሁ።

# የኢንቨስትመንት ዘርፉንም የጎዳው የክህደት ጥቃት

አንተነህ ቸሬ

የዛሬ ሁለት አመት በዛሬው ቀን፤ ጥቅምት 24 ቀን 2013 ዓ.ም። ይህ ቀን የኢትዮጵያ ጠላት ሆኖ ከሩብ ክፍለ ዘመን በላይ ኢትዮጵያን የገዛው አሸባሪው ሕወሓት የኢትዮጵያን፣ በተለይም የትግራይን፣ ሕዝብ ከጠላት በሚጠብቀውና ለትግራይ ሕዝብ ብዙ ውለታ ባኖረው የሀገር መከላከያ ሰራዊት የሰሜን ዕዝ ላይ ጥቃት ሰንዝሮ ታሪክ ይቅር የማይለውን ዋነኛ ክህደት የፈጸመበት ነው። በዚህ የክህደት ተግባር በርካታ የመከላከያ ሰራዊት አባላት በአሸባሪው ሕወሓት ተጨፍጭፈዋል፤ በርካታ የሚሆኑት ደግሞ በጠላት ላይ ጭምር ሊፈጸም ይችላል ተብሎ የማይታሰብ ግፍ ተፈጽሞባቸዋል።

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ መንግስት በዚህ ከሀዲ ቡድን ላይ ባካሄደው የሕግ ማስከበር እርምጃ ከሀዲ ቡድኑ ኢትዮጵያን ለማፈራረስ ያሰለፈው ሰብዓዊና ቁሳዊ አቅም በጥቂት ቀናት ውስጥ ተሰባብሮ መላ ትግራይን በመቆጣጠር የሀገርን ሉዓላዊነት ማስጠበቅ ቢቻልም፣ ቡድኑ ያ ሁሉ ቅጣት ደርሶበትም ከጥፋቱ ሊማር አልቻለም።

መንግሥት በሰኔ ወር 2013 ዓ.ም የተናጠል ተኩስ አቁም አድርጎ የሀገር መከላከያ ሰራዊትን ከትግራይ ማስወጣቱን ተከትሎ አሸባሪ ቡድኑ አጋጣሚውን ለጥፋት ተግባር በማዋል ታሪካዊ የኢትዮጵያ ጠላትነቱን በአማራና አፋር ክልሎች ላይ ባካሄደው ወረራ ደግሞታል። በዚህም ወረራም በሰሜን እዝ ላይ ክህደት በመፈጸም የሀገር ባለውለታዎቹን የቁርጥ ቀን ልጆች እንደጨፈጨፈው ሁሉ በአማራና አፋር ክልልም ንጹኃንን በአሰቃቂ ሁኔታ ጨፍጭፏል፤ አያሌ ሰዎችን ከቀዬቸው አፈናቅሏል፤ ታጣቂዎቹ ያደረሱት ዘግናኝ አስገድዶ መድፈርና የስነ ልቦና ቀውስም ተዘርዝሮ የሚያልቅ አይደለም። የህዝቡን ሀብትና ንብረት ዘርፏል፤ አውድሟል። በቅርቡም ሌላ ሶስተኛ ዙር ጦርነት ቢከፍትም፣ በጥምር ጦር በሚገባ እየተመከተ ይገኛል።

### የፀጥታ መደፍረስ፣ ዘረፋና ውድመት

በሕግ ማስከበርና በህልውና ዘመቻዎቹ ወቅት አሸባሪው ሕወሓት የመከላከያ ሰራዊቱን ጥቃት መቋቋም ሲያቅተው በብዙ ገንዘብና እውቀት የተገነቡ የኢንቨስትመንትና ሌሎች የመሰረተ ልማት ተቋማትንም አውድሟል። ቡድኑ ጥቅምት 24 ቀን 2013 ዓ.ም. በመከላከያ ሰራዊት የሰሜን እዝ ላይ ክህደት ከፈጸመ አንስቶ የአማራና አፋር ክልሎችን በወረረበት ወቅት ከፍተኛ ዘረፋና ውድመት ከፈጸመባቸው ዘርፎች መካከል አንዱ የኢንቨስትመት ዘርፉ ነው። ቡድኑ በኢንቨስትመንት ተቋማት ላይ የፈፀመው አሳፋሪ ዝርፊያና ውድመት፣ የሕወሓት ወዳጅ ዓለም አቀፍ ተቋማትና የአንዳንድ ምእራባውያን ሀገሮች መንግሥታትና ተቋማት ጫና የኢንቨስትመንት ተቋማት ጉዳት እንዲደርስባቸውና ዘርፉ እንዲቀዛቀዝ አስገድደዋል።

በዚህ በተጠናና በባለሙያ በተደገፈ ዘረፋና ውድመት ሀገርና ባለሀብቶች እንደ አይናቸው ብሌን የሚመለከቷቸው፣ በእጅጉ ተስፋ የተሰነቀባቸው፣ የብዙ ሺዎች እንጀራ የሚጋገርባቸውና እጣ ፈንታቸው የተሳሰረባቸው የመንግስትና የባለሀብቶች የኢንቨስትመንት ተቋማት ተዘርፈዋል፤ እንዲወድሙ ተደርገዋል።

የቡድኑ የዘረፋና የውድመት ድርጊት ሆን ተብሎ የታቀደበትና ሕዝብን ለመጉዳት ያለመ እንደሆነ በርካታ ማስረጃዎችን ማቅረብ ይቻላል። በጦርነቱ ላይ ተሳታፊ ያልሆኑ እናቶችና ህፃናት አገልግሎት የሚያገኙባቸውን የውሃ፣ የጤናና የትምህርት ተቋማትን ማውደም ሕዝብን የመጉዳት ዓላማ እንጂ ሌላ ምን ሊባል አይችልም፤ ሌሎች አሰቃቂና አሳፋሪ ድርጊቶቹን ለመዘርዘር ጊዜና ቦታም አይበቃም።

የአማራ ክልል መንግሥት በቅርቡ ይፋ ያደረገው ጥናት እንዳመለከተው፤ ሕወሓት ከሰኔ 2013 እስከ ታኅሳስ 2014 ዓ.ም በክልሉ 292 ቢሊዮን ብር የሚገመት ንብረት አውድሟል። ቡድኑ ከአንድ ዓመት በላይ በወረራ ይዟቸው በነበሩት እንዲሁም ለሦስተኛ ጊዜ ወረራ በፈፀመባቸው የክልሉ አካባቢዎች የፈፀመው ውድመት ሲታሰብ በክልሉ ያደረሰው ዘረፋና ውድመት መጠን ከተጠቀሰው የበለጠ ሊሆን እንደሚችል ይገመታል።

ዝርፊያና ውድመት ከተፈፀመባቸው ተቋማት መካከል የማምረቻ ድርጅቶች ተጠቃሽ ናቸው። ለአብነት ያህል በደሴና በኮምቦልቻ ከተሞች በርካታ



በአሻባሪው ሕወሓት የክህደት ተግባር የኮምቦልቻ ኢንዱስትሪ ፓርክም ከፍተኛ ጉዳት ደርሶበታል

ፋብሪካዎች ዘረፋና ውድመት የተፈፀመባቸው ሲሆን፣ በእነዚህ ፋብሪካዎች ውስጥ ይሰሩ የነበሩ ሰራተኞችና ቤተሰቦቻቸው ለኢኮኖሚያዊና ለስነ ልቦና ችግር መዳረጋቸውን እንዲሁም አስር ፋብሪካዎች ከፍተኛ ውድመት እንደደረሰባቸው መረጃዎች ያመለክታሉ።

በተለይም ቡድኑ በርካታ የውጭ ሀገራት ኩባንያዎች በሚገኙበት የኮምቦልቻ ኢንዱስትሪ ፓርክ የፈፀመው ዘረፋና ውድመት ትልቅ አቅም ባላቸው የፓርኩ ኩባንያዎች ላይ ካስከተለው ኪሳራ በተጨማሪ በሀገሪቱ የውጭ ምንዛሬ ግኝት ላይም ከፍተኛ ጫና አሳድሯል። የኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን ይፋ ባደረገው መረጃ፣ የኮምቦልቻ ኢንዱስትሪ ፓርክ የአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫዎች፣ የማምረቻ ቦታዎች፣ የኬሚካል ማጣሪያ እና ሌሎች በፓርኩ ውስጥ አገልግሎት ይሰጡ የነበሩ ክፍሎች በሙሉ ዝርፊያና ውድመት ደርሶባቸዋል።

በኢንዱስትሪ ፓርኩ ውስጥ ያሉ ድርጅቶች ተሽከርካሪዎችም በአሸባሪው ሕወሓት ታጣቂዎች ተወስደዋል። የፓርኩ የቢሮ እቃዎችና የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሲስተሞች፣ የአምራች ኩባንያዎች ቢሮዎችና ቁሳቁስ፣ ለውጭ ገበያ የተዘጋጁ የጨርቃ ጨርቅ አልባሳትና የቆዳ ውጤቶች ተዘርፈዋል። በተጨማሪም የምርት ማከማቻ መጋዘኖች ውስጥ የነበሩ ለምርት የተዘጋጁ ጥሬ እቃዎች፣ የተለያዩ ተሽከርካሪዎች እንዲሁም አምቡላንስ እና የእሳት አደጋ ተሽከርካሪዎችን ጨምሮ ሌሎች በፓርኩ ውስጥ የሚገኙ ቁሳቁስ ዝርፊያና ውድመት ደርሶባቸዋል።

በኮምቦልቻ ኢንዱስትሪ ፓርክ ላይ የደረሰው ጉዳት በሁለት መንገድ የሚገለጽ እንደሆነ ያመላከተው የኮርፖሬሽኑ መረጃ፣ የመጀመሪያው ዝርፊያ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ውድመት ነው። ከዝርፊያው አንጻር ድርጅቶቹ ያመረቷቸውና ወደ ውጭ ሊላኩ የነበሩ ምርቶች ተዘርፈዋል፤ የኩባንያዎቹን ምርቶች ለማምረት ጥቅም ላይ የሚውሉ ጥሬ እቃዎች ሙሉ በሙሉ ተወስደዋል፤ በድርጅቶቹ ቢሮዎች ውስጥ የነበሩ መገልገያዎች ሙሉ በሙሉ በሚባል ደረጃ ተዘርፈዋል። በተለይ ደግሞ በቀላሉ ሊተኩ የማይችሉ መሳሪያዎችና የምርት ሥርዓቶች ሙሉ በሙሉ ወድመዋል።

በፓርኩ ውስጥ በሚሰሩ ድርጅቶች ላይ ከደረሰው ጉዳት በተጨማሪ የቢሮ እንዲሁም የአገልግሎት መስጫ መሳሪያዎች ውድመትና ስርቆት ተፈፅሞባቸዋል። የኢንዱስትሪያል ፓርኩ ማጣሪያዎች ተነቅለው ተወስደዋል። ሊወሰዱ ያልቻሉት ደግሞ እንዲወድሙና እንዲቃጠሉ ተደርገዋል። የደኅንነት መጠበቂያ መሳሪያዎችም ጭምር ወድመዋል። የኤሌክትሪክ እና ሌሎች ገመዶች አገልግሎት እንዳይሰጡ ተደርገው ተቆራርጠዋል። ለፓርኩ ተጨማሪ ግንባታ ለማድረግ እንደ መጋዘን ሲያገለግሉ የነበሩ ሦስት ኮንቴይነሮች ተጭነው ተወስደዋል።

የአማራ ክልል መንግሥት እንዳስታወቀው፣ በክልሉ የነበረው የተሻለ የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴ በአሸባሪው ሕወሓት ወረራ ክፉኛ ተጎድቷል። አሸባሪው ሕወሓት በክልሉ ላይ ወረራ በፈፀሙት ወቅት በኢንቨስትመንት ተግባራት ላይ ተሰማርተው የነበሩ በርካታ ባለሀብቶች ዘረፋና ውድመት የደረሰባቸው በመሆኑ አካባቢውን ለቀው እስከ መውጣት ደርሰዋል። ውድመት ባልደረሰባቸው ቦታዎችም የስነ-ልቦና ችግሮችን አስከትሏል።

በሕወሓት ጥቃትና ወረራ ምክንያት የተከሰተው የሰላምና ፀጥታ መደፍረስ ከፍተኛ የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴ በሚከናወኑባቸው ኢንዱስትሪ ፓርኮች አፈፃፀም ላይም ከፍተኛ አሉታዊ ተፅዕኖ አሳድሯል። የኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን መረጃዎች እንደሚሳዩት፣ የፀጥታ መደፍረሱ በፓርኮቹ ውስጥ የነበሩ ትልልቅ አምራች ድርጅቶችን ትልቅ ጫና ውስጥ አስገብቷቸዋል። አለመረጋጋቱን ተከትሎ የመጣው የውጭ መገናኛ ብዙኃን እንዲሁም የዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ ዘመቻና ጫና አምራች ድርጅቶች ተረጋግተው እንዳይሰሩና አዳዲስ ኢንቨስትመንቶች በቀላሉ ወደ ኢትዮጵያ እንዳይመጡ ተፅዕኖ አሳድሯል። በተጨማሪም ኤምባሲዎች ዜጎቻቸው ከኢትዮጵያ እንዲወጡ ከፍተኛ ግፊት ሲያደርጉ ስለነበር አምራቾች በጫና ውስጥ ሆነው ለመስራት ተገድደውም ነበር።

በኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥ የሚሰሩና ምርቶቻቸውን ለዓለም አቀፍ ገበያዎች የሚያቀርቡ ኩባንያዎች ምርቶቻቸውን በረጅም ጊዜ የግዥ ውል ለገዢዎች ስለሚያቀርቡ ምርቶቻቸውን በሌሎች ሀገራት ወደሚገኙ ቅርንጫፍ ማምረቻዎች እንዲያዞሩ ጫናዎች ነበሩባቸው፤ ገዢዎችም ይሰርዙባቸው ነበር።

ሕወሓት በኢንቨስትመንት ተቋማት ላይ ያደረሰው ውድመት በተቋማቱ ውድመት ብቻ የሚለካና የሚገለፅ አይደለም። የተቋማቱ መውደምና መዘረፍ የችግሩ አንዱ መገለጫ ከመሆኑ ባሻገር ውድመቱንና ዝርፊያውን ተከትለው የተከሰቱት ውጤቶች በኢንቨስትመንቱ ዘርፍ ላይ ተራዛሚና አሉታዊ ተፅዕኖዎችን የሚያስከትሉ ናቸው። በኢንቨስትመንት ተቋማት ላይ የደረሰው ጉዳት ካስከተላቸው ችግሮች መካከል የሰራተኞች ከስራ መፈናቀል፣ የምርት አገልግሎትና አቅርቦት መቋረጥ፣ የምርት ሽያጭ ገቢ መቀነስ፣ የስነ ልቦና ጫናዎችና ሌሎች ቀጥተኛ ችግሮች ተጠቃሽ ናቸው። በተጨማሪ ዘረፋውና ውድመቱ ካስከተላቸው ቀጥተኛና ፈጣን ውጤቶች ባሻገር ተጨማሪ ኢንቨስትመንት ወደ ኢትዮጵያ እንዳይመጣ እንቅፋት ሆኗል።

ቡድኑ በህልውና ዘመቻው ድል መደረጉን ተከትሎ የወጡ ሌሎች መረጃዎች እንደሚያመለክቱት፤ አሸባሪ ሕወሓት በኮምቦልቻ ኢንዱስትሪ ፓርክ ላይ ብቻ አይደለም ዘረፋና ውድመት ያደረሰው። በተለይ ከኢንዱስትሪ ፓርኩ ውጭ በሚገኙ ሌሎች ኢንዱስትሪዎችና ሆቴሎች ላይም ጭምር ነው። በዚህም በርካታ የኢንቨስትመንት ተቋማት ምርቶቻቸውን ግብአቶቻቸውን፣ ተሽከርካሪዎቻቸውን በቡድኑ ተዘርፈዋል፤ ቡድኑ የዘረፈውን እየዘረፈ የተቀሩትን ደግሞ አውድሟል፤ አዳዲስ የኢንቨስትመንት ተቋማት ጭምር የዚህ ግፍ ሰለባ ተደርገዋል።

### የዓለም አቀፍ ሚዲያዎችና ተቋማት ጫና

አሸባሪው ሕወሓት ብቻውን የሚንቀሳቀስ አይደለም፤ የኢትዮጵያ ታሪካዊ ጠላቶች ተላላኪ ሆኖም ነው የሚሰራው። በትግራይ ክልል የሕግ ማስከበር እርምጃ ማካሄድ ከተጀመረ አንስቶም ብዙዎቹ ዓለም አቀፍ (የውጭ) መገናኛ ብዙኃንና ዓለም አቀፍ ተቋማት ዘዋሪ የሆኑት እነዚህ የኢትዮጵያ ጠላቶች ስለህግ ማስከበር ዘመቻው፣ ስለሰብዓዊ አቅርቦቱና ስለመሳሰሉት የሚያሰራጩት ዘገባ በእውነተኛ መረጃ ላይ ያልተመሰረተ፣ ነባራዊ ሁኔታዎችን ከግምት ውስጥ ያላስገባና ተገቢ ያልሆነ፣ ፍጹም ለአሸባሪ ቡድኑ የወገነ፣ ፀረ-ኢትዮጵያ ይዘት የነበረው ነው። ይህም ዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ ስለጉዳዩ የተሳሳተ ግንዛቤ እንዲይዝ (እንዲኖረው) ከማድረጉ ባሻገር የኢትዮጵያ ጠላቶች «ኢትዮጵያን ለመበታተን ከዚህ የተሻለ ጊዜ/ እድል አናገኝም» ብለው ታጥቀው እንዲነሱና በረጅም ጊዜ ታሪኳ ከጦርነት ይልቅ ሰላምን፤ ከኃይል ይልቅ ንግግርን ለማስቀደም እንዲሁም ዓለም አቀፋዊ ትብብርንና ወንድማማችነትን የሚያሰፍኑ አህጉር አቀፍና ዓለም አቀፍ ተቋማት እንዲመሰረቱና እንዲጠነክሩ ባላት ቁርጠኛ አቋም የምትታወቀው ኢትዮጵያ ስሟ እንዲጠለሽ በር ከፍቷል።

የቀድሞ ወዳጃቸውን የከሃዲውን የሕወሓትን የቁልቁለት ጉዞ አምኖ መቀበል ያቃታቸው አንዳንድ ምዕራባውያን መንግሥታት፣ ዓለም አቀፍ መገናኛ ብዙኃን፣ ጋዜጠኞች፣ ተንታኝ እና የሰብዓዊ መብት ተሟጋች ተብዬዎች በኢትዮጵያ ላይ የከፈቱት አፍራሽ ዘመቻ ዛሬም ድረስ ቀጥሏል። «ውሻ በበላበት ይጮሃል» እንዲሉ ሕወ.ሓ.ት የኢትዮጵያ አድራጊ ፈጣሪ በሆነበት ወቅት የኢትዮጵያን ሐብት እንዳሻቸው እንዲዘርፉት የፈቀደላቸውና ከኢትዮጵያ ሕዝብ ከዘረፈው ገንዘብ እየመዠረጠ ያጎረሳቸው መንግሥታት፣ ድርጅቶችና ግለሰቦች [ውለታቸውን ለመመለስ አልያም ወዳጃቸውን ከሞት አስነስተው በድጋሚ ኢትዮጵያን ለመዝረፍ በማሰብ] ሐሰተኛና የጥላቻ መረጃዎችን፣ ወገንተኛ መግለጫዎችን እንዲሁም አሳፋሪ የክህደት ሪፖርቶችን ሲያወጡና ሲያሰራጩ እንደነበር ይታወሳል።

ሕወሓት በተለያዩ ዓለም አቀፍ ተቋማት ውስጥ ባሉ አጋሮቹ በኩል አገሪቱ ልትበታተን እንደሆነና የፌዴራሉ መንግሥት በትግራይ ሕዝብ ላይ ጦርነት እንዳወጀ አስመስሎ በርካታ የውሸት መረጃዎች እንዲሰራጩ አድርጓል። እነዚህን መረጃዎች ያዳመጡና የተመለከቱ ብዙ የውጭ አገራት ሰዎችና ዓለም አቀፍ ተቋማት ደግሞ መረጃዎቹን እንደወረዱ በመቀበል ከእውነት የራቀ ድምዳሜ ላይ ሲደርሱ ተስተውለዋል። ቡድኑ ስለሕግ ማስከበር እርምጃው የተዛባ መረጃ ሲያስተላልፍና በኢትዮጵያ መንግሥት ላይ ጫና ሲፈጥርም ነበር። እነዚህ ሁሉ የሐሰት ውንጀላዎች በኢንቨስትመንት ዘርፉ ላይ ቀላል የማይባል ተፅዕኖ አሳርፈዋል።

የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን በ2014 በጀት ዓመት ያከናወናቸውን ዋና ዋና ተግባራትና የተገኙ ውጤቶችን አስመልክቶ ይፋ ባደረገው መረጃ፣ ከጦርነቱ ጋር ተያያዥነት ያላቸው የኢትዮጵያ ከአጎዋ መታገድ እና የዓለም አቀፍ ሚዲያዎች ጫና በበጀት ዓመቱ ካጋጠሙ የኢንቨስትመንት ዘርፉ ተግዳሮቶች መካከል እንደሚጠቀሱ አመልክቷል። በ2014 በጀት አመት ከሦስት ነጥብ ሦስት ቢሊዮን ዶላር በላይ የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት መሳብ ቢቻልም ማሳካት የተቻለው የዕቅዱን 64 ነጥብ አራት በመቶ ብቻ ነው። በሀገሪቱ በነበረው አለመረጋጋትና የዓለም አቀፍ መገናኛ ብዙኃን በአፈፃፀሙ ላይ ተፅዕኖ ማሳደራቸውን የኮሚሽኑ መረጃ ያሳያል።

የሕወሓት የክህደት ተግባር ኢትዮጵያ አሜሪካ ከሰሃራ በታች ላሉ የአፍሪካ ሀገራት ከሰጠችው ነፃ የንግድ እድል /አጎዋ/ ተጠቃሚነት እንድትታገድ አድርጓታል። ባለፈው ዓመት የአሜሪካ መንግሥት ባሳደረው ፖለቲካዊ ጫና ምክንያት ነው ኢትዮጵያ ከዚህ ነፃ የንግድ እድል ተጠቃሚነቷ የታገደችው። ከ2014 በጀት አመት የኢንቨስትመንት ዘርፍ ተግዳሮቶች መካከል አንዱ ሆኖ የተጠቀሰውም ይኸው የኢትዮጵያ ከ«አጎዋ» ተጠቃሚነቷ የመታገዷ ጉዳይ ነው።

ኮሽታ የሚያስበረግገው ኢንቨስትመንት በአጠቃላይ የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት በተለይ በአሸባሪው ሕወሓት የክህደት ተግባር በአያሌው ተጎድቷል። ቡድኑ የኢትዮጵያን ኢኮኖሚ ለማዳከም አጥብቆ የሚሰራ እንደመሆኑ የሀገሪቱን ኢኮኖሚ ለማሳደግ ጉልህ ሚና ይኖራቸዋል ተብለው በታመነባቸው በእነዚህ ኢንቨስትመንት ተቋማት ላይ አቅዶና በቂ ዝግጅት አድርጎ ያደረሳቸው ጥፋቶች ሁነኛ ማሳያዎች ናቸው። ከላይ የተጠቀሱት ችግሮች ሁሉ መነሻቸው አሸባሪው ሕወሓት ጥቅምት 24 ቀን 2013 ዓ.ም የኢትዮጵያን፣ በተለይም የትግራይን፣ ሕዝብ ከጠላት ሲጠብቅና ለትግራይ ሕዝብ ብዙ ውለታ ሲውል በነበረው የሀገር መከላከያ ሰራዊት ሰሜን ዕዝ ላይ የፈፀመው እጅግ አስነዋሪና አሳፋሪ የክህደት ጥቃት ነው! ይህ ግፍ በኢትዮጵያውያን ላይ መጥፎ ጠባሳ አሳርፎ አልፏል፤ የግፉ ሰለባዎች ጀግኖች ኢትዮጵያውያን ግን ሁሌም ይታወሳሉ።

# በድሎ ካሱኝ፤ እሾህ ይዞ እጄን ዳብሱኝ

**ሙሉቀን ታደገ**

ከቅርብ ወራት ወዲህ ወፈፌው ይልቃል እንደዚህ ቀደሙ በየቀኑ ሌሊት ሌሊት እየተነሳ መጮሁን አቁሟል። ወትሮ ሰማይ የአህያ ሆድ ሲመስል መጮህ የጀመረ የሚያቆመው ማታ የሌሊት ወፎች ከዋሻቸው ወጥተው ውር ውር ማለት ሲጀምሩ ነበር። አሁን ላይ ግን ዋርካው ስር ከሚገኘው ድንጋይ ላይ ቆሞ የሚጮኸው ለሰፋራችን ሰዎች መልዕክት ለማስተላለፍ ሲፈልግ ብቻ ነው። ጩኸቱም እንደዚህ ቀደሙ በወፈፌነት የሚታለፍ ባለመሆኑ፤ ሁሉም በምስራቋ ኮከብ የሚገኙ የእድራችን እና የሰፈራችን ሰዎች በጥሞና እየተከታተሉ በጭብጨባ ያጅቡታል።

ወፈፌው ይልቃል አዲሴ የዛሬውን ንግግሩን የጀመረው « በድሎ ካሱኝ ፣ እሾህ ይዞ እጄን ዳብሱኝ ፤ ምን የሚሉት እብሪት ነው? » በማለት ነበር። ነገር ግን የይልቃል አዲሴን ውስጠ ወይራ ንግግር የተረዳው አብሿሙ ክንፈ ጉደታ ሁሉም የሰፈራቸው ሰው አባባሉን እንዲረዳው መብራራት እንዳለበት ጠየቀ።

ወፈፌው ይልቃል አዲሴም በአብሿሙ ክንፈ ጉደታ ንግግር ተስማምቶ የተናገረውን አባባል በምሳሌ ለማስረዳት አስቦ ንግግሩን እንዲህ ሲል ቀጠለ.... የአንድን ገበሬ በሬ ጎረቤቱ ይሰርቀዋል። በሬውን የሰረቀው ጎረቤትም የጠፋውን በሬ አብሮ አፈላላጊ ሆኖ ቀረበ። በሬ የጠፋበት ሰውዬም በሬውን ቢፈለግ ቢያስፈልግ በሬውን የበላው ጅብ አልጮህ ይለዋል። ከቀናት በኋላ ግን በሬውን ጎረቤቱ እንደሰረቀው ይደርስበታል። ነገር ግን ምስክር ስለሌለው «በሬዬን መልስልኝ» ሳይል በውስጡ ስለበሬው ያወጣ ያወርድ ያዘ።

ይህ በእንዲህ እያለ አንድ ቀን ሌባው ጎረቤት በሬ የጠፋበትን ሰው «ጌታው እንደው ያ በሬ ጠፍቶ መቅረቱ ነው?» ሲል ይጠይቀዋል። በሬ የጠፋበትም ሰው ምን ቢል ጥሩ ነው? «ሌባው አብሮ እያፈላለገ እንዴት በሬው ይገኛል ብለህ ነው?» ሲል መለሰለት።

የባይደን አስተዳደር እና አንዳንድ ምዕራባውንም እኛን እርስ በርስ ካጣሉ በኋላ ራሳቸው አስታራቂ ሆነው ይመጡልሃል። የሰውዬውን በሬ ሰርቆ አብሮ እንደሚያፈልገው ሌባ ማለት ነው፤ ብሎ ይልቃል አዲሴ ንግግሩን ሳይጨርስ በሰፈራችን ተዋቂው የቅኔ መምህር የንታ (የኔታ) ፍሬው እንደሚፎክር ሰው ከተቀመጡበት ድንጋይ ላይ ተነስተው፤ የባይደን አስተዳደር እና አንዳንድ ምዕራባዊንም በምስራቋ ታላቅ ሀገር የሚገኙ እድሮችን እና ሰፈሮችን እንዲበጠበጡ እና ከእነአካቴውም እንዲጠፉ ለማድረግ የእረጅም ጊዜ እቅድ አውጥተው ሲሰሩ ኖረዋል። ለእዚህ እቅዳቸውም በሰብዓዊ እና በዴሞክራሲዊ መብቶች ሰበብ ከፍተኛ እረብጣ ገንዘብ መድበው ተመለከተናል በማለት ንግግራቸውን ጀመሩ።

ይህ የጥፋት እቅዳቸው እንዲሳካ ለእነአይተ ጭሬ ልድፋው የጥፋት እና እልቂት ተልዕኮ በመስጠት የእድራችን እና የሰፈራችንን ጠባቂ የሆነውን ቅራት በተኛበት እንዲጨፈጨፍ አይዞህ ግፋ በለው አሉ። «ለውሃቤ ዝናም፤ ማየ ከልእዎ .....ለዝናቡ ጌታ ውሃ ነሱት ወይም አባት ላም ይሰጣል ፤ ልጅ አጓት ይነሳል » እንዲሉ አባቶች፤ አይተ ጭሬ ልድፋውም ዘመዶች ስንት እና ስንት ውለታ የዋለውን ቅራት በተኛበት አረደው።

በአንዳንድ ምዕራባዊያን ግፋ በለው እየተባለ ቅራቶችን በተኙበት የጨፈጨፈው አይተ ጭሬ ልድፋው በጦርነቱ የሚያሸነፍ መስሎት «ጦርነት ባህላዊ ጨዋታችን ነው» በማለት ሲፈጠር ጫካ ይዟት የገባትን እና ለዓመታት ከጫካ ወጥታ የማታውቀውን፤ በሽረሪት ድር የተወረረችውን ከበሮ የሸረሪት ድሯን እንኳን ላራግፍ ሳይል በችኮላ አስረሽ ምችው! ይል ያዘ።

የንታ ፍሬው ንግግራቸውን ቀጠሉ... በቅራታችን ላይ የፈጸሙትን አስነዋሪ ጭፍጨፋ እንደ ጀግንነት ቆጥረውት «መብረቃዊ ጥቃት» አካሄድን ሲሉ ታበዩ። «ሕወሓት ቀሞት ውስተ እደ ልሳን .....በለፈለፉ በአፍ ይጠፉ » እንዲሉ ይህም የምስራቋን ኮከብ ሙሉ ህዝብ ክፉኛ አበሳጨ። የተቆጣው ህዝብም በተላላኪው አይተ ጭሬ ልድፋው ላይ ዘመተ። መብረቃዊ በሆነ በሁለት ሳምንትም የጸረ ማጥቃት ምላሽ አይተ ጭሬ ልድፋውን በዓለም ፊት አዋረዳቸው።

በምስራቋ ኮኮብ ህዝብ እና መንግስት ጀብዱ ወዳጆቻችን ሲደሰቱ ጠላቶቻችን ደግሞ ክፉኛ ተደናገጡ።



የባይደን አስተዳደር እና አንዳንድ ምዕራባዊንም አይተ ጭሬ ልድፋውን ከተቀበረበት በርሃ ለመመለስ በሰብዓዊ ድጋፍ ስም ያዙኝ ልቀቁኝ አሉ ። ለምስራቋ ኮኮብ መንግስት እና ቅራቶች እንዲሁም ህዝብ ያለስም ስም መስጠት ጀመሩ ።

በጭፍጨው ምንም እንዳልሰሩ እና የእነሱ እጅ እንደሌለበት አስመስለው በምስራቋ ኮኮብ በሚገኙ እድሮች እና ሰፈሮች ሰላም ማምጣት የሚቻለው የባይደን አስተዳደር እና አንዳንድ ምዕራባዊንም ከተሳተፉበት ብቻ ነው አሉ። ካልሆነ ግን ሰላም ማምጣት አይቻልም ። «ከምላሳችን ጸጉር ይነቀል ! » ሲሉ ተደመጡ። በሬ ሰርቆ አብሮ አፈላላጊ እንደሆነው ሌባ ማለት ይህ አይደል ?

እውነት ለመናገር ሰላም ለማምጣት በሚል አንዳንድ ምእራባዊን የገቡበት እድር እና ሰፈር ከመፍረስ ውጭ አንድም ቀን ህልውናውን ሲያስቀጥል ታይቶ አይታወቅወም። ይህ ደግሞ በተለያዩ ሃገራት የታየ ሃቅ ነው። ብለው ንግግራቸውን ጨርሰው ሲቀመጡ ከታዳሚው የሞቀ ጭብጨበ ተቸራቸው።

የየንታ ፍሬው ንግግር ሲያልቅ ወፈፌው ይልቃል አዲሴ ከቆመበት ቀጥሎ «በነገራችን ላይ አንዳንድ ምዕራባዊያን የምስራቋን ታላቅ ሀገር ለማፍረስ እና ለማተራመስ ቆርጠው ከተነሱ ውለው አድረዋል። በርካታ በደሎችን ፈጽመውባታል። ሁሉንም በደሎችን መቁጠር ሊያዳግተን ይችላል። ነገር ግን የተወሰኑትን በወፍ በረር ማየቱ ሳይሻል አይቀርም።» በማለት ጉሮሮውን እህ....እህ.. እያለ ጠራረገ ።

**ሴራ አንድ፡-** በአጼዎቹ ዘመን አንዱ የምስራቋ ኮኮብ ንጉስ ለጉብኝት ወደ አሜሪካ ተጋበዙ። በጉብኙቱም ንጉሱን ነጥብ ለማስጣል ተልዕኮ የተሰጣት ጋዜጠኛ በነጩ ቤተመንግስት ተዘጋጅታ ትጠባበቅ ነበር።

ንጉሱም አሜሪካ በገቡ ማግስት ለነጥብ ማስጣል የተዘጋጀችው ጋዜጠኛ ተልዕኮዋን ለማስፈጽም ንጉሱን ለቃለ መጠየቅ እንዲተባበሯት በአስተርጓሚያቸው በኩል ጠየቀች። ንጉሱም ለቃለ መጠይቁ ተባበሯት። ንጉሱ እና ጋዜጠኛዋ ቃለ ምልልስ የሚያደርጉበት ሰዓት ደርሶ ቃለ ምልልሱ ተጀመረ።

በቃለ ምልልሱ መካከል ጋዜጠኛዋ ሆነ ብላ «እርስዎ እኮ በነጩ ቤተ መንግስት የገቡ የመጀመሪያው ጥቁር መሪ ነዎት፤ በዚህ ምን ተሰማዎት? » ስትል ጠየቀቻቸው። ንጉሱም በንዴት ጡፈው «እንዴት እኔን ጥቁር ትያለሽ!? እኔ ጥቁር አይደለሁም ! የዘር ሃረጌ ከጠቢቡ ሰለሞን የሚመዘዝ የአይሁድ እንጂ !» ሲሉ መለሱ። ይች ንግግር ቀላል ልትመስለን ትችላለች። ነገር ግን በወቅቱ የአፍሪካ አባት እየተባሉ የሚሞካሹትን ንጉስን በመላ ጥቁር አፍሪካዊ እንዲወገዙ ለማድረግ ሆነ ተብሎ የተደረገ የአሜሪካኖች ወይም የምዕራባዊን ሴራ ነበር።

**ሴራ ሁለት፡-** ኒወዮርክ ታይምስ የተባለው ጋዜጣ ከላይ የተጠቀሱትን የምስራቋ ኮኮብ ንጉስ በአስር ዓመት ውስጥ ሁለት ጊዜ የዓለም ተጽዕኖ ፈጣሪ ሰው ብሎ መረጠ። ይህን ተከትሎ ምዕራባዊን የምስራቋን ታላቅ ሀገር ንጉስ እና ህዝቦቿን ለማጥፋት በዩኒቨርሲቲዎች ሁሉ ጥናት እስከማስጠናት ድረስ ተጓዙ። የዚህን እውነታ ማረጋገጥ ከፈለጋችሁ ዘ ላየን ኦፍ ጁዳ ኢን ዘኒው ወርልድ ( THE LION OF JUDAH IN THE NEW WORLD ) የሚለውን መጽሃፍ ተመለከቱ።

**ሴራ ሶስት፡-** የምስራቋ ታላቅ ሀገር በሶማሊያ በተወረረችበት ሰዓት የምስራቋ ኮኮብ የጦር መሳሪያ ለመግዛት ከአሜሪካ ጋር ተስማማች። የምስራቋ ኮኮብም ለአሜሪካ ረብጣ ዶላሮችን ከፈለች። ይሁን እንጂ አሜሪካ ለጦር መሳሪያ መግዣ የተሰጣትን ረብጣ ዶላር ወደ ካዝናዋ ካስገባች በኋላ ስምምነቱን ወደ ጎን ጥላ የጦር መሳሪያውን አልሰጥም አለች። ለመሳሪያ መግዣ የተከፈላትንም ገንዘብ በልታ ቀረች።

የዚህ ሴራ ዋና ዓላማ ሶማሊያ የከባድ ጦር መሳሪያ የበላይነት እንዲኖራት በማድረግ እና የምስራቋን ኮኮብ በከባድ መሳሪያ አረር አስበልቶ ለማፈራረስ ነበር። ነገር ግን የአሜሪካ እና ምዕራባዊያን ሴራ በምስራቋ ኮከብ ህዝብ እና መንግስት እልህ አስጨራሽ ትግል ሊከሽፍ ችሏል።

**ሴራ አራት፡-** ሌላው ግፍ ደግሞ አንዳንድ ምዕራባውያን ለምስራቋ ታላቅ ሀገር ካንሰር የሆኑ በርካታ የፖለቲካ ፓርቲዎችን እንደ አሜባ ተህዋሲን አብዝተው በመፈልፍል እና የብሔር ብሔረሰቦች መብት እስከመገንጠል የሚል በመርዝ የተጠቀለለ ኬክ በማብላት የምስራቋን ታላቅ ሀገር ለመበታተን አበክረው ሰርተዋል። ይህንን ለማሳካትም በነጻ የትምህርት እድል ስም የሰበሰቧቸውን የምስራቋን ታላቅ ሀገር ወጣቶች በገፍ ተጠቅመዋል።

ይህን የአንዳንድ ምዕራባውያንን ተልዕኮ የተቀበሉ የሀገራችን ልጆችም ከወጣትነት እስከ እርጅናቸው ድረስ ባሉበት ቆመው ይሄው ሀገራችን ይበጠብጧት ይዘዋል። ከእነኚህ መካከልም ኤይተ ጭሬ ልድፋው የሚመሩት የሽብር ቡድን አንዱ እና ዋነኛው ነው። ይህ ማለት ግን እነ ኤይተ ጭሬ ልድፋው የሚመሩት የሽብር ቡድን ብቻ ነው ማለት አይደለም።

በነገራችን ላይ የአይተ ጭሬ ልድፋው እና የአሜሪካ የረከሰ ጋብቻ «ሐንካስ በአግረ ዕውር ሖረ፤ ዕውርኒ በዐይነ ሐንካስ ነጸረ፤ ወበክሌሆሙ ወይንየ ተመዝበረ ...አንካሰው በዕውሩ ዐይን ሄደ ዕውሩም በአናካሰው ዐይን አየ ፣ በሁለቱም አታክለቴ ተመዘበረ» የሚለው አባባል በደንብ አድርጎ የሚወክለው ይመስለኛል።

ትህነግ እና ምዕራባውያን አትክልታችንን ለመመዘበር እያቦኩ እና እያነኮሩ ያሉት አንካሳ እና እውር ሃሳብ ይዘው ነው። የሚገርመው ደግሞ ራሳቸው ገድለውን፣ ራሳቸው አንሳቁለውን ሲያበቁ ተበድለናል ካሳ ክፈሉን ይሉናል። ብድሎ ካሱኝ፣ እሾህ ይዞ እጄን ዳብሱኝ !? ማለት ምን አይነት ትዕቢት ነው? እኛ የአባቶቻችን ልጆች ነን፤ ለባንዳዎች እና ለቀኝ ገዢዎች እጅ አንሰጥም። አታክልታችን አናስበላም።

በመጨረሻም አለ ወፈፌው ይልቃል አዲሴ .... ሰዎችን የሚገፋ እና ከእውነት በተቃራኒው የሚቆሙ ሰዎች የመጨረሻቸው መጨረሻ ውርደት እንደሚሆን አያጠራጥርም። ይሄን በአንድ በታላቋ የምስራቋ ሀገር ተረት ላሳያችሁ...

ከዕለታት አንድ ቀን አንድን ነብር አዳኞች ሊገድሉት ያሯሩጡታል። ነብሩም በጣም ይደክምና ሮጦ ማምለጥ እንደማይችል ይረዳል። በዚህ ወቅት ዙሪያውን ሲቃኝ አንድ ጉድጓድ የሚቆፍሩ ሽማግሌ ይመለከታል። ጉድጓድ ሲቆፍሩ የነበሩትን አባትም እንዲያድኑት ይማጸናቸዋል። ጉድጓድ እየቆፈሩ የነበሩት አባት ከቆዳ በተሰራ አቁማዳ (ጆንያ) ይደብቁታል።

ከተወሰኑ ደቂቃዎች በኋላም አዳኞችም ጉድጓድ የሚቆፍረው ሰው ጋር ይደርሳሉ። «አባቴ በዚህ የመጣውን ነብር አላዩም?» ሲሉም ይጠይቋቸዋል። አባትም «እየቆፈርኩ ስለነበር ቀና ብዬ አላየሁም »ሲሉ ይመልሳሉ።

አዳኞችም ሰውዬውን አምነው ነብሩን ፍለጋ ነብሩ ይሄድበታል ብለው ወደ ገመቱት አቅጣጫ ሮጡ። የአዳኞችን መራቅ የተመለከቱት አባት ነብሩን ከደበቁበት አወጥተው «አሁን አዳኞች ከዚህ ስለራቁ መሄድ ትችላለህ» ሲሉ ይነግሩታል።

ነብሩም አዛውንቱን የዋሉለትን ውለታ ከምንም ሳይቆጥር «እስካሁን እዚህ ደብቀህ ስላቆየኸኝ እርቦኛል። ስለሆነም አንተን እበላኻለሁ» ይላቸዋል።

አባትም «እንዴት እኔ ከገዳዮችህ ደብቄ ባተርፍ ልብላህ ትለኛለህ?» ሲሉ ይመልሱለታል። «የለም እዚህ በጆንያህ ለብዙ ሰዓታት ስላቆየኸኝ እርቦኛል። ስለሆነም እበላሃለሁ »ይላቸዋል።

አዛውንቱም እንስሳት ይጠሩና ይዳኙን እንጂ እንዴት ዝም ብለህ ትበላኛለህ አሉ። ነብሩም ለዳኝነት ይሻላሉ ያላቸውን የዱር እንስሳ ጠራ። ከተጠሩት ዳኞች መካከል አንዷ ቀበሮ ስትሆን ሌላኛዋ ደግሞ ጦጣ ነበረች።

ቀበሮ የተፈጠረውን ነገር አዳማጠች። ነገር ግን ትክክለኛውን ፍርድ ብትፈርድ ነበር ሊበላት ስለሆነ እስካሁን በአቁማዳዎት (በጆንያዎት) ደብቀው ስላቆዩት መበላት አለብዎት ብላ ፈረደች። አዛውንቱም በቀበሮ ፍርድ ስላልተስማሙ ወደ ሁለተኛዋ ዳኛ ጦጣ ሄዱ።

ጦጣም ነብሩ እና ሽማግሌው የተጣሉበትን ፍሬ ነገር ካዳመጠች በኋላ እኔ ፍርድ ለመስጠት ይመቸኝ ዘንድ ዛፍ ላይ መውጣት አለብኝ አለች። ሁለቱም ተሟጋቾች ተስማሙ። ጦጣም እንዴት ሆነህ ነበር ወደ አቁማዳቸው የገባኸው? ስትል ነብርን ጠየቀች። ነብርም ወደ አቆማዳው እንዴት እንደገባ ለማሳየት ወደ አቁማደው ገባ። ጦጣም ሰውዬውን አቁማደውን አፍ ይዞ ነብሩን እንዲያፍነው እና በያዙት ድሉ እንዲቀጠቅጡት ጠቆመቻቸው። አዛውንቱም የጦጣን ጥቆማ ተቀብለው ቶሎ ብለው ነብሩ ሳይወጣ የአቁማዳውን አፍ በእጃቸው ጠቅጥቀው ያዙት። በሌላኛው እጃቸው በያዙት ዱላ ደግሞ ጥሩ አድርገው ቀጠቀጡት። ነብሩም ሞተ። የግፈኞች የመጨረሻ የሚሆነውም ይሄው ነው፤ ተቀጥቅጦ መሞት።

«የሽብር ቡድኑ እና የጥፋት አጋሮቹም የመጨረሻ እጣ ፋንታቸው ተቀጥቅጦ መሞት መሆኑን መገንዘብ ይኖርብናል » ብሎ ንግግሩን ሲያጠቃልል ስብሰባውን የታደመው ሰው ወፈፌው ይልቃል አዲሴን በጭብጨባ ሸኘው።



በ(ጌታቸው በለጠ /ዳግላስ ጴጥሮስ)
gechoseni@gmail.com

የሥነ ጽሑፍና የኮሙዩኒኬሽን ባለሙያ ናቸው። የኢትዮጵያ ደራስያን ማኅበርን ለዘጠኝ ዓመታት ያህል በፕሬዚዳንትነት መርተዋል። ከ1977 ዓ.ም ጀምሮ በአዲስ ዘመንና የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ጋዜጣ፣ በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገራት ታትመው በሚሠራጩ የተለያዩ የኅትመት ውጤቶች ላይ (ዳግላስ ጴጥሮስ) በሚል የብዕር ስሙ በርካታ ጽሑፎችን አስነብበውናል። በግላቸው 12፣ ከሌሎች ጸሐፍት ጋር በርካታ መጻሕፍትን ለአንባብያን አቅርበዋል።

# “አልሞትኩም ብዬ አልዋሽም!”

**ጥቂት ስለ ርዕሱ፤**

ለዚህ ጽሑፍ የሰጠነው ርዕስ የተውሶ መሆኑን ከምሥጋና ጋር ቀድመን ለአንባብያን እናስታውቃለን። የተወሰደውም ከራስ ቢትወደድ መኮንን እንዳልካቸው (ከ1883 - 1956 ዓ.ም) “አልሞትኩም ብዬ አልዋሽም” የመጽሐፍ ርዕስ ነው። መጠነኛ ገጾች ያሉት ይህ ቤሳ ልቦለድ ታትሞ ለንባብ የበቃው በ1944 ዓ.ም ሲሆን ከሌሎች ሰባት ያህል ታሪኮች ጋር ተዳብሎም “አርሙኝ” በሚል ርዕስ ተደጋግሞ በመታተም ለንባብ የበቃ ተወዳጅ ታሪክ ነው።

የትረካው ዋና ይዘት የ1928 ዓ.ም የፋሽስት ወረራን ለመመከት ወደ ጦርነት ዘምቶ የነበረ አንድ ጀግና ኢትዮጵያዊ ወደ ድሉ መቃረቢያ ግድም ከፍ ያለ አካላዊ መስዋዕትነት ከፍሎና መላ ሰውነቱ በመርዝ ጋዝ እንዳልነበረ ሆኖ ወደ ቤቱ ሲመለስ ሚስቱ የፋሽስት መኮንን በመውደድ እንዴት እንደ ካደችው የሚተርክ ነው።

ይኼው የመጽሐፍ ታሪክ ወደ ባለ ሦስት ገቢር ተውኔት ተለውጦ የካቲት 11 ቀን 1952 ዓ.ም በዕለተ ዓርብ የየካቲት 12ን የሰማዕታት መታሰቢያ ምክንያት በማድረግ ከምሽቱ ሁለት ሰዓት ጀምሮ ግርማዊ ንጉሠ ነገሥትና ግርማዊት እቴጌ በክብር እንግድነት በተገኙበት በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ቴያትር (የዛሬው ብሔራዊ ቴያትር) ተመርቆ ለሕዝብ ዕይታ ቀርቦ የነበረ በትራጄዲ ዘውግ ሥር የሚመደብ ቴያትር ነው።

ደራሲው ራስ ቢትወደድ መኮንን እንዳልካቸው ሀገሪቱ ካፈራቻቸው ታላላቅ ልጆቿ መካከል አንዱ ሲሆኑ አርበኛ፣ በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ ሥልጣን የመጀመሪያው ጠቅላይ ሚኒስትር፣ ከንቲባ፣ አምባሳደር፣ የውጭ ጉዳይ ተደራዳሪ፣ የሕግ ምክር ቤት ፕሬዚዳንትና የበርካታ መጻሕፍት ደራሲ ነበሩ።

**ሕወሓት እየተወነበት ያለው ተመሳሳይ ርዕስ፤**

የዛሬው ጥቅምት 24 ቀን 2015 ዓ.ም አሸባሪው ትህነግ ፤ “አልሞትኩም ብዬ አልዋሽም” የሚለውን የልቦለድና የተውኔት ርዕስ ተውሶ “ምታ ነጋሪት፤ ክተት ሠራዊት” በማለት ጥቅምት 24 ቀን 2013 ዓ.ም የሰሜን ዕዝ መከላከያ ሠራዊታችንን ከድቶ ወደ አማራና አፋር ክልሎች ጀሌዎቹን ለወረራ ያዘመተበት ዕለት ነው። ካንዴም ሁለቴ የጀግናውን የመከላከያ ሠራዊትን ክንድ ቀምሶ ቅስሙ የተሰበረው ወራሪው ትህነግ “ካፈርኩ አይመልሰኝ” በሚል እብደትና እብሪት ለሦስተኛ ጊዜ ጦር ሰብቆ ከገባባቸው ክልሎች በምን ዓይነት አይቀጡ ቅጣት ዋጋውን አግኝቶ ወደ ኋላ እንዳፈገፈገና አሁን በምን ዓይነት አጣብቂኝ ውስጥ ገብቶ “በነፍስ ውጭ፤ ነፍስ ግቢ” ትንቅንቅ ላይ እንደሚገኝም የምንሰማውና የምናየው ነው።

ጥቂት የቃላት ማሻሻያ የተደረገበት የሚከተለው ሕዝባዊ የሁለት ስንኝ ግጥም ከላይ የጠቀስነውን ሃሳብ በሚገባ የሚወክል ስለመሰለን እነሆ ልናስታውሰው ግድ ሆኗል፤

**“አንተ ጩካኝ ፈሪ ጩካኝ አዘዘብህ፣**
**እንደ ገና ዳቦ እሳት ነደደብህ።”**

እርጅና ጉልበቱን የጫነባቸው ጥቂት የሕወሓት መሪዎች ዓይን እያላቸው የማያዩ፣ ጆሮ እያላቸው የማይሰሙና ልባቸውና መንፈሳቸው በትዕቢት ታጅሎ የወፈረና የሰባ መሆኑ ተደጋግሞ በእኩይ ድርጊታቸው ማሳያነት እውነቱ በግላጭ ሲገለጥ ኖሯል። አካላቸው ብቻም ሳይሆን አስተሳሰባቸው ጭምር የጃጀው እነዚህ መሪ ተብዬዎች የትግራይ ወጣቶችን በጭካኔ ሲያስፈጁና ሕዝቡን ለመከራ ሲዳርጉ አንዳችም የኅሊና ወቀሳ የሚሉት ሰብዓዊ ባህርይ የሚስተዋልባቸው አይመስልም። ይህ ቀን የእብሪት ወረራቸው የተጀመረበት ዕለት ነበር ከማለት ይልቅ “የሙት ዓመት የቁም ዝክራቸውን” ዋንጫ መጎንጨት የጀመሩበት ዕለት ነበር ማለቱ ይቀላል።

እንዴት? ቢሉ “የቀብራቸው ግባ መሬት” የተጀመረው ልክ የጅብደኝነት ወረራ በጀግናው የመከላከያ ሠራዊትና በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ለመፈጸም “ሀ” ባሉበት ዕለት ስለሆነ ነው። የወረራቸውን ፊሽካ የነፉትም “አልሞትኩም ብዬ አልዋሽም” እንዲሉ የሞታቸውን ከፈን መከናነባቸው እንደማይቀር እያመኑ ነበር።

በዘመነ ደርግ “ገንጣይና አስገንጣይ” እየተባለ በመወገዝ ከቀድሞ የሀገሪቱ ሠራዊት ጋር ለዓመታት በጦር ሜዳ የተፋለመውን ይህንን የባሩድ ሱሰኛ ቡድን ብልሁ የሰሜን አርሶ አደር የገለጸበትን አንድ ታሪክ እናስታውስ። ለገለጻው ማነጻጸሪያነት የተጠቀመው በአካባቢው የመንገድ ኮንስትራክሽን ላይ ይከወን የነበረን አንድ አጋጣሚ መነሻ በማድረግ ነበር።

የመንገዱን ግንባታ ያከናውኑ የነበሩት የአውራ ጎዳና መ/ቤት ባለሙያዎች በታላላቅ ማሽነሪዎች ተራራውን እየነደሉና ለዘመናት ተገሽሮ የኖረውን ታላላቅ ቋጥኝ ድንጋይ እየፈረካከሱና እየከሰከሱ ጥርጊያ መንገዱን ሲያሳምሩ ያስተዋለው ያ ጠቢብ ባለ ሀገር ነገሩን ይከታተል የነበረው በአንክሮ ነበር። እናም የመከላከያ ሠራዊቱ የወራሪውን ኃይል በአይቀጡ ቅጣት እያርበደበደ ወደፊት ሲገሰግስና የሽምቅ ተዋጊ ኃይሉም እንዳልነበረ ሆኖ ሲበታተን አስተውሎ ከሚከሰከሰው የቋጥኝ ድንጋይ ጋር በማመሳሰል እንዲህ በማለት እንደተቀኘ በወቅቱ በስፋት ይወራ ነበር።

**ድንጋይ አይሞት ያሉት ሞት ተፈረደበት፣**
**እየከሰከሱ መኪና ነዱበት።**
**እስቲ በል ተፈጨው እስቲ በል ተቦካ፣**
**እስቲ በል ተጋገር፣**
**አንተም ማን አስኔን አብዝተኸው ነበር።**

የዚህ አርሶ አደር ግጥም ለትናንት ብቻም ሳይሆን ለዛሬም ጭምር የሚያስተላልፈው ወቅታዊ መልእክት ከዐውዳችን ጋር የሚስማማ ነው።

የአሸባሪው ትህነግ ትልቁ ችግሩ ፈሪ ሆኖ እያለ ራሱን እንደ ጀግና ቆጥሮ ማቅራራቱ ነው። ፈሪ ሰው ዘመኑን የሚፈጀው እንደባነነና እንደ በረገገ ነው። ስለዚህም ሳይሆን አይቀርም “ፈሪ ካልጋ ላይ እየባነነ መውደቅ ልማዱ ነው” የሚባለው። ከተረጋጋ እንቅልፍ እየባነነ የሚያነጋ ሰው በጨለማ መደነባበሩ አይቀሬ ነው። ዕቃ መስበር ብቻም ሳይሆን እርሱም መሰበሩ አይቀርም።

የሕወሓት ሞት “ሀ” ብሎ የጀመረው መንግሥታዊ ሥልጣኑን በያዘ ማግሥት ነበር። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ነው “አልሞትኩም ብዬ አልዋሽም” ማለትን መለማመድ የጀመረው። አንዳንድ አብነቶችን እናስታውስ። ጀግና ማለት ካሸናፊነቱ በኋላ ተረጋግቶ ለአዳዲስ ድሎች የሚዘረጋ እንጂ የትናንቱን ገድል እየተረከ በማላዘን የሚኖር አይደለም።

ትህነግ ግን እንደዚያ አልነበረም። “ራሱን ጀግና” እያለና እያሰኘ በማንቆለጳጰስ የኖረው የደርግ ሥርዓትን በየደቂቃውና በየሰኮንዱ እያብጠለጠለና የእርሱን ሠራዊት ጀግንነት እየተረከና እያስተረከ ነበር። ገና በጠዋቱ በአብዛኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ ልብ ውስጥ ሞቶ መቀበሩ ጠፍቶት ነበር ማለት አይቻልም። ለማሳያነትም የስሙን፣ የአርማውንና የርዕዮተ ዓለሙን ይዘት ማስታወሱ ብቻ በቂ ይሆናል።

ሀገር እየመራ እያለ እንኳን “ሕዝባዊ ወያኔ ሓርነት ትግራይ - ሕወሓት” / ትህነግ የሚለውን የጫካ ስሙን ለመለወጥ አልፈለገም። ይህ የሚያሳየን የመንግሥትን ሥልጣን ጨብጦ እንኳን ፍርሃቱ እንዳለቀቀውና የሕዝብ ቁጣ ወደ ወጣበት ጫካ እንደሚመልሰው በማመኑ ነበር። ፍርሃቱ ከዓመታት በኋላ ተግባራዊ መሆኑ በእጅጉ የሚያስገርም ነው። በአርማውም ላይ ጎላ ብሎ ይታይ የነበረው የክላሽንኮቭ ጠብመንጃ መሆኑ ትዝ ይለናል። “አብዮታዊ ዲሞክራሲ” የሚለው የፖለቲካ ፍልስፍናውም ሞቶ መቃብር ውስጥ ከገባው የምሥራቅ አውሮፓ ኮሚኒስታዊ ርዕዮተ ዓለም የተቀዳ ነበር።

ለምን እንደዚህ ሲሸበር ኖረ? መልሱ ግልጽና ቀላል ነው። እብሪተኛና ፈሪ ስለሆነ ብቻ ነው። በጓዳውና በውስጡ “አልሞትኩም ብዬ አልዋሽም” የሚለው እውነት ያቃጭልበታል፤ ላይ ላዩን ግን “ጀግና” እያለ ራሱን ሲሸነግል ኖሯል። ስለዚህም ነው ሕወሓት በአገዛዝ ዘመኑ ሳይቀር የኖረው በፍርሃት እያላበው ነበር የምንለው።

በዚህ ጸሐፊ እምነት ይኼው ቡድን ከጅምሩ የሰሜንን ዕዝ የተዳፈረው “አሸንፋለሁ” በሚል ሞራል ሳይሆን ፍርሃት ውስጡን እየናጠ መረጋጋት ስለነሳው ብቻ ነው። ቀደም ሲል በኢትዮጵያና በኢትዮጵያውያን ላይ የፈጸማቸው በደሎችና የዘመነ ገዢነቱ ግፎችና ዘረፋ መረጋጋት ስለነሳው ጀግናውን የሉዓላዊነታችንን ዘብ ለመዳፈር በርግጎ ዘራፍ አለ። ድል የቀናው ስለመሰለውም በአደባባይና በዓለም ፊት “ኢትዮጵያን ለማፈራረስ እስከ ሲዖል ድረስም ቢሆን እወርዳለሁ” በማለት መሬት ጠበበኝ ብሎ እስከ ማቅራራት ደረሰ።

በሁለተኛውና በሦስተኛው ወረራውም የግፉ ዋንጫ ሞልቶ እስኪገነፍል ድረስ ንጹሐንን ለመጨፍጨፍ፣ የሀገርን ንብረትና ሀብት ለማውደም በግፍ ጭካኔ በረታ። ፍርሃቱ ባያስበረግገው ኖሮ በተቀጣቀጠ ሸንበቆ የሚመሰለውን የጀሌውን ሠራዊት አሰልፎ እንደምን ከመቶ አሥራ አምስት ሚሊዮን በላይ ከሚገመት ሕዝብና ከሕዝብ አብራክ ከወጣ ጀግና ሠራዊት ጋር ይላተም ነበር?

ፈሪ ባይሆን ኖሮ ለሃያ ሰባት ዓመታት ያህል በመጨረሻው የሀገሪቱ የሥልጣን ወንበር ላይ ተቀምጦ እያለም ቢሆን ከየካቲት እስከ የካቲት የዋለበትን የጦር ሜዳ ፊልም ሲያሳየን ባልኖረ ነበር። ፈሪ ባይሆን ኖሮ በአምሳሉ የቀረጻቸውን ጋዜጠኞችና ፕሮፓጋንዲስቶች ከበረሃ የቋንቋ አጠቃቀምና ድምጸት በማረቅ ባስተካከላቸው ነበር። ዛሬም ከሠላሳ ዓመት በኋላ እንደ ስሙና አርማው ለመለወጥ እየተናነቀው ያለው የቅስቀሳ ስልቱ ነው። ፍርሃቱን የሚሸሽግበት ውሸት፣ ትምክህት፣ እብሪት፣ ትዕቢት፣ ማን አለብኝነት ዋናዎቹ የትህነግ መታወቂያዎች ናቸው።

የሦስተኛ ዙሩ የወረራ ታሪኩ ተቀልብሶ ሊደመደም ቋፍ ላይ ደርሶ የመቃብር ጉድጓዱን ቁልቁል እያስተዋል እንኳን “ጀግናው የሕወሓት ሠራዊት” እያለ ማቅራራቱ ፈሪ ብቻ ተብሎ የሚደመደም ሳይሆን “ጅል” የሚል ቅጽልም ሊታከልበት ይገባል። “ፈሪና ጅል ሁለት ጊዜ ያለቅሳል። አንዴ ሲመከሩት አንዴ ሲቀጡት” ይባላል። የሕወሓት ፈሪነትና ጅልነት ግን ከሁለትም አልፎ ሦስተኛ ደረጃ ላይ ደርሷል። “አንድም ሲመከሩት፣ አንድም ሲያስመክሩት፣ አንድም ሲቀጡት። ” ሀገረኛው ተሚጋች፤ “ምንሽም ምንሽ አይበጅን፤ ሞትሽ ነው የሚከሰን” ያለው በሚገባ ትህነግን ይገልጻል።

ቡድኑ እየተወነ ያለው “አልሞትኩም ብዬ አልዋሽም” በሚል ባለ ሦስት ገቢር የትራጄዲ ተውኔት ነው። “በግባ መሬት” ሊጠናቀቅ ቋፍ ላይ የደረሰው የታሪኩ መጋረጃ ሊጣልና የመድረኩ ብርሃን እየደበዘዘ ያለውም በፈጣን ሁኔታ ነው። አልገባውም እንጂ “ልጡ ተርሶ፤ መቃብሩ ተቆፍሮ” አልቃሽና አስለቃሾቹ እያረገዱለት ሊሸኙት የቀረው አንድ ሐሙስ ብቻ ነው። “ከፉን ከነከንፉ” እንዲሉ ቀጣዮቹ ወርተረኞች በአምሳሉ የፈለፈላቸው መጋለቢያ ጌኛዎቹ ስለመሆናቸው ጥርጥር አይገባንም።

ኢትዮጵያ በአሸናፊነት እንደምትወጣ እንኳን ከእኛ ከልጆቿ ከጠላቶቿም የተሰወረ አይደለም። አሸባሪውን የትህነግ ቡድን ጅል ነው የሚያሰኘው አንዱ ምክንያት ሽንፈቱ ብቻም ሳይሆን አስተሳሰቡ ጭምር ነው። በኢኮኖሚያቸውና በፖለቲካ ጡንቻቸው ሊጋርዱት የሚሞክሩት “ጌቶቹ” ለጊዜው ጮኸው ሲያጯጩኹለት “የሙጥኝ” በማለት ሥራቸው ለመሸጎጥ መሞከሩ የትም ሊያደርሰው እንደማይችል የገባው አይመስልም። ወይንም እውነቱ ገብቶት እያለም ልቡን እንደለመደው አደንድኖ በዕብሪቱ ገፍቶበትም ሊሆን ይችላል።

እስከ ዛሬ ድረስ እንደ በቀቀን ፕሮፓጋንዳውን ሲያራግቡለት የኖሩት ቅጥረኞቹ “ዓይንህ ላፈር” በማለት ገሸሽ እያደረጉት ነው። ሥርዓተ ቀብሩ ሙሉ ለሙሉ ተፈጽሞ ታሪኩን በግባ መሬት ለመደምደም የሚቀረው አንዱ ወሳኝ ክስተት በመከራ ውስጥ እያለፈ ያለው ራሱ የትግራይ ሕዝብ “በቃኸን! ማንነትህ በሚገባ ተገልጾልናል” ብሎ ከትከሻው ላይ አሽቀንጥሮ ሲጥለው ነው። ያኔ ሕወሓት ይሉት የሀገር ጉድ አፈር ለብሶ ድንጋይ ይንተራስና በነበር ሲረገም ይኖራል። ሰላም ይሁን።




# በሰራዊቱ ላይ የተፈጸመውን ግፍ ብቻ ሳይሆን መስዋእትነቱንም መቼም አንረሳውም!

**ወጋሶ**

ያቺ ቀን፣ አዕምሯቸው በትዕቢት አብጦ፤ ልባቸው ክፋት አምጦ፤ መንፈሳቸው ተንኮልን አብሰልስሎ ለዓመታት የትግራይን ህዝብ ሲጠብቅ በኖረው የመከላከያ ሰራዊት ላይ የክህደት እና የጭካኔ ተግባር የፈፀሙባት ዕለት ነች። የአገርን ልብ እንደሰው ልብ ያደሙበት። አዎ! ያቺን ዕለት እኛ ኢትዮጵያውያን መቼም ቢሆን አንረሳትም - ጥቅምት 24 ቀን 2013 ዓ.ም ውድቅት ላይ የሰሜን እዝ ጀርባውን በከሃዲው አሸባሪው ትህነግ የተወጋበትን ቀን።

አሸባሪዎቹ ትህነጎች፣ መንገዳቸው የጨለማ ስለነበር የት ጋር ሊሰናከሉበት እንደሚችል አላወቁም፤ ከዛ ይልቅ ከውልደታቸው ጀምሮ የተጠናወታቸው እብሪትና እብሪቱ የወለደው ጀብደኝነታቸው ዋጋ ወደሚያስከፍላቸው የፍጻሜያቸው መጀመሪያ ወደሆነው ስህተታቸው ገቡ።

ለበርካታ ዓመታት ጥላ ከለላ ሆኖ ሲጠብቃቸው፣ በጉልበቱ ሲያገለግላቸው በነበረው የመከላከያ ሰራዊታችን ላይ ጥቃት በመሰንዘር አንድም ለስልጣን የቱንም አይነት ዋጋ እንደሚከፍሉ፤ ስልጣን ለእነሱ ከአገር እና ከህዝብ በላይ መሆኑን በተጨባጭ አስመሰከሩ። በእጅጉ ዘግናኝ እና መራራ በሆነው የክህደት ተግባራቸው በኢትዮጵያውያኑ ልብ ውስጥ የነበራቸውን እንጥፍጣፊ ቦታ አሟጠው ከመሬት ደባለቁት። በሰሩት ግፍም ከንቱነታቸው በአደባባይ ተገለጸች።

የአሸባሪው ትህነግ ትዕቢትና እብሪት ጠማማውንና ክፉውን መንገድ እንዲከተል አስገድዶት የሕዝብ ልጅ በሆነው በአገር መከላከያ ሰራዊት ላይ እጁን ማንሳቱ የገዛ አካሉን በገዛ ሳንጃው በጭካኔ እንደወጋውና እንደቆረጠው ተቆጥሯል። አስቦበት እና አቅዶበት የታመነበትን ወገኑን አድብቶ ማጥቃቱ ግን እንደ መሻቱ ሊሳካላት የፈለገውን ሊያሳካለት አልቻለም። እውን ለማድረግ የቋመጠለት ሕልም አልተሳካለትም።

ጀግናው የመከላከያ ሰራዊታችን በከዳተኛው ቡድን ከጀርባው በተወጋበት ቅጽበት በወቅቱ የቡድኑ ቃል አቀባይ የነበረው ሴኩቱሬ ጌታቸው፣ አስነዋሪ ድርጊታቸውን ያለምንም ሃፍረት በሰራዊቱ ላይ «መብረቃዊ ጥቃት» መፈጸማቸውን መናገሩ የክህደታቸውን ጥግ የሚያሳይ ነበር። ይሁንና ከሃዲው ሴኩቱሬ፣ ‹መብረቃዊ ጥቃት› ያለው ድምፁ ሳይደበዝዝ ላይነሳ ማሸለቡን ታሪክ ዘግቦት አልፏል።

በባንዳው የተከዳው የአገር መከላከያ ሰራዊት ከቸገራቸው ጎን በመቆም የሚስተካከለው አልነበረም። ከሁለት አስርት ዓመት በላይ በትግራይ ሲቆይ ጊዜውን በቀበሮ ጉድጓድ አገርን ከጠላት ለመታደግ፣ በአርሶ አደሩ ማሳ አንበጣ ለማባረር እንዲሁም የደረሰ ሰብል ለመሰብሰብ ሕይወቱንም ጉልበቱንም ሰስቶ አያውቅም፤ ካለው አካፍሎ ትምህርት ቤት፣ ጤና ጣቢያና መሰል በጎ ተግባር ሲሰራ የቆየ፤ ዜማው ህዝባዊነት፤ መገለጫም ህዝባዊነት ነበር።

በቡድኑ የአደባባይ ክህደት የመላው ኢትዮጵያዊ ልብ ተሰብሯል። ስንቶቹን የአገር ኩራት በግፍ መነጠቃችንን ስንሰማ አምርረን እንደ አንድ ልብ አልቅሰናል። ሉዓላዊነታችን ተወጋ የሚል መረጃ ሲደርሰን አንጀታችን ተንሰፍስፏል። ጉዳታቸው አሳምሞናል።

እርግጥ ነው የባንዳው ዓላማ የቀለሞች ኅብር የሆነችውን ታላቋን ኢትዮጵያ ለማፍረስ ነበር። ለእርሱ ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊያነት ዛሬም ቢሆን አይገባውም። ኢትዮጵያዊነት እንደ አለት ጽኑ መሆኑን ከቶ አያውቀውም።

አሸባሪው ትናንትም የነበረው መሰረት የባንዳነት ነው። ዛሬም የሚያንጸባርቀው ያንኑ ባንዳነቱን ነው። ምክንያቱም እሱ ይመቸው እንጂ የትግራይ ሕዝብ ሆነ የተቀረው የኢትዮጵያ ሕዝብ ለእርሱ ምኑም አይደለም፤ በተከፈለው እና በተገባለት ቃል ልክ አገሩንና ሕዝቡን እያዋረደ ራሱን ከሰገነት ላይ ማስቀመጥ ሕልሙ ነው።

አገራችን ኢትዮጵያ ከዚህ ከሃዲ ቡድን የጥፋት እና የባንዳነት ተልእኮ የተነሳ በርካታ ፈተናዎችን ለማሳለፍ ተገዳለች፤ አሁንም እንደተገደደች ነው። ይህም ሆኖ ግን የቀደመ ታሪኳ ሆነ አሁን እየሆነ ያለው እውነታ የሚመሰክረው ከፈተናዎች በላይ የመሆን አቅም ባለቤት መሆኗን ነው። ከሁሉም በላይ ሉዓላዊነቷን ለመድፈር የሚቀላውጠውን የትኛውንም ኃይል ማዋረድ የቀደመ ማንነቷ ነው።

ሉዓላዊነቷን አደጋ ውስጥ ሊያስገባ የሚችል የትኛውም ፈተና ቢከባት፣ ዓለም አቀፍ ጫና ቢበረታባት በፍጹም አንገቷን አያስደፋትም። ይልቁኑ ከወትሮው በተለየ ሁኔታ አንድነቷን እንደ ብረት አጽንቶ የሚያቆማት አገር ነች። ይህን ደግሞ የ50 ዓመት የክህደት ልምድ ያለው አሸባሪው ትህነግ ቀርቶ ዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ ጠንቅቆ የሚያውቀው ጉዳይ ነው።

ዛሬ ትናንት አይደለም፤ የከሃዲው ትህነግ ጀምበር ጠልቃለች። መብራቱም ጠፍቷል። እስካሁንም ድረስ ‹ከፋፍዬ በትኛቸዋለሁ› ያላቸው ኢትዮጵያውያን በተለይ ደግሞ በእርሱ የአገዛዝ ዘመን ያደጉ ወጣቶች ሕልሙን ቅዠት በማድረግ በኩል ግንባር ቀደም ተሰላፊ መሆናቸውን በተግባር አሳይተውታል።

መሸሸጊያ ያደረገውም የትግራይ ሕዝብ ‹በቃኸኝ› ሲል ከጀግናው መከላከያ ሰራዊታችን ጎን በመቆም በእነርሱ ዘንድ አለመፈለጉን በተግባር እያሳየው ነው። የቡድኑ መዝገቡ ሲገለጥ የሚነበበው ኹከትና ሽብርተኝነት በመሆኑ ራሱ በቆፈረው ጉድጓድ እየገባ ነው።

ቡድኑ በሰሜን ዕዝ ላይ የፈጸመው ግፍ ከክብደቱ የተነሳ ሐዘኑን፣ እንኳን የሰው ልብ ምድር ልትሸከመው የሚከብዳት ነው። ይህ ግፍ የተሞላበት ክህደት በጀግናው መከላከያ ሰራዊታችን መፈጸሙን ለመዘከር በተዘጋጀ መድረክ የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር እና የጦር ኃይሎች ጠቅላይ አዛዥ ዶክተር ዐቢይ አሕመድ፣ «ጥቅምት 24 ቀን 2013 ዓ.ም በግፍ የተገደለው ወታደር ብቻ ሳይሆን ኢትዮጵያም ተገድላለች፤ በእለቱ የተጨፈጨፈው ሰራዊቱ ብቻ ሳይሆን የኢትዮጵያ ህዝብም ጭምር ነው» ማለታቸው የሚታወስ ነው።

ታድያ ይህ ክፋት መቼም ቢሆን በማንም ላይ እንዳይደገም ትውልድ በአግባቡ ሊገነዘበው ይገባል። የአሸባሪው ትሕነግ ግፍ አምና የታወሰው «አልረሳውም፤ እኔም የኢትዮጵያ ሰራዊት ነኝ” በሚል መሪ ሃሳብ ነበር፤ ዘንድሮም ጥቅምት 24 ቀን 2013 ዓ.ምን «መቼም አንረሳውም» በሚል መሪ ሐሳብ እየተከበረ ይገኛል።

የሽብር ቡድኑ በሰራዊቱ አባላት ላይ የፈጸመው ይህ ክህደት ሆነ አሰቃቂ ግፍ ሊረሳ የሚችል አይደለም። ይህ አይነቱ በአገርና በህዝብ ላይ የሚፈፀም ክህደት ዳግም እንዳይፈጸም የዚህ ትውልድ ብቻ ሳይሆን የመጪውም ትውልድ ኃላፊነት ነው፤ ለዚህም ነው ዛሬ ላይ ሆነን «መቼም አንረሳውም» የምንለው!

# የክፍለ ዘመኑ የክህደት ጥግ እና ሀገርን የመታደግ ተጋድሎ

**ታምራት ተስፋዬ**

በጎጥ በረት ውስጥ የተፈለፈለውና የጎሳ ጡጦ ጠብቶ ያደገው አሻባሪው ትህነግ የአራት ኪሎ ቤተ-መንግስትን በወረራ ተረክቦ በትረ-ስልጣኑን አስጠብቆ በቆየባቸው 27 አመታት ሲለው በዴሞክራሲ ስም እያላገጠ፤ ሲያሰኘው ደግሞ በኃይል እየደፈጠጠ አምርሮ የሚጣላትን አገር ሲያስተዳድር ቆይቷል።

«እንዳሻዬ አዛዥ ናዛዥ እንዳልሆን ያደርጉኛል» በሚል ስጋት ከእሱ የተለየ አመለካከትና ሃሳብ ያላቸው ወገኖች ሁሉ የተለያዩ ቀለሞችን በመቅባት፣ የፈጠራ ስም በመለጠፍና ሰበብ አስባብ በመፈለግ በቀጥታም ሆነ በረቀቀ መንገድ ሰውሯል፤ አስሯል፤ ገድሏል ፤ አስገድሏል።

ቡድኑ በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ የሚፈፅመው የበደልና የግፍ ጽዋ ሞልቶ መፍሰሱን ተከትሎ፤ ውድ የኢትዮጵያ ልጆች በከፈሉት መራራ መስዋትነት ሳይወድ በግድ እጁ ተቆልምሞ ከአራት ኪሎ ቤተ-መንግስት ከተባረረና መቀሌ ከመሸገ ወዲህም የቀደመ እብሪትና የጥፋት ሱሱ ሊላቀቀው አልቻለም።

በጎሰኝነት አስተሳሰብ፣ በመጥበብ ፖለቲካ የተካኑት አሻባሪዎቹ የትህነግ አመራሮች በኢትዮጵያ ህዝብ ትግል ከስልጣን ተብራው ከመሪነት ርካብ በወረዱ ማግስት ጀምሮም በዚህ ስብእናቸው ከቀደመው ዘመን በላይ ወርደው፤ ዘቅጠው ታይተዋል።

ኢትዮጵያን የሚፈልጓት እነርሱ እስከገዟትና የበላይነትን ይዘው እስከቀጠሉ ብቻ መሆኑንም በተጨባጭ አስመስክረዋል። እግሬ አውጭኝ ብለው መቀሌ ከመሸጉ ጀምሮም ለውጡን እና የለውጡን ሀይል ሲያጥላሉና ሲቃወሙ፤ የለውጡ ትሩፋት ለትግራይ ህዝብ እንዳይደረስ እንደ ጎሊያድ መንገድ ሲዘጉም ተስተውለዋል።

በለመዱት የከፋፍለህ ግዛ መርህ በጎሳዎች፣ በብሔሮችና በአጠቃላይ በህዝቡ መካከል “encouraging blood feuds“ የእርስ በርስ ጥላቻና መርዝ ሲያሰራጩ ሲያራግቡም ከርመዋል። ስለ ጦርነት እየዘመሩም አደባባይ ወጥተዋል። ኢትዮጵያን መምራት የምንችለው «እኛ» ብቻ ነን በሚል ፍፁም ድንቁርና ኢትዮጵያ ከምታክል አገር ይልቅ እነርሱ ለምዕራባውያን ፍላጎት የተሻሉ ስለመሆናቸውን ደስኩረዋል።

የአገር ክብር ዘብ የሆነውን ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊያንን ለዘመናት ከአለት አፅንቶና ከምሰሶ አበርትቶ ያቆመውን መከላከያ ሰራዊት ሳይቀር ከክብር በታች ለማውረድና ለመከፋፈል ብዙ ደክመዋል። የሐሰት ወሬ በስፋት አሰራጭተዋል። ወታደራዊ ሚስጥርን የሚጥሱ መግለጫዎችን ሳይቀር አሳልፈው በመስጠት ሀገርን ለውጭ ባዕዳን ከማጋለጥ እንደማይቆጠቡ በግልፅ አስመስክረዋል።

ይባስ ብሎ መንግሥት ለሰላም የዘረጋውን እጅ እንደሸንፈት በመቁጠር የቡድኑ አባላትና ጋሻ ጃግሬዎች የስልጣን አባዜ የሚያመጣው እብደት «ከእኛ በላይ ላሳር» በሚል ትእቢት ተወጥረው፣ ከሁሉም በላይ ጤንነታቸውን በሚያጠያይቅ መልኩ ጥቅምት 24 ቀን 2013 ዓ.ም የኢትዮጵያ ቀይ መስመር ተላለፉ። :

አገርን ዳር ድንበር ከማስጠበቅ ባሻገር ለትግራይ ህዝብ ኮቾሮአቸውን አካፍለው፣ የኮዳ ውኃቸውን ለግሰው፣ ደመወዛቸውን ለትምህርት ቤት ግንባታ ቀንሰው ለመስጠት በማይሰለቹ የሰሜን ዕዝ ሰራዊት አባላት ላይ ጥቃት በመፈጸም የእብደትና የእብሪት ጥጋቸውን በአደባባይ ገልጸዋል።

ቀን በጠራራ ፀሐይ አንበጣ ሲያብርሩና የትግራይን አርሶ አደር ሰብል ሲያጭድ የዋሉ የሰራዊቱ አባላት እንኳን በእውን በህልማቸው እንኳን ለማሰብ ፈፅሞ በማይችሉት መልኩ ከድካም እንዳረፉና ትጥቃቸውን እንደፈቱ ምሽት ላይ ድንገት ከጀርባ ወግተዋቸዋል። ሰራዊቱ መሳሪያውን ለማንሳት፣ ለመገመትም ሆነ ለመጠራጠር እንኳን ጊዜ ባላገኘበት ፍጥነት ከውስጥና ከውጭ ጥቃት ፈጽመውበታል።

ከሀዲዎቹ የደደቢት ሽፍቶች በታሪክ ታይቶም ሆነ ተሰምቶ በማይታወቅ መልኩ አመታትን አብራቸው ጦር ሜዳ የተሰለፈን፣ አብሮ የተዋደቀን፣ አብሮ የበላና የጠጣውን የሀገር መከላከያ ሠራዊት በመክበብ እንደ ጠላት ሰቅጣጭና በጣም ዘግናኝ በሆነ መልኩ ጨፍጭፈዋል።

ኢ-ሰብአዊ የመሆናቸውን ጥግ በሚያስመሰክር መልኩ ከሰው ልጅ ሰብዓዊ ክብር በእጅጉ በወረደ መልኩ ከጭፍጨፋው የተረፉትን የመከላከያ ሠራዊት አባላት በሙሉ ሰብስበው የለበሱትን ወታደራዊ ሬንጀር ልብስ አስወልቀው፣ ትጥቃቸውን አስፈትተው፣ ጫማቸውን አስወልቀው ረሽነዋል። የጠላት ወታደር ላይ እንኳን ለመፈፀም በሚከብድ መልኩ ጥይት ላለማባከን በማለት አስተኝተው ከባድ ተሽከርካሪ ነድተውባቸዋል።

በዚህ የባንዳ ተግባር በርካታ የኢትዮጵያ መከላከያ ሰራዊት አባላት ቢጨፈጨፉና መስዋትነት ቢከፍሉም በርካቶች «ለወያኔማ እጃችንን አንሰጥም» በሚል እጅግ በላቀ ቆራጥነትና አስደናቂ ጀግንነት ተዋግተው የጠላትን ከበባ ሰብረው መውጣት ችለዋል።

መከላከያ ሰራዊቱም በደረሰበት ክህደት ልክ ሳይሆን ሀገርን በሚያድን መልኩ አካባቢውን ሙሉ በሙሉ ለመቆጣጠር የሚያስችል ወታደራዊ ስምሪት በማድረግ የአሸባሪው ቡድን አባላት በቀበሮ ዋሻ ውስጥ ለመቀርቀር ረጅም ጊዜም አላስፈለገውም። ፍጹም በሆነ ጀግንነት የቡድኑን ሀገር የማፍረስ ተልእኮ ተቋቁሞ አስደናቂ በሆነ መልኩ አገርን ታድጓል።

የፌደራል መንግስት ሰኔ 21 ቀን 2013 ዓ.ም ከትግራይ ጊዜያዊ አስተዳደር የቀረበለትን ጥያቄ መሰረት በማድረግ የተናጠል ተኩስ አቁም አውጆ ክልሉን ለቆ ሲወጣ፣ “ለውሻ ከሮጡለት፣ ለልጅ ከሳቁለት” እንደሚባለው የአሸባሪው ትህነግ አመራሮች በእነርሱ ኃይል የተገኘ ድል በማስመሰል ከተንቤን በረሃ አዋራቸውን አራግፈው መቀሌ ገብተዋል።

ለህዝብና ለአገር ደንታ የሌላቸው የሽብር ቡድኑ አመራሮች የፌደራል መንግስቱን ውሳኔን እንደ ድክመት በመመልከትና «ኢትዮጵያን ለማፍረስ ሲኦልም ቢሆን እንወርዳለን» በሚል አብሪት ጦርነቱን ወደ ከትግራይ አጎራባች ክልሎች በማሻገርም አፋርና ወደ አማራው ክልል በመግባት የግፍ ተግባራቸውን ቀጥለዋል።

ጦርነቱን ገፍተው በገቡበት አጎራባች ክልሎች፣ ወጣት ሴቶች፤ ህጻናትና አዛውንቶች ጨፍጭፈዋል። ደፍረዋል። የእምነት ተቋማትን አቃጥለዋል። ለመተካት የማይቻሉ ቅርሶች ሰርቀዋል፤ አወድመዋል። በድሃ ህዝብ የተሰሩ ክሊኒኮች፤ ሆስፒታሎች ዘርፈዋል፤ አቃጥለዋል። በርካቶችን ከቀያቸው አፈናቅለዋል፤ ለረሃብ አጋልጠዋል።

የዘረፉትን ዘርፎ ወደ ትግራይ ከመውሰድ ባለፈ መውሰድ የማይችሉትን አቃጥለዋል። አርሶ አደሮች ወዛቸውን ጠብ አድርገው ያለሙትን ሰብል ዘርፈዋል። የአርሶ አደሮችን ቤት በሞርታር አረር አንድደዋል።

ትህነግውያኑ ሌላው ቀርቶ የአምልኮ ተቋማቶችን ሳይቀር አውድመዋል። አቃጥለዋል። ቤተእምነት መቅደስ ውስጥ ሳይቀር ተፀዳድተዋል። ቤተ እምነቶችን እንደ ዳንኪራ ቤት በመመልከት መጠጥ ሲጠጡና ሲደንሱም ታይተዋል።

ከሃዲው ቡድንና አባሪዎቹ ኢትዮጵያን በሁሉም አቅጣጫ በማዳከም ለማንበርከክ አስፍስፈው ለመሻታቸው ብዙ ቢታታሩም የኢትዮጵያን ስም ጠርቶ፣ ስለ ኢትዮጵያ ሰይፍ አንስቶ ተሸንፎ የማያውቀው ጀግናው የመከላከያ ሰራዊታችንን ክንድ ግን መቃወም አልሆነላቸውም።

በተለይ የጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ከቤተ መንግስት ወንበር ላይ ተነስተው አገሬ ከእኔ ስልጣን፣ ክብር፣ እውቀት፣ ነፍሴ በላይ ነች በሚል ወደግንባር መዝመት ተከትሎ ይበልጥ የተነቃቁት የኢትዮጵያ የቁርጥ ቀን ልጆች፣ በአጭር ቀናት ውስጥ ወራሪውና ተስፋፊው ቡድን እንደለመዱት ድባቅ አድርገውታል።

ጠላት ለበርካታ ወራት የዘረፈውን ሀብት በመጠቀም በወረራ በያዛቸው አካባቢዎች ህዝብ በማስገደድ ያሰራውን ባለብዙ እርከን ኮንክሪት ምሽግ በተቀናጀ እቅድ፣ አመራርና ቴክኖሎጂ በመታገዝ በአነስተኛ መስዋዕትነት ሰባብረውታል።

የኢትዮጵያ ጀግኖች ኢትዮጵያ ከናዚስት ትህነግና ከሚመራው የሲያል ሠራዊት ተልእኮ ለማዳን በእያንዳንዱ ግዳጅ ኢትዮጵያ የተከበረች፣ ለአሸናፊነት የተመረጠች፣ ለምስክርነት የተቀመጠች ጀግና የምትወልድ፣ ወልዳ የምታሳድግ አገር መሆኗን በተጨባጭ አስመስክረዋል። ታሪክ ሁሌም የሚዘክረው ጀብድ ፈፅመዋል።

በክህደት መንገድ ተራምዶ ከናፈቀው የአራት ኪሎ ግቢ ለመግባት የመጠው ቡድኑ ያሻውን ማድረግ ተስኖት በመጨረሻ «በማንኛውም ግዳጅ ወይም ተግባር የላቀ ውጤት» በሚል እሴት በተገነባው፣ በየትኛውም ሁኔታ በማንኛውም የአየር ፀባይ ማንኛውም ግዳጅ በውጤት የማጠናቀቅ አንፀባራቂ ድል የማስመዝገብ አቋምና አቅም ባለው የኢትዮጵያ ሰራዊትና የቁርጥ ቀን ልጆች ተቀጥቅጦ ወደ መጣበት ተመልሷል።

ቡድኑ ዳግም ተቀጥቅጦ ወደ መጣበት መቀሌ ከፈረጠጠ ወዲህም አመራሮቹ ከህዝብና ከሀገር ሰላም እና ደህንነት ይልቅ የራስን ምቾትና ፍላጎት በማስቀደም፣ ለሰላም የተዘረጋን እጅ በመቁረጥ ሶስተኛ ዙር ጦርነት በመክፈት ለጥፋት የማይደክም መሆኑን አስመስክሯል።

የፌደራል መንግስቱ ለኢትዮጵያ ደህንነት በተለይም ትግራይ ህዝብና ሰላም ሲል ሁሉንም ይቅር ቢለውም፣ አሸባሪው ቡድን በአንፃሩ በግፍ ያፈሰሰው ደም አስክሮት ዳግም ጦርነት ከፍቷል። አገርን እና ህዝብን መካዱን አስቀጥሏል።

ፈተና የሚፀናቸው ችግር የሚያጠነክራቸው፣ ክፉ ቀን የሚያስተሳስራቸው ኢትዮጵያዊያን የሰላም አማራጮች እንደተጠበቁ ሆነው በአሁን ወቅት በቁጣ ተነስተውና በአንድነት ቆመው የሽብር ቡድኑን በሚገባው ቋንቋ እያናገሩት ይገኛሉ።

የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊትና ሕዝባዊ ሠራዊቱ (ልዩ ሀይላት፣ ፋኖ፣ ሚሊሺያ) ኢትዮጵያን ወደ ሲኦል አወርዳታለሁ ብሎ የዛተውንና የሚዳክረውን የናዚስት የሲያል ሠራዊት ወረራ እየመከቱና ወደ ግብአተ መሬቱ እየወሰዱት ይገኛሉ።

ጀግናው የመከላከያ ሰራዊታችንም በእያንዳንዱ ግዳጅ በሰከነ መልኩ በሚፈፅመው አገርን ማዳን ተልእኮ ኢትዮጵያ የነኳትን እየሰበረች፣ የደፈሯትን እያሳፈረች ከታሪክ ላይ ታሪክ እየጨመረች፣ ታሪኳን እያደመቀች፣ ስሟን እያገነነች እንድትቀጥል ፍቅርና ውድ ሕይወቱን እየሰጠ ይገኛል።

የሰላም በሮች እንደተከፈቱ ሆነው በአሁን ወቅት ጀግኖች በደም ቀለም ታሪካቸውን እየፃፉ ነው። ጠላትን እየደመሰሱ ወደፊት እየገሰገሱ ነው። የመጨረሻው የድል ቀን ተቃርቧል። የጠላት መዳፈኛ መቃብሩ ተቆፍሯል። አፈር የሚመልሱበት ኢትዮጵያዊያንም ዙሪያ ገባውን ተዘጋጅተዋል። የሚያቆማቸው ማሸነፍ ብቻ ነው። የጠላት የማምለጫ ተስፋው አልቋል። በሮች በሁሉም በኩል ዝግ ናቸው።

ድል ለጀግናው ሠራዊታችን !

# " የጠላሽ.... ይጠላ....!! "

**ከአስባቸው ደሳለኝ አበሻ (ስንደን)**

አፈሩን ያቅልለት ነፍሡን ይማረውና ድምፃዊ ጥላሁን ገሰሰ

“ የጠላሽ ይጠላ ብድሩ ይድረሰው
የጎዳሽ ይጎዳ ተፈጥሮ ትውቀሰው
በከንቱ የሚያማሽ ስምሽን የሚያነሳ
ክፉ በመሆኑ አለበት ወቀሳ ... “

እያለ በምሬት እየጮህ ያንጎራጎረው እርግማን አሁን ድረስ በጆሮየ ውስጥ ያቃጭላል::

ጥላሁን ወዶ አልነበረም “የጠላሽ ይጠላ “ እያለ ለዘመናት የጮህው:: አሁንም የትግራይ ሕዝብ ወደ አምላኩ መጮህ አለበት::

እንደነ፣ ደብረፅዮን እንደ፣ ጌታቸው እረዳ፣ እንደ ጻድቃን ገብረ ትንሳይ፣ ወዘተ... የመሳሰሉ አረመኔ ሰይጣኖች በትግራይ ምድር ዳግም እንዳይፈጠሩ የትግራይ ሕዝብ እንደ ዕምነቱ ወደ ፈጣሪው ኤሎሔ ብሎ የጠላሽ ይጠላ በማለት መጮህ አለበት::

የአሸባሪው ትህነግ እኩይ ተግባር በትግራይ ሕዝብ ብቻ አላበቃም:: በመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ የመንፈስ ሽብር ፈጥሯል:: አንድ ለጋ የትግራይ ትውልድ/የትግራይ ወጣት እንዲቀጠፍ ምክንያት ሆኗል:: በውጤቱም አገር ያልተገባ መስዋእትነት ለመክፈል ተገዳለች ::

በአሸባሪው ትህነግ አጥፊ ቡድን የህዝቡ ላብና እውቀት የፈሰሰባቸውን የኢኮኖሚ ተቋሞች የዘመናዊ ስልጣኔ ምልክት የሆኑ ታሪካዊ ቦታዎች፤ ትምህርት ቤቶችና የጤና ጣቢያዎች ወድመዋል። የህዝብ መገልገያ ተቋማት ወድመዋል፤ተዘርፈዋል:: ትህነጎች በሀይማኖት ተቋማት ያልተገቡ ኢሞራላዊ ተግባራትን በመፈጸም ለህዝብ እምነት ያላቸውን ንቀት በአደባባይ ገልጸዋል።

በስልጣን በነበሩባቸው ዘመናት ለዘመናት በሰላም አብረው በመኖር የአንድ ቤተሰብ አካል የሆኑትን የአገሪቱን ሕዝቦች የሚለያይ፤ የአንድነት ገመዳቸውን የሚበጣጥስ ቋንቋና ዘርን መሰረት ያደረገ የፖለቲካ ስርአት በመፍጠር አገርን ለጥፋት መዳረጋቸው የቅርብ ግዜ ትውስታችን ነው።

ከስልጣን ከተወገዱ በኋላ ደግሞ የትግራይን ሕዝብ የመንግስት ጠላት አድርገው በማቅረብ ቢያንስ ያለመተማመን እንዲፈጠር የመተሳሰብ የልብ ግንኙነት እንዳይኖር ጥላችን በመንዛት እጅ... እጅ ፣ በሚል ፕሮፖጋንዳ በሕዝብና በመንግስት መካከል ያለውን ግንኙነት በጠበንጃ አፈሙዝ ቀይረው ህዝቡን ለሞትና ለስደት ዳርገውታል: :

ትህነግ ትናንት ሆነ ዛሬ ለአገራችን የሰብአዊነት ስጋት የሆነ አሸባሪ ድርጅት ነው:: ላለፉት 27 አመታት ለእራሳቸው ፍላጎትና ጥቅም ሲሉ በስልጣን ላይ ስልጣን በሀብት ላይ ሀብት ሲሰበስቡ ለሆዳምነትና ሞራለቢስነታቸው ወሰንና ድንበር ያልነበራቸው. ስግብግብ የቀን ጅቦች እንደነበሩ ዛሬ መላው ዓለም በደንብ እያወቃቸው መጥቷል ::

ትናንት ስልጣን ይዘው በነበረበት ወቅት ትልቁ ችግራቸው ስልጣንና ዕውቀትን አቀናጅቶ የፖለቲካ ልዩነቶችን በማቻቻል ተባብሮ ለመስራት አለመቻላቸው፤ እራስን ብቻ ትክክል አድርጎ በመቁጠር ሌላውን ጠላት አድርገው መውሰዳቸው ነበር። በዚህ አጥፊ ባህሪያቸው የተነሳም ሕዝቡ አሽቀንጥሮ፣ በትረ መንግስታቸውን ቀምቶ ታሪክ እንዲሆኑ አድርጓቸዋል::

በአገራችን በተቀጣጠለው. የመደመር ለውጥ ሁሉንም በይቅርታ ዘግተን በአገር ግንባታ ተሰልፈን የዲሞክራሲ ስርአትን በማነፅ ስለ ፍቅር ስለወንድማማችነት ስለአንድነት በመቆም ጠንካራ አገር እንፈጥራለን ብለን ስንነሳ ጭራሽ ይግረማችሁ ብለው የበቀል ጦርነት በማወጅ ሀያ ዓመት ቀበሮ ጉድጓድ ውስጥ ተኝተው የጠበቋቸውን የሰሜን ዕዝ የመከላከያ አባሎች በተኙበት የዛሬ ሁለት አመት በጥይት እረሸኗቸው:: እንደ ባእድ አያንገላቱም ክብርና ስብእናቸውን በማዋረድ ምርኮኛም አደረጓቸው። ይህንን የጭካኔ የክህደት ተግባር መቼም ቢሆን የማንረሰው እውነት ነው !

በጥይት የፈጇቸው ወታደሮች አስከሬናቸው እንኳን እንዳይቀበር ከልክለው እርቃናቸውን አደባባይ ጥለው በአስከሬናቸው ላይ ጨፍረዋል ... በህይወት እያሉ ሲኖ ትራክ የነዱባቸውም ጥቂት አይደሉም:: ልብሳቸውን አስወልቀው እርቃነ ስጋቸውን በባዶ እግር ወደ ጎረቤት አገር ያሰደዷቸውም እነሱን ለመጠበቅ በሺዎች ኪሎ ሜትር አቋርጠው በዛው የተገኙ ለእነሱ ባለውለታና የአገሪቱም የቁርጥ ቀኝ ልጆች ናቸው:: ይህ አረመኔያዊ ጭካኔ “ታሪክና ትውልድ የማይረሳው የበደል ፍፃሜ “ ነው። ይህች ቀን የኢትዮጵያ ሰማዕታት ቀን ነች “ መቼም ቢሆን እናስባታለን “ ::

የኢትዮጵያ ክብር ጠባቂ ሰይፍ እና ጋሻ ሆነው ያለፉትን የሰሜን ዕዝ መከላከያ ሰራዊት አባሎችን በበኩሌ ባሰብኩ ቁጥር በደም ዋጋ የተገነባው መከላከያ ሰራዊታችን ውድ ሕይወቱን ለአገሩ በመስጠት እየከፈለ ያለውን መስዋዕትነት በምንም ቃላት ለመግለፅ እንደማልችል እረዳለሁ ::

በአንፃሩ ደግሞ አሸባሪው ትህነግ ዛሬም የትግራይን ሕዝብ የአጥፍቶ መጥፋት ትርኢቱ ተካፋይ አድርጎ ለማቅረብ የኢትዮጵያ መንግስት ለለውጥ የሚያደርገውን እንቅስቃሴ በትግራይ ሕዝብ እንደመጣበት አድርጎ በአጥፊና ዘረኛ ቅስቀሳ ወጣቱን የሽብር ድርጊቱ ተሳታፊና የእልቂቱ ሰለባ እያደረገው ይገኛል ::

ቡድኑ በእብሪትና በቀቢሰ ተስፋ በሕዝብ ላይ ሶስት ጊዜ ወረራ አካሄዷል:: ይህ አስቀያሚና ወራዳ ተግባር የወያኔ አንድ የተበላሸ የታሪክ ዘመን መባቻ ተደርጎ መመዝገቡ የብዙ. ኢትዮጵያውያን እናቶች እርግማን ይመስለኛል .::

የትግራይ ሕዝብ ግን እንደሌላው የኢትዮጵያ ሕዝብ የአዲሱ ስርአት የለውጥ ራዕይ አጋር ለመሆን የተነሳ ሕዝብ ነበር :: ምንም እንኳን በአሸባሪው ትህነግ ካድሬዎች የጥላቻ መርዝ እንዲጨልጥ ተደረጎ በስቃይ፣ በጨለማ እና በጠኔ እየተገረፈ እንዲኖር የተገደደ መንፈሳዊና ሕሊናዊ ነፃነት ያጣ ህዝብ ቢሆንም ።

እንኳን እንደ ኢትዮጵያ አዲስ የእድገት ምእራፍ በጀመረች አገር ይቅርና ለማንኛውም ማህበረሰብ ቢሆን ጦርነት የሰላምና የልማት ጠንቅ በመሆኑ ማህበራዊ ሕይወትን ይረብሻል:: በሰላም ሰርቶ ለመኖር የሚፈልግን ሕብረተሰብ የማይነጋ መራራ ለሊት እንዲያሳልፍ የሚያደርግ ነው:: ጦርነት ውጤቱም ቢሆን የሚያስደስት ሳይሆን መድረሻ የሌለው ትርምስ ነው ::

ዛሬ አገራችንን ከአሸባሪው ትህነግ አገር የማፍረስ ተልእኮ ለመታደግ፤ የትግራይንም ህዝብ ከአሸባሪው ቡድን መንፈሳዊና ሕሊናዊ ባርነት ለመታደግ የምናካሒደውን ጦርነት ተገደን ገባንበት እንጂ ምርጫችን ምን ግዜም ሰላም ነበር ::

አሸባሪው ቡድን ግን እታገልልሀለሁ የሚለውን የትግራይን ህዝብ ጨምሮ ደም በማፍሰስ፣ ሕዝብን በማሰቃየት.፣ በማፈን፣ በመሰወር፣ በመጨፍጨፍና በመግደል የሚረካ በመሆኑ በአገርና በህዝብ ላይ ታሪክ ይቅር የማይለው ግፍ እየፈፀመ በአገራዊ ሰላማችንም ላይ ተግዳሮት ሆኖ ይገኛል::

ቡድኑ ደም በማፍሰስ የሚረካ አሸባሪ ቡድን መሆኑን በአፋርና በአማራ ሕዝብ ላይ የፈፀመውን ግፍ በማስረጃ ማቅረብ ይቻላል: : የንጹሀንን ደም፣ በማፍሰስ የሚረኩ ሰዎች ደግሞ ፍፁም ጤነኞች ናቸው ለማለት አይቻልም: :

ቡድኑ የሚያራምደውን የሽብር ጥቃት አቁሞ ያለፈውን እረስቶና ፍርዱን ለታሪክ አስረክቦ ትጥቁን በመፍታት በዘመናዊ ፖለቲካ በውይይትና በይቅርታ አምኖ አብሮ በሰላም ለመኖር በደልን ለመርሳት ቃል. እንዲገባ ላለፉት ሁለት አመታት ሲለመን ከርሟል::

ነገር ግን አንድን የጋራ ታሪክ የመሰረቱትን ሕዝቦች በፈጠራ ታሪክ ለመከፋፈልና የቅጥፈት ፕሮፖጋንዳ በማራገብ የአባቶቻችንን አኩሪ ታሪክ በመካድ ለትግራይ ሕዝብ የተቆረቆረ በመምሰል ኢትዮጵያን ለማፈራረስ ከታሪካዊ ጠላቶቿ ጋር በማበር ጠመንጃ አንግቶ ምሽግ ቆፍሮ የኢትዮጵያን ሕዝብ ወግቷል ::

ይህም ሆኖ አሁንም በድጋሚ እጃችንን ለሰላም የዘረጋነው ሳንበደል ቀርተን ሳይሆን ሁሉም ነገር እንዳልነበረ ተቆጥሮ በሕዝቦች ላይ የተፈፀመው ግፍ ዶሴው ተዘግቶ ለዚህ ሁሉ ችግር ያበቁንን መሰረታዊ ጠንቆች ለትውልዱ ትምህርት በሚሰጥ መልኩ በሰላም ለመዝጋት ነበር ።

እነዚህ ጠንቆች ተመልሰው የማይመጡበትን ሁኔታ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ዘግተን ለሁሉም እኩል የሆነች የተረጋጋች ኢትዮጵያን ለማቆየት ስንልም ነበር ያለቅድመ ሁኔታ ለሰላም በሚደረግ ውይይት ዝግጁ ነኝ ሲል የኢትዮጵያን መንግስት አጨብጭቦበን የደገፍ ነው::

እነሱ ግን በሀያ አንደኛው ክፍለ ዘመን እየኖሩ አሁንም ከጫካው ፖለቲካቸው ጋር ነፍሳቸው ተጣብቆ የአልባኒያን ዲሪቶ ዲሞክራሲ እየጎተቱ ለተከበረው የትግራይ ሕዝብ ደንታ ሳይሰጣቸው የጀመሩትን የማተራመስና የማሸበር ተግባር ቀጥለውበታል::

ዛሬ እንኳን በአስራ አንደኛው ሰአት ለትግራይ ሕዝብ ቢያስቡ ኑሮ ደቡብ አፍሪካ የሚደረገውን የሰላም ንግግር በሽምጋዮች በኩል ተደራድረው ትጥቃቸውን ፈተው ለሰላም እጃቸውን ለመስጠት መስማማት ይጠበቅባቸው ነበር: : ቢያንስ ይህን ሁሉ ጥፋት ካጠፉ በኋላ ተፀፅተው አብሮ ለመኖር. በኢትዮጵያዊነት ለመተሳሰር በደልን ለመርሳትና የጋራ አገርን በጋራ ጠብቆ ለትውልድ ለማስተላለፍ ወዘተ..ቃል መግባትና የሕብረቱን ሽምግልና መቀበል ነበረባቸው: :

ነገር ግን ላለፉት ሀምሳ አመታት ቡድኑ የትግራይን ሕዝብ የአመፅ ትርምስ ባሕል ፈጥሮ ያአፈሰሰው ደምና እንባ አልበቃ ብሎት ትግራይን በራሷ ልጆች የገና ዳቦ እያደረጓት ይገኛል። ዛሬ በተግባር እንደምናየው ከላይም ከታችም በእሳት እንድትነድ አድርገዋታል። ግን አሁንም ድረስ ትግራይን የእርስ በእርስ ፍጅት መፅነሻ በማድረግ ጀርባዋ የተላላጠ እንዲሆን በማድረጋቸው ሲጸጽታቸው አይታይም::

ደቡብ አፍሪካ ላይ ለሰላም ውይይት ተቀምጠው አብይ ነጥቦች እያሉ የሚያስማሙባቸው ሀሳቦችም በልዩነት ላይ ብቻ ያለቅጥ አትኩረው ችግሮቹን ለመፍታት አለመፈለጋቸው ምን ያህል በጥፋትና በተስፋ መቁረጥ ውስጥ መዘፈቃቸውን አመላካች ነው። ስህተትን መቀበልና ማረም እንደ ነውር የሚቆጥሩት አሸባሪዎቹ ትህነጎች፣ የተሠጣቸውን የሰላም ዕድል ላለመጠቀም ለሰላም እጇን የዘረጋውን የኢትዮጵያ ሕዝብና መንግስት አሻፈረኝ ብለው ስለ አጉል ግትር ፀባያቸው ተጨማሪ ዋጋ መክፈላቸው አይቀሬ ነው : :

የኢትዮጵያ ስጋት የሆነው አሸባሪው ትህነግ ሕገ መንግስቱን አክብሮ ትጥቁን ሲፈታ ብቻ መሆኑን የኢትዮጵያ መንግስት አቋሙን አስታውቋል። በትዕግስትና በብልሀት የሰላም ውይይቱ እንዲሳካ የአገራችንን ብሔራዊ ጥቅም በማይነካና በሉአላዊነታችንና በክብራችን እንደማንደራደር አስቀድሞ ይፋ በመድረጉ የኢትዮጵያን መንግስት ምስጋና ይገባዋል : :

አሸባሪው ትህነግ ግን ለጥፋት አላማ ግብ መምቻ የያዙትን አገር የማፈራስ ተልእኮ በሚተናነቃቸው ኢትዮጵያዊነት የታሪክ ፍርድ እንደሚቀበሉ በእርግጠኝነት መናገር ይቻላል:: የኢትዮጵያ አምላክም ይችን አገር ጥሎ አይጥላትምና ለኢትዮጵያ የደገሱላትን ጥፋት የሕዝብ እንባ እርግማን ሆኖ በምድራቸው በበደሉት ሕዝብ ፊት ላደረሱት በደል ዋጋ ይከፍላሉ :: ያን ግዜ ከትግራይ ሕዝብ ወንድሞቻችን ጋር በጋራ ሆነን የጠላሽ ይጠላ በማለት አብረን እንዘምራለን:: ለዛሬው በዚሁ አበቃሁ በሌላ ርዕስ እስከምንገናኝ ቸር እንሰንበት::

# መቼም አንረሳውም !

ፎቶ - በእዮብ ተፈሪ

በመልካምሥራ አፈወርቅ እና ፅጌረዳ ጫንያለው

**ጥቅምት 24 ቀን 2013 በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ የተለየች ቀን ናት። አሸባሪውና ከሃዲው የትህነግ ቡድን ከ20 ዓመታት በላይ የትግራይ ህዝብን ሲጠብቅ የነበረውን የሰሜን ዕዝን ከጀርባው የወጋበትና አሳፋሪ ታሪክ የፈፀመበት ቀን ነው። ይህች ቀን መከላከያ ብቻ ሳይሆን የኢትዮጵያ ህዝብም የተከዳበት ቀን ነው። ዘንድሮም ለሁለተኛ ጊዜ ‹‹መቼም አንረሳውም ›› በሚል መሪ ቃል ቀኑ በመከበር ላይ ይገኛል። ይህቺን ቀን በተመለከተ የአዲስ አበባ ነዋሪዎችም እንደሚከተለው ያስታውሷታል።**



## ‹‹ጥቃቱ ክህደት እንጂ ጀግንነት አይደለም››

**- ወጣት ፍጹም ዓለሙ**

ወጣት ፍጹም ዓለሙ የጥቅምት ሀያ አራቱን የሰሜን ዕዝ ጥቃት ዛሬም ድረስ በቁጭት ያስበዋል። ህዝብ የሚጠብቅ፣ ለአገር ደጀንና መከታ በሆነ ሠራዊት ላይ ግፍ መፈጸሙ ዛሬም ድረስ እንደሚያሳዝነው የሚገልጸው በተለየ ስሜት ነው።

‹‹የዛሬ ሁለት ዓመት የጥቅምት ሀያ አራትን ጥቃት የሰማሁት በድንገት ነበር። በመከላከያ ሰራዊታችን ላይ የተፈጸመው ግፍና በደል እንደ አንድ ወጣት ኢትዮጵያዊ በእጅጉ አሳዝኖኛል። በወቅቱ እውነቱን በተረዳሁ ጊዜም ስሜቱን የተቀበልኩት ከዕንባ ጋር ነበር። በጣም የሚገርመው ይህ ክደት የተፈጸመው በራስ ወገን እጅ መሆኑ ነው። ይህ ደግሞ ክፋትን፣ ክህደትን ያመለክታል።

የመከላከያ ሰራዊታችን የህዝብና የአገር ደጀን ነው። በሰራዊቱ መከታነት ድንበር ተከብሮ ህዝብ ሰላም ውሎ ያድራል። ይህን ታላቅ መስዋዕትነት በሚፈጽም ሰራዊት ላይ ያልታሰበ ጥቃት መፈጸም ደግሞ ጀግና አያሰኝም።

አገራችን ኢትዮጵያ ከጥንት አስከ ዛሬ በጀግኖች ልጆቿ ታፍራና ተከብራ ኖራለች። ዛሬም ይህ ታሪካዊ ተጋድሎ ከቆራጥ ልጆቿ ጋር እንደዘለቀ ነው። አሁንም በጀግናው የመከላከያ ሰራዊታችን ደጀንነት እንኮራለን። በሰራዊታችን የጀግንነት ውሎ የአገራችን ሉዓላዊነት ተከብሮ ይኖራል።

በእኔ ዕምነት ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ባለበት በቆመበት ሙያ ለአገሩ ከልብ ካገለገለ እንደ መከላከያ ሰራዊት ዘብ እንደቆመ ይቆጠራል። ሁላችንም ባለን አቅም፣ በያዝነው ችሎታ ለሰራዊታችን አጋርነታችንን ልናሳይ ይገባል። ሁሌም ጀግንነት ታሪካችን ነው። ድል ማድረግ ደግሞ ልምዳችን ነው ብሏል።

## ‹‹አይደለም የአገር መከታ የሆነ ወታደር ሰው ጠላት እንኳን በተኛበት አይታረድም››

**- ወጣት ብርሃን ፋንታሁን**

ወጣት ብርሃን ፋንታሁን ይባላል። የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪ ነው። ጥቅምት 24ን ሲያስታውሰው ቀድሞ እንባ ይቀድመዋል። ምክንያቱም ይህ ጊዜ ዘግናኝና ግፍ የበዛበት ቀን ነው። እንደ ኢትዮጵያዊነት ብቻ ሳይሆን እንደሰውም ሊደረግ ቀርቶ ሊታሰብ የማይገባው መሆኑን ያነሳል። ተግባሩ በምን አማርኛ መግለጽ እንዳለበትም ግራ ይገባዋል። ‹‹አይደለም የአገር መከታ የሆነ ወታደር ጠላት እንኳን በተኛበት አይታረድም›› ፤ አሸባሪው የከወነው ተግባር ግን ጀግንነት አይሉ ጅልነት በምን መልኩ እንደሚፈረጅ የማይታወቅ ነው። ጀግና የሆነ ሰው ጀግንነቱን ማሳየት ያለበት ሰው አይቶት ፀሐይ ሞቆት ነበር። እርሱ ግን ሰነፍና ተሸናፊ ስለሆነ መከላከያውን የደከመ አዕምሮውን ለማሳረፍ በተኛበት የግፍ ግፉን ፈጽሞበታል።

አሸባሪው ሕወሓት በምንም መልኩ ማሸነፍን እንደማይቀናጅ ስለሚረዳ ስልታዊ የሚባል ነገርን አያውቅም። ፊት ለፊት መጋፈጥንም አይደፍርም። በዚህም በውሸት ፕሮፓጋንዳ ሕዝብን ያሸብራል፤ በጅምላም ይጨፈጭፋል። ይህ ተግባሩ ደግሞ በመከላከያው የጀመረው ነው። ቢያውቀው ኖሮ መከላከያ ለሰዎች ነጻነት ሲል ተራራና ሸንተረሩ፤ ቁሩና ሐሩሩ የሚፈራረቅበት ነው። ለሕይወቱ ሳይሳሳ ቅድሚያ አገሬ ትኑር የሚል ነበር። ሆኖም የአገር ክብር የማይገባው ስለሆነ የጭካኔን ጥግ በእርሱ ላይ አድርጓል።

አሸባሪው ሕወሓት ሁሌ እየሰራው ያለው ተግባር ተመሳሳይ ነው። ይህም ሁለት ነገር ሲሆን፤ የመጀመሪያው አገርን ማጥፋት ነው። ሁለተኛው ደግሞ ሕዝብን መጨረስ ነው። በዚህ ደግሞ የውጪ አካላት በተከታታይ ሲደግፉት ይታያል። ምክንያቱም የአገርን ውድመት ይፈልጋሉና። ስለሆነም እንደህዝብ መደረግ ያለበት አንድነትን በማጠንከር ያሰበውን ነገር እንዳይሳካለት ማድረግ ነው። ምክንያቱም እርሱ ሁሌ መልካም ነገር ቢደረግለትም ይቅርታና ሰላምን አይወድምና ከምድረገጽ ማጥፋቱ ላይ መስራት ያስፈልጋል። እድል እየተሰጠው ያልተማረን ሰላም ጠል አካል ተንከባክቦ ማኖር ትርፉ ኪሳራ እንጂ ሌላ ሊሆን አይችልምና እንደ አገር ይህንን አስቦ መስራት ተገቢ ነው።

ሕወሓት በሰራው ሴራና በአደረገው ተግባር



መተማመንን ጭምር ነጥቋል። ምክንያቱም ሲያገለግለው የነበረውን ከማረድ በላይ ክህደት የለም። አብሮ አደግን፤ ቤተሰብን ማረድ ደግሞ ነገ አምኖ አብሮ መራመድን በምንም መልኩ ሊያመጣ አይችልም። ስለዚህም እርሱ የነጠቀንን እምነት እኛ መገንባት ላይ መረባረብ አለብን።

## ‹‹የመከላከያ ሰራዊቱ መከዳት የአገር መከዳት ነው››

**- ወጣት ፋሲካ ታደለ**

ወጣት ፋሲካ ታደለ ጥቅምት 24ትን በተለየ ሁኔታ ታስታውሰዋለች። በሁለት መልኩ ከፍላም ታብራራዋለች። የመጀመሪያው ከአገር አንጻር ያለውን አንድምታ ሲሆን፤ መከላከያ የሌለው አገር የፈረሰ አገር ነው። ስለዚህም አሸባሪው ሕወሓት ሲሰራ የቆየው የፈረሰች አገር እንድትኖረን ነው። ያንን ለማድረግ ደግሞ ሲሰሩ ቆይተው እፎይ ለማለት የተኙትን ወታደሮች በግፍ ጨፍጭፏል። ሁለተኛው እንደሴትነት የሚነሳው ተግባር ሲሆን፤ ሴቶች ላይ ያደረሱት የሰብዓዊ መብት ጥሰት በዓለም ላይ ጭምር ታይቶና ተሰምቶ የማይታወቅ ነው።

አገር ለመምራት ሞራል ያስፈልጋል፤ ሕዝብም አመኔታ ሊጣልበት ይገባል። ነገር ግን እነርሱ ሁለቱንም ሳይዙ አገር ካልመራን በሚል ተልካሻ ምክንያት ዛሬ ድረስ በጦርነት ውስጥ እንድንቆይ ፈርደውብናል። ከዚህ አንጻርም የእነርሱ ፍላጎት ግላዊ ጥቅምና ገንዘብ ነው ብዬ እንዳምን አድርጎኛል።

አሸባሪው ሕወሓትና መከላከያ በእርሱ ውስጥ ሕዝብን ሲያገለግሉ የቆዩ ቢሆኑም ሁለቱ የሥራም፤ የወዳጅነትም፤ የቅርበትም ትስስር ነበራቸው። እንደውም የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታ ነበሩ። ምክንያቱም



ሕወሓት መሪ ድርጅት ነበር። ስለዚህም በእርሱ አመራር ውስጥ ሆነው ለአገር ያልሰሩት ነገር የለም። ነገር ግን ‹‹በአጎረስኩ እጄን ተነከስኩ›› ሆነ ነገሩ። በጓደኛ፤ በቅርብ ወዳጅ መከዳት ምን አይነት ስሜት እንዳለው ሁሉም ያውቀዋል። ይህ ነውም በመከላከያና በሕወሓት መካከል የሆነው። ስለዚህም አሸባሪው ሕወሓት እምነትንም እውነትንም የቀበረ ተግባር ፈጽሟል ብንል ማጋነን አይሆንም።

ሕወሓት ትናንትም የራሱ አይደለም አሁንም የራሱ አይደለም። ነገም ራሱን ሆኖ አገር የሚመራ አይሆንም። ይህ ደግሞ የሚመጣው የሌላ እስትንፋስ ሲኮን ነው። ተላላኪና የተባለውን የሚያደርግ በመሆኑ ሁሌ ጦርነትን እንጂ ሌላ አይፈልግም። ለዚህም ማሳያው አገርን ከድቶ፤ መከላከያን ወግቶ ሰላማዊ ድርድር ይደረግ ሲባል፤ ተኩስ አቁም ሲታወጅ አሻፈረኝ ብሏል። ስለሆነም የራሱን ዓላማ ያልያዘ ድርጅት ነውና እስከመጨረሻው ታግለን ልንረታው ይገባል። የአስተሳሰቡ ተከታዮችንም ቢሆን ማስቆም አለብን። ለዚህ ደግሞ አንድነታችን ወሳኝ ነው። አባቶች በዚህ ዙሪያ መስራት አለባቸው።

አሁን አሸባሪው ሕወሓት ተስፋ የቆረጠበት ጊዜ ላይ ይገኛል። ስለዚህም የመጨረሻ የሚለውን የጭካኔ ስራ መስራቱ አይቀርም። ስለሆነም መንግስትም ቆራጥ ውሳኔ ማስተላለፍ ይገባዋል። ሕዝብም እንደ ሕዝብ ማድረግ ያለበትን ያህል ማድረግ ይገባዋል።

## ‹‹ያን ክፉ ዜና በሰማሁ ጊዜ ስለአገሬ በእጅጉ አልቅሻለሁ››

**-እማማ ድልድል ገብሬ**

እማማ ድልድል ገብሬ ይባላሉ። የእድሜ ባለጸጋ ወይዘሮ ናቸው። እማማ ድልድል በአገራችን ላይ የተቃጣውን ጦርነት ሲያስቡ በእጅጉ ያዝናሉ። የእሳቸው ምኞትና ፍላጎት አገር ሰላም ውላ እንድታድር ሕዝብ በፍቅር እንዲኖር ነው።

‹‹ ኢትዮጵያ አገሬ ዕድሜዬን ሙሉ ጌጤ መዋቢያዬ ሆና ኖራለች። ጉልበት በነበረኝ ጊዜ ያሻኝን ሰርቼ አድሬባታለሁ። ተድሬ የተኳልኩት፤ ወልጄ ወግ ማዕረግ ያየሁት በዚህች ድንቅ ምድር ነው። በእርሷ ላይ ብዙ አግኝቻለሁ። ወድቄ ተነስቻለሁ፣ አዝኜ ስቄያለሁ። ወጣትነቴን አልፌ ከእርጅናው ዘመኔ የደረስኩትም በኢትዮጵያ ክንድ ላይ ነው።

ለእኔ ይህች ምድር ትርጉሟ ይለያል። አልባሽ አጉራሼ፣ አሳዳሪ መኖሪያዬ አገሬ ኢትዮጵያ ናት። ሰላም ውላ ባደረች ጊዜ እፎይታው ለሁላችንም ነው። ሰርተን ለመኖር፣ ተኝተን ለማደር መተማመኛ ይኖረናል። በጦርነት ፈተና ሰላም ባጣች ጊዜ ህመሙ የሁላችንም ነው። ማንኛችንም ብንሆን ያለሰላም ኑሮና ህይወት የለንም።

እውነቱን ተናገሪ ካላችሁኝ ለእኔ ኢትዮጵያ ከልብ ታሳዝነኛለች። እንደውም አንዳንዴ ምን እንደማደርጋት፣ እንዴት እንደምገልጻት ሁሉ ግራ ይገባኛል። ልብስ አይደለች እንደጨርቅ አለብሳት፣ እንደው ምን ላድርጋት? እያልኩ እጨነቃለሁ። ይህን ሁሉ የማስበው ለእሷ ካለኝ የተለየ ፍቅር ነው። ሰላሟ፣ ለሁላችንም ሰላም መሆኑን አውቃለሁ። አገራችን በቸር ውላ ማደሯ ጥቅሙ ለጋራችን ነው።

የዛሬን አያድርገውና እኔ በአገሬ ሰርቼ ተከብሬያለሁ፣ አግኝቼም ኮርቻለሁ። እጄን የሚያውቁ ሙያዬን የሚሹ ሁሉ ወደ እኔ ሲመጡ ማናት ከወዴት ናት ብለው አልነበረም። በእኔ ወጥና እንጀራ ጠላና ጠጅ ያልተዳረ፣ ያልተኳለ የለም። ይህ ሁሉ የሆነው ሰላም በመኖሩ ልዩነት ባለመፈጠሩ ነው።

አሁን ዕድሜዬ ገፍቷል። እንደቀድሞው ሮጬ



ማደር፣ ሰርቶ መግባት አይሆንልኝም። ባለኝ አቅም ውዬ ለመመለስ ግን ሰላም እፈልጋለሁ። እስከዛሬ ብዙ ሰምተናል፣ ብዙ ደርሶብናል፣ ጦርነት ያላሳጣን ያልወሰደብን የለም። አሁን ይህ አይነቱ መከራ ቢበቃን ምኞቴ ነው።

አዎ! ይብቃን አገራችን ሰፊ፣ ምድራችን ወርቅ ናት። ተስማምተን፣ ተከባብረን ካደርን፣ ለሁላችንም ትበቃለች። ለሰው፣ ለአውሬና እንስሳው የምትበቃ የማትቆረቁር አገር አለችን። ልንጣላ ልንጋጭ አይገባም። ጦርነት ለማንም አይበጅም። አገር ያፈርሳል፣ ህይወት ይነጥቃል።

እኔ አገሬ ወሎ ወልድያ ነው። ከወጣትነት አስከ እርጅና የዘለቅሁት ግን በአዲስ አበባ ነው። በትውልድ ስፍራዬ ያሉ ወገኖቼ በጦርነቱ ማለቃቸውን ሰምቼ አዝኛለሁ። የዛሬ ሁለት ዓመታ በወታደሩ ላይ ሆነ የተባለውንም አውቃለሁ።

በወቅቱ ያን ክፉ ዜና በሰማሁ ጊዜ ስለአገሬ በእጅጉ አልቅሻለሁ። የጠፋው ህይወት፣ የፈሰሰው ደም ያሳዝናል። ዛሬም ስለአገሬ አብዝቼ እፀልያለሁ። የእኛ መኖር በእሷ ላይ ነውና ስለሰላሟ ፈጣሪዬን ዘወትር እማልዳለሁ።

# “ጥቅምት 24ን ስናስብ የአሸናፊ እና ተሸናፊ ትርክትን ለመፍጠር ወይም ቂምና ጥላቻ እንዲነግስ ሳይሆን እንዲህ ዓይነት ታሪክ እንዳይደገም ትውልድ እንዲማርበት ለማድረግ ነው”

**- የመከላከያ ሚኒስቴር**

## የጥቅምት 24 2ኛ ዓመትን መታሰቢያን አስመልክቶ የተሠጠ አጭር ማብራሪያ፡-

ዕለቱን የተለያዩ የሕብረተሰብ ክፍሎች አስበውት እንዲውሉ ይጠበቃል። በሠራዊታችን በኩል በመከላከያ ጠቅላይ መምሪያን ደረጃ በልዩ ሥነ-ሥርዓት፤ እንዲሁም በሀገር ውስጥና በውጭ ያሉ የሠራዊታችን ልዩልዩ ክፍሎች አመራርና አባላት፤ ሲቪል ሰራተኞች ታስቦ ይውላል።

እንደሚታወቀው ጥቅምት 24 ቀን 2013 ዓ/ም አሸባሪውና ክህደት የማይሰለቸው ሕወሓት ሀገር የማፍረስ ተግባሩን ይፋ ያደረገበት ዕለት ነበር። ቀድሞ ተዘጋጅቶ እና የተለያዩ ስልቶችን ተጠቅሞ፤ በተመሳሳይ ቀንና ሰዓት በሠራዊታችን በተለይም በሰሜን ዕዝ ላይ ሀገራችን ቀርቶ ለዓለም እንግዳ እና ኢ-ተገማች በሆነ መልኩ ጭፍጨፋ የተፈፀመበት ቀን ነው።

ጥቅምት 24ን ስናስብ የአሸናፊ እና ተሸናፊ ትርክትን ለመፍጠር ወይም ቂምና ጥላቻ እንዲነግስ ሳይሆን እንዲህ ዓይነት ታሪክ እንዳይደገም ትውልድ እንዲማርበት ለማድረግ ነው።

ሀገሩን ለመከላከል ብሎ ከጥንት አያት ቅድመ አያቶቹ የወረሰውን የሀገር ፍቅር ስሜት እና ጀግንነት ለማስቀጠል መስዋእት እየሆነ ከራሱ በፊት ሕዝብን አስቀድሞ ተልዕኮውን በሁሉም የሀገሪቱ ክፍሎች እየተወጣ የነበር ሠራዊት ነው።

ትግራይ ክልልም በፍፁም ወታደራዊ ዲሲፕሊንና ሕዝብ አክባሪነት ከሃያ ዓመታት በላይ ተግባሩን ሲወጣ ቆይቷል። ይሁን እንጂ በመለዮው ጥላ ስር ከፉና ደጉን አብረው ያሳለፈ፤ ወገኔ፤ ጓዴ ብሎ ባመናቸው መከዳቱን፤ ደግመን ደጋግመን ስናስበው ለማመን የሚከብድ ከአዕምሮ በላይ የሆነ ቃላት የማይገልፀው ጭካኔ ነበር። ይህ ተግባር እኛ ኢትዮጵያውንን የማይመጥን መጥፎ




የታሪካችን ጠባሳ ስለሆነ ዕለቱን ስናስብ ከእንደዚህ አይነት ጥፋቶች ላለመላመድና ላለመውረስ ፤ እንዲህ አይነት ጥፋት በራሱ፤ አጥፊዎችም የሚያጠፉ እንደሆነ የምንማርበት አጋጣሚ አድርጎ ማሰብ ይገባል።

የተቋማችን ሪፎርም ዋናውና ማጠንጠኛ የሆነው ነጥብ ገለልተኛና የሀገሩን ሉዓላዊነት የሚጠበው ተቋም መገንባት መቻል ነው። ይህ አቅጣጫ በንድፈ ሃሳብ ደረጃ ትክክል ስለሆነ ብቻ ሳይሆን በተግባር ጥቅምት 24 ገለልተኛ ያለመሆን ችግር ምን ያክል ዋጋ እንደሚያስከፍል ያሳዩን በመሆኑ ነው፤ ገለልተኛ የምንሆንበት አንዱ ከብሔርተኝነት እሳቤና ተግባር ነው። ወያኔ ከዚህ ባለመፅዳቱ ነው ሠራዊታችን ያስጨፈጨፈው። የኔ የሚለውን የብሄር ታጣቂ በዘር አነሳስቶ፤ ኮትኩቶና አሰማርቶ ሌላውን የኢትዮጵያ ሠራዊት በብሔር ሳይለይ፤ በሃይማኖት ሳይለይ፤ በፆታ፤ በእድሜ ሳይለይ በጅምላ ዘግናኙን ወንጀል የፈፀመው።

ሁለተኛው ከፖለቲካ ወገን ነፃ መሆን ነው። ይህን ስንልም አሁንም ማሳያው ጥቅምት 24 ነው። የታላቋና ታሪካዊት ሀገር ኢትዮጵያ ሠራዊት ከመሆን ይልቅ ለአንድ የፖለቲካ ፓርቲ ወግኖ የፓርቲውን የፖለቲካ ዓላማም እንደ ሃይማኖት ቀኑና አምኖና ከዛም በላይ ሰለባ ሆኖ ከሽብር ቡድኑ ሕወሓት አስተሳሰብ ውጭ ያለውን በለመደው የፓርቲው ክህደት ሠራዊታችን ግማሹን ግብዣ ብሎ ጠርቶ የፈሪ ዱላወን ያሣረፈባቸው። ስለዚህ ከብሔር፤ ከፖለቲካ፤ ከሃይማኖት ወገንና ገለልተኛ ተቋም መገንባት አለበት ተብሎ ስራ በተጀመረ አጭር ጊዜ ውስጥ መልካም ውጤት መመዝገብ የቻለው ከጉዳታችንም ጭምር በተግባር መማር ስለቻልን ነው።

ሌላው በመከላከያ መሪ መዝሙር “ከመሞት በላይ እንሙት ደማችን ሺ ጊዜ ይፍሰስ፤ አየር አፈሯ ይባረክ ምንጊዜም ስሟ ይታደስ። “የዘመርንላት ኢትዮጵያን ከሞት በላይ ሊገሉን የሞከሩት፤ እንዴት ጥሰን አልፈን የማይሞት ታሪክ እንደሰራን፤ እንዴት ከችግር ወደ ድል መሸጋገር እንደቻልን ያሳየንበት ዕለትም ነው።

ሠራዊታችን ላይ ጠላቶቻችን ሊሳለቁ ቢያስቡም፤ ሥርዓትና የሥርዓቱ መሪዎች እንደሌላት ሀገር፤ ጠባቂ ሠራዊት እንደሌላት ሀገር፤ ከማን ጋር ነው የምንደራደረው ቢሉንም፤ ሠራዊታችን እንዲበተንና በትዕቢት እጅ እንዲሰጥ ቢጋበዙም፤ ጠቢቡ “እጅ ስጥ አለኝ ፈረንጅ፤ እጅ ተይዞ ሊወሰድ? ምን እጅ አለ የሳት ሰደድ፤ አያውቅም እንጂ ክንጄ እንደሚያነድ” ብሎ ሎሬት ፀጋየ ገ/መድን እሳት ወይ አበባ የግጥም መድብሉ ለአፄ ቴዎድሮስ መቅደላ ስንብት እንደፃፈው። እጅ ስጡ ያሉንን እብሪተኞች፤ የሠራዊታችን እጅ ቀምሰው፤ ብረት በሚያቀልጥ ክንዳችን ራሳቸው እጅ መስጠት ጀምረዋል።

የኢትዮጵያ ሕዝብ በሀገር ውስጥና በውጭም ያለው በጥቅምት 24 የደረሰብንን ግፍ በአንደበታቸውም ጭምር ሲናገሩ ሰምቶ፤ ዛሬም በክብሩ ፤ በኢትዮጵያ ጉዳይ ሳይደራደር ከጎናችን ሆኖ በሁለንተናዊ ድጋፍ ላልተለየን ሕዝባችን ከፍተኛና ልባዊ ምስጋና እናቀርባለን።

እኛም እንላለን የኢትዮጵያን ሕዝብ ይዘን፤ ኢትዮጵያንና ከፈጣሪ በታች ጠባቂ ሠራዊቷን ማሸነፍ ከቶ አይቻልም።

ኢትዮጵያ በልጆቿ መስዋዕትነት ታፍራና ተከብራ ለዘላለም ትኖራለች።

**የመከላከያ ሕዝብ ግንኙነት ዳይሬክቶሬት**

---

በኢፌዴሪ የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት
FDRE Government Communication Service

# “የሰሜን ዕዝ ሰማዕታትን በመዘከር ታሪካዊ አደራችንን እንወጣለን”

**- የመንግስት ኮሙዩኒኬሽን አገልግሎት**

ኢትዮጵያ በዘመኗ በርካታ ህልውናዋን የሚጋፉ እብሪት የወጠራቸው ሀገራት ወረራ ፈጽመው ጥቅምና ፍላጎታቸውን ለመጫን ተፈታትነዋታል፡፡ ነገር ግን ኢትዮጵያ ጀግና መውለድ ታውቅበታለችና ጀግኖች ልጆቿ ጠላቶቿን በጦርና በጋሻ ተፋልመው እንደአመጣጣቸው በመመለስ ሉዓላዊት ሀገር አስረክበውናል።

አሸባሪው ሕወሓት ከሀገራዊ ለውጡ በኋላ ለ27 ዓመታት እንደፈለገ በሕዝብ ሰብዓዊ መብቶች ላይ ሲረማመድ ቆይቶ ሀገሪቱን ለውድቀት የዳረገ ዘረፋ በማካሔዱና በዚህ ጦስ የነበረውን የፌዴራል መንግሥት ሥልጣን በማጣቱ ገና በለውጡ ጅማሬ የሕወሓት አመራሮች ሀገራዊ ለውጡን ማጥላላትን ሥራዬ ብለው ተያያዙት።

የሰሜን ዕዝ ሠራዊት ከ1990 ዓ.ም ጀምሮ መቀመጫውን በትግራይ ክልል አድርጎ ከትግራይ ሕዝብ ጋር እድሜ ልኩን የኖረ ሠራዊት ነው። ዕዙ በሰውና በመሣሪያ የመከላከያን ከፍተኛ ድርሻ የያዘ የተቋሙ ግዙፍ ኃይል ነበር። ወቅቱ መኸር በመሆኑ ሠራዊቱ የአርሶ አደሩን ሰብል መሰብሰብ እና በክልሉ ተከስቶ የነበረውን የአንበጣ መንጋ በማባረር ውሎ አዳሩን ከትግራይ ገበሬ ጋር አድርጓል።

ጥቅምት 24 ቀን 2013 ዓ.ም ሕወሓት ከሰው ልጅ በማይጠበቅ ጭካኔና በዓለም መድረክ ባልታየ ክህደት ለዘመናት በቀበሮ ጉድጓድ እየኖረ ሲጠብቀው የኖረውን የሰሜን ዕዝ ሠራዊት በተኛበት ጥቃት ከፈተበት። ሀገር እንጠብቅ ሕዝብ እናገልግል ያሉ፤ ቀን ገበሬ ሌሊት ጥበቃ ሆነው ለበርካታ ዓመታት ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይሉ፣ ቀን ሀሩሩ ሌሊት ብርዱ ሳይበግራቸው፣ ክረምት ከበጋ የሚለፉ ውድ የኢትዮጵያ ልጆች በሕወሓት የክህደት በትር ሀገር አማን ብለው በተኙበት ተወጉ።

በዚያ ጥቃት ብዙዎቹ የሰሜን ዕዝ አባላት በግፈኛው የሕወሓት ጥቃት ተገደሉ። በቅጡ እንኳ ሳይቀበሩ ጅብና አሞራ በላቸው። በሬሳቸው ላይ ከበሮ እየደለቁ ጨፈሩበት፡፡ ብዙዎቹ እየቆሰሉ አካላቸውን አጡ። እንዲሁም ታፍነው በርሃብና ውሃ ጥም እየተቀጡ ተንገላቱ። እነኝህ ታፋኝ የሰሜን ዕዝ አባላት በግፈኞች ዱላ ተደበደቡ። ተገደሉ። ሴት የሠራዊቱ አባላት በጉልበተኞች ተደፈሩ።

ሕወሓት ምንም እንኳ የሰሜን ዕዝን ሲያጠቃ በብሔር እየመረጠ በርካታ ጓዶችን ይግደል እንጂ በወቅቱ “የራሴ” ለሚላቸው የትግራይ ተወላጆች እንኳ ከመጨከን ወደ ኋላ አላለም። የሰሜን ዕዝን በሚያጠቃበት ወቅት ለሴራው ያልተባበሩትን በርካታ የትግራይ ተወላጅ የሰሜን ዕዝ ሠራዊት አመራሮችንና አባላትን ገድሎ የጭካኔውን ጥግ አሳይቶናል።

የሰሜን ዕዝ አባላት ትምህርት ቤት ሠርተው ሕፃናት ይማሩ ባሉ፣ ጤና ጣቢያ ሠርተው የእናቶችንና የሕፃናትን ሞት እንቀንስ ባሉ፤ የውሃ ጉድጓድ ቆፍረው እናቶችን ከሸክም በገላገሉ የተከፈላቸው ወሮታ የግፈኛው ሕወሓት ጥይት ሆነ።

ሕወሓት ከሃያ ዓመታት በላይ ትግራይ ክልል እየኖረ ከአነስተኛ ደመወዙ ቀንሶ ገንዘብ አዋጥቶ፣ እጁና ትከሻው እስኪላጥ ድንጋይ ፈልጦና ተሸክሞ ትምህርት ቤት፣ ጤና ኬላ፣ የወጣቶች መዝናኛ የገነባ፤ የክረምቱን ጭቃ ሳይጠየፍ የአርሶ አደሩን ሰብል ሲኮተኩት እና ሲያርም ከርሞ፤ ጠዋት ብርዱን ቀን ፀሐዩን ሳይፈራ የደረሰውን ሰብል ሲያጭድ እና ሲወቃ፤ ምሽግ ውስጥ እየኖረ የጠበቀውን፣ የሞተለትንና የቆሰለለትን የሰሜን ዕዝ ሠራዊትን ከዶ የወጋ የጭካኔና የክህደት ጥግ መታወቂያው የሆነ የማፍያዎች ጥርቅም ነው።

አሸባሪው ሕወሓት የጥቅምት 24ቱ የሰሜን ዕዝ የክህደት ጥቃት አልበቃው ብሎ ለሌላ ጦርነት ከመሰለፍ ወደ ኋላ አላለም። በ2013 ዓ.ም ሰኔ ወር መንግሥት የተናጠል ተኩስ አቁም አድርጎ ሠራዊቱን ከትግራይ ባስወጣበት ወቅት በየበርሃው ተበታትኖ የነበረውን ታጣቂውን አሰባስቦ የአፋርና አማራ ክልሎችን በስፋት ወረረ። በዚህ ወረራ ወቅትም አመራሮቹ ኢትዮጵያን ለማፍረስ ሲኦል ድረስ መሔድ ካለባቸው እንደሚሔዱ እየማሉ ተናገሩ።

በአማራና አፋር ክልሎች ምንም የማያውቁ ንፁሃን ላይ ከባድ መሣሪያ በመተኮስ እና በጅምላ በመረሸን የጥፋት መሐላቸውን በተግባር አሳዩን። ጭና፣ ጋሊኮማ፣ እና ሌሎች ቦታዎች ላይ ያለርህራሔ ንፁሃን ዜጎችን በጅምላ ገደሉ። ከትልልቅ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች እስከ የገበሬው ቤት ድረስ ዘረፉ፤ አወደሙ፤ አቃጠሉ። የአርሶ አደሩን ሰብል አጭደውና ወቅተው ከመውሰድ እስከ በእሳት ማቃጠል የደረሰ ጉዳት አደረሱ። ህሊናቸውን የሸጡ ሕወሓታውያን ከመነኩሴ እስከ ህፃናት ያሉ ሴቶችን አስገድደው ደፈሩ።

የጀመሩት ወረራ በጀግናው ሠራዊታችን ጠንካራ ምት ተፈረካክሶ ከአፋርና አማራ ክልል ተጠራርገው ሲወጡ መንግሥት የተኩስ አቁም ስምምነት አድርጎ ባለበት ሰአት ነሐሴ 18 ቀን ሦስተኛ ወረራ ከፈቱ።

ደብተር ይዘው ትምህርት ቤት መሔድ ከነበረባቸው ህፃናት እስከ መነኩሴ ድረስ በግድ ወደ ግንባር በማምጣት የትግራይን ሕዝብ ለጥይት ማብረጃነት ተጠቀሙበት፡ ፡ ሕወሓት ከሀገር ውስጥ ባንዳዎች እስከ ታሪካዊ ጠላቶቻችን ጋር በመተባበር ወረራ ቢከፍትም የብርቱውን ሠራዊታችንን ክንድ መቋቋም አልቻለም። ትንሽ ድል ሲያገኝ የሚፎክረው፤ ሲሸነፍ ደግሞ የሚያለቅሰው ሕወሓት ከኢትዮጵያ ሕዝብ በዘረፈው ከፍተኛ ሀብት የውጭ ሀገር ሰዎችን (ሎቢስት) ቀጥሮ ፕሮፓጋንዳ ቢያስነዛም ውጤቱ ኪሳራ ሆኖበታል።

ይህን ኢትዮጵያን የማፈራረስ ተልዕኮውን ለማሳካትም አንዴ በጦርነት ሌላ ጊዜ ደግሞ በድርድር ጊዜ ሸምቶ ለማገገም ያለመታከት እየሠራ ይገኛል። ግን እኛ የአባቶቻችን ልጆች ነን። በየትኛውም ግንባር እንፈተናለን እንጂ ፈጽሞ አንሸነፍም።

ምንም እንኳ አሸባሪው ሕወሓት ቀደም ብሎ በሰሜን ዕዝ ላይ ቀጥሎም በመላው ኢትዮጵያ ላይ የፈጸመው ጥቃትና ወረራ መዘዙ እስከዛሬ ድረስ ዘልቆ ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያታያን ላይ ከፍተኛ የሰብአዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ቀውስ እንዲሁም ዓለም አቀፍ ጫና ያስከተለ ቢሆንም ሁሉንም በአሸናፊነትና ድል እየተወጣን እንገኛለን።

ከመላው ሕዝባችን ጋር ሆነን ባደረግነው ታላቅ ተጋድሎ ሕወሓት ራሱ በለኮሰው ጦርነት ሊጠፋ የመጨረሻው ምዕራፍ ላይ ደርሰናል፡፡ የሰማዕታቱን ፍሬ የምናይበትና ድሉን የምንዘክርበት ወቅት ላይ ነን።

እኛ አደራ የምንዘነጋ ሳንሆን የወንድሞቻችንን፣ የኢትዮጵያን ክብርና የግዛት አንድነት የማስጠበቅ ተጋድሎ ከዳር ለማድረስ አስፈላጊውን ሁሉ መስዋዕትነት በጀግንነት ለመክፈል የተዘጋጀን ነን።

አሸባሪው ሕወሓት የፈፀመብን በደልና ሰቆቃ ተቆጥሮ የማያልቅ በታሪክና ትውልድ ፊት ይቅርታ የማይቸረው ነው፡፡ በወንድሞቻችን ላይ የደረሰውን ግፍና መከራም መቼም አንረሳውም፡፡ ነገር ግን እኛ እንደ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ኃይል ሕዝብና ሀገርን አጽንተን የምናስቀጥል ሕዝባዊ ሠራዊት ነን፡፡

ስለሆነም በደልን ስንቆጥር የምንኖር ሳንሆን የኢትዮጵያን ሕዝብ በተለይም የትግራይን ሕዝብ ከሕወሓት የዘመናት ባርነትና ጭቆና ነፃ ለማውጣት የከፈልነውንና እየከፈልን ያለነውን መስዋዕትነት አጠናክረን በመቀጠል የመጨረሻው የድል ዋዜማ ላይ ሆነን ሰማዕታትን እየዘከርን ኢትዮጵያችንን አስከብረን በአሸባሪው ሕወሓት መቃብር ላይ ድላችንን እናበስራለን።

“ጥቅምት 24ን መቼም አንረሳውም!!”

ክብርና ሞገስ ለተሰዉ ሰማዕታት!!





አሸባሪው ትህነግ ሠራዊቱ በተኛበት የግፍ ጭፍጨፋ ፈጽሞበታል













አሸባሪው ትህነግ አፍኖ የያዛቸውን የሠራዊት አባላት አሠልፎ ሲኖ ትራክ ነድቶባቸዋል፡፡







አሸባሪው ትህነግ የመከላከያ ሠራዊት አባላት ቤተሰቦችንም ለሠቆቃ ዳርጓል፡፡



አሸባሪው ትህነግ ሴት የሠራዊቱ አባላት ላይ ታሪክ ይቅር የማይለው ግፍ ፈጽሟል



አሸባሪው ትህነግ ጥቃት በፈጸመበት ምሽት በምጥ ተይዛ በትግራይ እናቶች እርዳታ የወለደች እናት አሸባሪው ቡድን ደብቆ በማቆየት ለመከላከያ ሠራዊት ያስረከባት ወታደር